ምድረ ፡ በዓ ፡ በቃዲስ ፡ ባለው ፡ በመሪባ ፡ ውኃ ፡
ስለ ፡ በደላችሁኝ ÷ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
፶፪፡ መካከል ፡ ስላልቀደሳችሁኝ ÷ ምድሪቱን ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ታያለህ ፡ እንጂ ፡ ወደዚያች ፡ እኔ ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደምሰጣቸው ፡ ምድር ፡
አትገባም ።

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

፩፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሙሴ ፡ ሳይሞት ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የባረከበት ፡ በረከት ፡
፪፡ ይህች ፡ ናት ። እንዲህም ፡ አለ ፡—
እግዚአብሔር ፡ ከሲና ፡ መጣ ÷
በሴይርም ፡ ተገለጠ ፤
ከፋራን ፡ ተራራ ፡ አበራላቸው ÷
ከአእላፋትም ፡ ቅዱሳኑ ፡ መጣ ፤
በስተ ፡ ቀኙም ፡ የእሳት ፡ ሕግ ፡ ነበረላቸው ።
፫፡ ሕዝቡንም ፡ ወደዳቸው ፤
ቅዱሳኑ ፡ ሁሉ ፡ በእጅህ ፡ ናቸው ፤
በእግሮችህም ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጡ ፤
ቃሉችህን ፡ ይቀበላሉ ።
፬፡ ሙሴ ፡ ለያዕቆብ ፡ ጉባኤ ፡ ርስት ፡ የሆነውን ፡
ሕግ ፡ አዘዘን ።
፭፡ የሕዝቡ ፡ አለቆች ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡
ሁሉ ፡ ጋር ፡ በተከማቹ ፡ ጊዜ ÷
ንጉሥ ፡ በይሹሩን ፡ ነበረ ።
፮፡ ሮቤል ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ÷ አይሙት ፤
ሰዎቹም ፡ በቍጥር ፡ ብዙ ፡ ይሁኑ ።
፯፡ የይሁዳ ፡ በረከት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ አለ ፡—
አቤቱ ÷ የይሁዳን ፡ ድምፅ ፡ ስማ ÷
ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ አግባው ፤
እጆቹ ፡ ይጠንክሩለት ፤
በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ረዳት ፡ ትሆነዋለህ ።
፰፡ ስለ ፡ ሌዊም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡—
ቱሚምህና ፡ ኡሪምህ ፡ ለቅዱስህ ፡ ሰው ፡
ነው ÷
በማሳህ ፡ ለፈተንኸው ÷
በመሪባ ፡ ውኃም ፡ ለተከራከርኸው ÷
፱፡ ስለ ፡ አባቱና ፡ ስለ ፡ እናቱ ፡— አላየሁም ፡
ላለ ÷
ወንድሞቹንም ፡ ላላስተዋለ ÷
ልጆቹንም ፡ ላላወቀ ፤
ቃልህን ፡ አደረጉ ÷
ቃል ፡ ኪዳንህንም ፡ ጠበቁ ።
፲፡ ፍርድህን ፡ ለያዕቆብ ÷
ሕግህንም ፡ ለእስራኤል ፡ ያስተምራሉ ፤
በፊትህ ፡ ዕጣንን ÷
በመሠዊያህም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡
ይሠዋሉ ።
፲፩፡ አቤቱ ÷ ሀብቱን ፡ ባርክ ÷
የእጁንም ፡ ሥራ ፡ ተቀበል ፤
የሚነሣበትን ፡ ወገብ ፡ ውጋው ÷
የሚጠሉትም ፡ አይነሡ ።
፲፪፡ ስለ ፡ ብንያምም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡—
በእግዚአብሔር ፡ የተወደደ ፡ በእርሱ ፡
ዘንድ ፡ ተማምኖ ፡ ይኖራል ፤
ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ ይጋርደዋል ÷
በትከሻውም ፡ መካከል ፡ ያድራል ።
ስለ ፡ ዮሴፍም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፲፫፡
ምድሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተባረከ ፡
ይሁን ፤
በሰማያት ፡ ገናንነት ፡ በጠል ÷
በታችኛውም ፡ ቀላይ ÷
፲፬፡ በፀሐዩ ፡ ፍሬያት ፡ ገናንነት ÷
በጨረቃውም ፡ መውጣት ፡ ገናንነት ÷
፲፭፡ በቀደሙትም ፡ ተራሮች ፡ ከፍተኛነት ÷
በዘላለሙም ፡ ኮረብቶች ፡ ገናንነት ÷
፲፮፡ በምድሪቱም ፡ ገናንነትና ፡ ሞላዋ ÷
በቍጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ከነበረው ፡ በረከት ፡
በዮሴፍ ፡ ራስ ፡ ላይ ÷
ከወንድሞቹም ፡ በተለየው ፡ ራስ ፡ አናት ፡
ላይ ፡ ይውረድ ።
፲፯፡ ለላሞች ፡ በኩር ፡ ግርማ ፡ ይሆናል ፤
ቀንዶቹ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ናቸው ፤
በእነርሱ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ያሉትን ፡
አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይወጋል ፤
የኤፍሬም ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ÷
የምናሴም ፡ አእላፋት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።
ስለ ፡ ዛብሎንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፲፰፡
ዛብሎን ፡ ሆይ ÷ በመውጣትህ ÷
ይሳኮር ፡ ሆይ ÷ በድንኳንህ ፡ ውስጥ ፡ ደስ ፡
ይበላችሁ ።
የተሰወረውን ፡ የአሸዋውን ፡ መዝገብ ÷ ፲፱፡
የባሕሩንም ፡ ባለጠግነት ፡ ይጠባሉና ፡
አሕዛብን ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ይጠራሉ ፤
በዚያ ፡ የጽድቅ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዋሉ ።
ስለ ፡ ጋድም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፳፡
ጋድን ፡ ሰፊ ፡ ያደረገ ፡ ቡሩክ ፡ ይሁን ፤
እንደ ፡ አንበሳይቱ ፡ ዐርፎአል ፤
ክንድንና ፡ ራስን ፡ ይቀጠቅጣል ።
፳፩፡ በዚያ ፡ የአለቃ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ቀርቶአልና ፡
የመጀመሪያውን ፡ ክፍል ፡ ለራሱ ፡ መረጠ ፤
ወደ ፡ ሕዝብ ፡ አለቆችም ፡ መጣ ፤
የእግዚአብሔርንም ፡ ጽድቅ ÷
ፍርዱንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡ አደረገ ።
ስለ ፡ ዳንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፳፪፡
ዳን ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ነው ፤
ከባሳን ፡ ዘልሎ ፡ ይወጣል ።
ስለ ፡ ንፍታሌምም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፳፫፡
ንፍታሌም ፡ በሞገስ ፡ ጠግቦአል ÷
የእግዚአብሔርንም ፡ በረከት ፡ ተሞልቶ ፡
አል ፤
ባሕሩንና ፡ ደቡቡን ፡ ይወርሳል ።
ስለ ፡ አሴርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— ፳፬፡
አሴር ፡ በልጆች ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፤
በወንድሞቹ ፡ የተወደደ ፡ ይሁን ፤
እግሩንም ፡ በዘይት ፡ ውስጥ ፡ ያጥቅ ።
ጫማህ ፡ ብረትና ፡ ናስ ፡ ይሆናል ፤ ፳፭፡
እንደ ፡ ዕድሜህ ፡ እንዲሁ ፡ ኃይልህ ፡ ይሆናል ።

ይሹሩን ፡ ሆይ ÷ በሰማያት ፡ ላይ ፡ ለረድ
ኤትህ ÷
በደመናትም ፡ ላይ ፡ በታላቅነት ፡ እንደሚ
ሄድ ፡
እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለ ፡ ማንም ፡ የለም ።
መኖሪያህ ፡ የዘላለም ፡ አምላክ ፡ ነው ÷
የዘላለምም ፡ ክንዶች ፡ ከአንተ ፡ በታች ፡
ናቸው ፤
ጠላትህን ፡ ከፊትህ ፡ አውጥቶ ፡—
አጥፋው ፡ ይላል ።
እስራኤልም ፡ ተማምኖ ÷
የያዕቆብም ፡ ምንጭ ፡ ብቻውን ÷
እህልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ባለባት ፡ ምድር ፡
ይኖራል ፤
ሰማያቱም ፡ ጠልን ፡ ያንጠባጥባሉ ።
እስራኤል ፡ ሆይ ÷ ምስጉን ፡ ነህ ፤
በእግዚአብሔር ፡ የዳነ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡
አንተ ፡ ማን ፡ ነው ?
እርሱ ፡ የረድኤትህ ፡ ጋሻ ÷
የክፍተኛነትህም ፡ ሰይፍ ፡ ነው ።
ጠላቶችህም ፡ ይገዙልሃል ፤
አንተም ፡ ከፍታቸውን ፡ ትረግጣለህ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

ሙሴም ፡ ከሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ናቦው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡
ፈስጋ ፡ ራስ ፡ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እስከ ፡
ዳን ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የገለዓድን ፡ ምድር ÷
የንፍታሌምንም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ÷ የኤፍሬም
ንና ፡ የምናሴንም ፡ ምድር ÷ እስከ ፡ ምዕራብም ፡
ባሕር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የይሁዳን ፡ ምድር ፡
ሁሉ ÷ ደቡቡንም ÷ እስከ ፡ ዘዓር ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡ ፫፡
ውንም ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ያሉበትን ፡ ከተማ ፡
የኢያሪኮን ፡ ሸለቆ ፡ ሜዳ ፡ አሳየው ። እግዚአ ፡ ፬፡
ብሔርም ፡— ለዘርህ ፡ እሰጣታለሁ ፡ ብዬ ፡ ለአ
ብርሃምና ፡ ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ የማልሁላ
ቸው ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፤ በዓይንህ ፡ እንድ
ታያት ፡ አደረግሁህ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ወደዚያች ፡
አትሻገርም ፡ አለው ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያም ፡ ፭፡
ሙሴ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በዚያ ፡
በሞዓብ ፡ ምድር ፡ ሞተ ። በቤተ ፡ ፌጎርም ፡ ፮፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዓብ ፡ ምድር ፡ በሸለቆው ፡
ውስጥ ፡ ተቀበረ ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ መቃ
ብሩን ፡ ማንም ፡ አላወቀም ። ሙሴም ፡ በሞተ ፡ ፯፡
ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፤
ዓይኑ ፡ አልፈዘዘም ÷ ጕልበቱም ፡ አልደነ
ዘም ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ፰፡
ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ለሙሴ ፡ አለቀሱለት ፤ ለሙሴም ፡
ያለቀሱለት ፡ የልቅሶው ፡ ወራት ፡ ተፈጸመ ።
ሙሴም ፡ እጆቹን ፡ ስለ ፡ ጫነበት ፡ የነዌ ፡ ፱፡
ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የጥበብን ፡ መንፈስ ፡ ተሞላ ፤
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ታዘዙለት ÷ እግዚአ
ብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ። እግ ፲፡
ዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዳወቀው ፡
እንደ ፡ ሙሴ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡
በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አልተነሣም ፤ በግብፅ ፡ ፲፩፡
ምድር ፡ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
በምድሪቱም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ምልክትንና ፡ ድን
ቅን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ላከው ፡ ያለ ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ በጸናች ፡ ፲፪፡
እጅ ፡ ሁሉና ፡ በታላቅ ፡ ማስደንገጥ ፡ ሁሉ ፡ እን
ዳደረገው ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ያለ ፡ አልተነሣም ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡
ሙሴ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሙሴን ፡
አገልጋይ ፡ የነዌን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ ተናገረው ፡— ባሪያዬ ፡ ሙሴ ፡ ሞቶአል ፤
አሁንም ፡ አንተና ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ተነሥ ፡
ታችሁ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደምሰጣቸው ፡
ምድር ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ። ለሙሴ ፡
እንደ ፡ ነገርሁት ፡ የእግራችሁ ፡ ጫማ ፡ የሚረ
ግጠውን ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ለእናንተ ፡ ሰጥቼአለሁ ። ፫፡
ከምድረ ፡ በዳው ፡ ከዚህም ፡ ከሊባኖስ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ታላቁ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ድረስ ፡
የኬጢያውያን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡
መግቢያ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ዳርቻ
ችሁ ፡ ይሆናል ። በሕይወትህ ፡ ዕድሜ ፡ ሁሉ ፡ ፬፡
ማንም ፡ አይቋቋምህም ፤ ከሙሴ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ እንዲሁ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እሆናለሁ ፤
አልጥልህም ÷ አልተውህም ። ለአባቶቻቸው ፡— ፭፡
እሰጣችኋለሁ ፡ ብዬ ፡ የማልሁላቸውን ፡ ምድር ፡
ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ታወርሳለህና ፡ ጽና ÷ አይዞህ ። ፮፡
ነገር ፡ ግን ፡ ጽና ÷ እጅግ ፡ በርታ ፤ ባሪያዬ ፡ ፯፡
ሙሴ ፡ ያዘዘህን ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ ጠብቅ ÷ አድርገ
ውም ፤ በምትሄድበትም ፡ ሁሉ ፡ እንዲከናወን
ልህ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አትበል ።
የዚህ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከአፍህ ፡ አይለይ ÷ ፰፡
ነገር ፡ ግን ፡ የተጻፈበትን ፡ ሁሉ ፡ ትጠብቅና ፡
ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ አስበው ፡
የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መንገድህ ፡ ይቀናልሃል ፤ ይከ
ናወንልሃልም ። በምትሄድበት ፡ ሁሉ ፡ አምላ ፱፡
ክህ ፡ እግዚአሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡
ጽና ÷ አይዞህ ፡ አትፍራ ÷ አትደንግጥ ፡ ብዬ ፡
አላዘዝሁህምን ?
ኢያሱም ፡ የሕዝቡን ፡ አለቆች ፡— በሰፈሩ ፡ ፲፡፡
መካከል ፡ እለፉ ÷ ሕዝቡንም ፡— አምላካችሁ ፡
እግዚአሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ወደሚሰጣ

ችሁ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ዮር
ዳኖስን ፡ ተሻግራችሁ ፡ ልትወርሱአት ፡ ትገቡ
በታላላችሁና ፡ ስንቃችሁን ፡ አዘጋጁ ፡ ብላችሁ ፡
እዘዙአቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፲፩ ኢያሱም ፡ የሮቤልን ፡ ልጆች ፡ የጋድንም ፡
ልጆች ፡ የምናሴንም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ እንዲህ ፡
፲፫ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡— የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡
ሙሴ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያዘዛችሁን ፡ ቃል ፡ አስቡ ፡—
አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰርፋችኋል ÷
፲፬ ይህችንም ፡ ምድር ፡ ይሰጣችኋል ። ሚስቶቻች
ሁና ፡ ልጆቻችሁ ፡ ከብቶቻችሁም ፡ ሙሴ ፡ በዮ
ርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በሰጣችሁ ፡ ምድር ፡ ይቀመጡ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እናንተ ÷ ጽኑዓን ፡ ኃያላን ፡ ሁሉ ÷
ተሰልፋችሁ ፡ በወንድሞቻችሁ ፡ ፊት ፡ ተሻገሩ ÷
፲፭ እርዱአቸውም ÷ እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡
እንዳሰረፋችሁ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ እስኪያሰ
ርፍ ፡ ድረስ ÷ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ አምላካችሁ ፡
እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ምድር ፡ እስኪ
ወርሱ ፡ ድረስ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡
ሰማችሁ ፡ ወደ ፡ ርስታችሁ ፡ ምድር ፡ ትመለሳ
፲፮ ላችሁ ፡ ተወርሱአትማላችሁ ። እነርሱም ፡ ለኢ
ያሱ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡— ያዘዝኸ
ንን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እናደርጋለን ፡ ወደምትልክ
፲፯ ንም ፡ ስፍራ ፡ እንሄዳለን ። በሁሉም ፡ ለሙሴ ፡
እንደ ፡ ታዘዝን ፡ እንዲሁ ፡ ለእንተ ፡ ደግሞ ፡
እንታዘዛለን ፡ ብቻ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከሙሴ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡
፲፰ ይሁን ። በትእዛዝህ ፡ የሚያምፅ ፡ ሁሉ ፡ የም
ታዝዘውንም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ የማይሰማ ÷ እርሱ ፡
ይገደል ፤ ብቻ ፡ ጽና ÷ አይዞህ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡— ሄዳችሁ ፡ ምድ
ሪቱንና ፡ ኢያሪኮን ፡ እዩ ፡ ብሎ ፡ ከሰጢም ፡
ሁለት ፡ ሰላዮች ፡ በስውር ፡ ላከ ። ሄዱም ፡
ረዓብም ፡ ወደሚሉአት ፡ ጋለሞታ ፡ ቤት ፡ ገቡ ÷
፪ በዚያም ፡ አደሩ ። የኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡— ፡
እነሆ ÷ ሰዎች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አገሩን ፡
ሊሰልሉ ፡ ወደዚህ ፡ በሌሊት ፡ ገቡ ፡ ሰብል ፡
፫ ወሬ ፡ ሰማ ። የኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡— አገሩን ፡
ሁሉ ፡ ሊሰልሉ ፡ መጥተዋልና ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡
የመጡትን ፡ ወደ ፡ ቤትሽም ፡ የገቡትን ፡ ሰዎች ፡
፬ አውጪ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ረዓብ ፡ ላከ ። ሴቲቱም ፡
ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ወስዳ ፡ ሸሸጋቸው ፡ እርስ
ዋም ፡— አዎን ÷ ሰዎቹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጡ ÷
ከወዴት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ግን ፡ አላወቅሁም ፤
፭ በሩም ፡ ሲዘጋ ፡ ሲጨልምም ፡ ሰዎቹ ፡ ወጡ ፡
ወዴት ፡ እንደ ፡ ሄዱ ፡ አላውቅም ፤ ፈጥናችሁ ፡
አሳድዱአቸው ÷ ታገኙአቸውማላችሁ ፡ አለች ።
፮ እርስዋ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ አውጥታቸው ፡
ነበር ፡ በዚያም ፡ በረበረበችው ፡ በተልባ ፡
፯ እግር ፡ ውስጥ ፡ ሸሸጋቸው ፡ ነበር ። ሰዎቹም ፡
ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መሻገሪያ ፡ በሚወስደው ፡ መን
ገድ ፡ አሳደዱአቸው ፡ አሳዳጆችም ፡ ከወጡ ፡
በኋላ ፡ በሩ ፡ ተቈለፈ ።

፰ እነዚህም ፡ ሳይተኙ ፡ ሴቲቱ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡
ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ ወጣች ። ሰዎቹንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡
፱ ቻቸው ፡— እግዚአብሔር ፡ ምድሪቱን ፡ እንደ ፡
ሰጣችሁ ÷ እናንተንም ፡ መፍራት ፡ በላያችን ፡
እንደ ፡ ወደቀ ÷ በምድሪቱም ፡ የሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡
ከፊታችሁ ፡ እንደ ፡ ቀለጡ ፡ አወቅሁ ። ከግ
፱ ብፅ ፡ ምድር ፡ በወጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡
የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ በፊታችሁ ÷ እንዳደረቀ ÷
በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በነበሩት ፡ እናንተም ፡
ፈጽማችሁ ፡ ባጠፋችኋቸው ፡ በሁለቱ ፡ በአሞ
ራውያን ፡ ነገሥታት ÷ በሲዎንና ፡ በዐግ ፡ ያደ
፲፩ ረጋችሁትን ፡ ሰምተናል ። ይህንም ፡ ነገር ፡ ሰም
ተን ፡ ልባችን ፡ ቀለጠ ፡ አምላካችሁም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡
እርሱ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡
ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ሰማንም ፡ ነፍስ ፡ አልቀረለትም ።
አሁንም ÷ እባካችሁ ÷ በእግዚአብሔር ፡ ማሉ
፲፪ ልኝ ÷ በእውነትም ፡ ምልክት ፡ ስጡኝ ÷ እኔ ፡
ለእናንተ ፡ ቸርነት ፡ እንደ ፡ ሠራሁ ፡ እናንተ ፡
ደግሞ ፡ ለአባቴ ፡ ቤት ፡ ቸርነት ፡ እንድትሠሩ ÷
አባቴንና ፡ እናቴንም ፡ ወንድሞቼንና ፡ እኅቶቼ
፲፫ ንም ፡ ያላቸውንም ፡ ሁሉ ፡ እንድታድኑ ÷ ሰው
ነታችኋንም ፡ ከሞት ፡ እንድታድኑ ። ሰዎቹም ፡—
፲፬ ይህን ፡ ነገራችኋን ፡ ባትገልጪ ፡ ነፍሳችን ፡ በነ
ፍሳችሁ ፡ ፋንታ ፡ ለሞት ፡ ይሆናል ፤ እግዚአ
ብሔርም ፡ ምድሪቱን ፡ በሰጠን ፡ ጊዜ ፡ ከእንቺ ፡
ጋር ፡ ቸርነትንና ፡ እውነትን ፡ እናደርጋለን ፡
አሉአት ።

፲፭ ቤትዋም ፡ በከተማ ፡ ቅጥር ፡ የተጠጋ ፡ ነበ
ረና ÷ እርስዋም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበ
ርና ፡ ከመስኮቱ ፡ በገመድ ፡ አወረደቻቸው ።
እርስዋም ፡— አሳዳጆቹ ፡ እንዳያገኙአችሁ ፡
፲፮ ወደ ፡ ተራራው ፡ ሂዱ ፡ አሳዳጆቹም ፡ እስኪ
መለሱ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተሰውራ
ችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ ኋላም ፡ መንገዳችሁን ፡ ትሄ
ዳላችሁ ፡ አለቻቸው ። ሰዎቹም ፡ አሉአት ፡—
፲፯ እኛ ፡ ከዚህ ፡ ካማልሽን ፡ መሐላ ፡ ንጹሓን ፡ እን
ሆናለን ። እነሆ ÷ እኛ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ በገባን ፡
፲፰ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ቀይ ፡ ፈትል ፡ እኛን ፡ በወረድሽ
በት ፡ መስኮት ፡ በኩል ፡ እሰሪው ፤ አባትሽንም ፡
እናትሽንም ፡ ወንድሞችሽንም ፡ የአባትሽንም ፡
ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡
ሰብስቢ ። ከቤትሽም ፡ ደጅ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ የሚ
፲፱ ወጣ ፡ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ÷ እኛም ፡
ንጹሓን ፡ እንሆናለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእንቺ ፡
ጋር ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ እጅ ፡
ቢነካው ፡ ደሙ ፡ በእኛ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።
፲፡ ይህንን ፡ ነገራችንን ፡ ግን ፡ ብትገልጪ ፡ ከዚህ ፡
ካማልሽን ፡ መሐላ ፡ ንጹሓን ፡ እንሆናለን ።
እርስዋም ፡— እንደ ፡ ቃላችሁ ፡ ይሁን ፡ አለች ፡
፲፡ ሰደደቻቸውም ፡ እነርሱም ፡ ሄዱ ፡ ቀዩንም ፡
ፈትል ፡ በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ አንጠለጠለችው ።

፲፪ እነርሱም ፡ ሄደው ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ደረሱ ÷
አሳዳጆቹም ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፡
ቀን ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ፡ አሳዳጆቹም ፡ በመን
፲፫ ገዱ ፡ ሁሉ ፡ ፈልገው ፡ አላገኙአቸውም ። ሁለ
ቱም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ÷ ከተራራውም ፡ ወር
ደው ፡ ተሻገሩ ÷ ወደ ፡ ነዌም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡
ኢያሱ ፡ መጡ ፤ የደረሰባቸውንም ፡ ሁሉ ፡
፲፬ አወሩለት ። ኢያሱንም ፡— በእውነት ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡
ሰጥቶአል ፤ በአገሩም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ በፊታችን ፡ ይቀልጣሉ ፡ አሉት ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ኢያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ÷ እርሱና ፡ የእስራ
ኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከሰጢም ፡ ተነሥተው ፡
ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጡ ፤ ሳይሻገሩም ፡ በዚያ ፡
፪ አደሩ ። ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ አለቆች ፡
፫ በሰፈሩ ፡ መካከል ፡ አለፉ ። ሕዝቡን ፡— የአምላ
ካችሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦ
ትና ፡ ሌዋውያን ፡ ከካህናት ፡ ተሸክመውት ፡
ባያችሁ ፡ ጊዜ ÷ ከሰፈራችሁ ፡ ተነሥታችሁ ፡
፬ ተከተሉት ። በእናንተና ፡ በታቦቱ ፡ መካከል ፡
ያለው ፡ ርቀት ፡ በስፍር ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡
ያህል ፡ ይሁን ፤ በዚህ ፡ መንገድ ፡ በፊት ፡ አል
ሄዳችሁበትምና ፡ የምትሄዱበትን ፡ መንገድ ፡
እንድታውቁ ፡ ወደ ፡ ታቦቱ ፡ አትቅረቡ ፡ ብለው ፡
አዘዙ ።

፭ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፡— ነገ ፡ እግዚአብሔር ፡
በመካከላችሁ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ያደርጋልና ፡ ተቀ
ደሱ ፡ አለ ። ኢያሱም ፡ ካህናቱን ፡— የቃል ፡
ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ተሸክማችሁ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡
አለፉ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፤ የቃል ፡ ኪዳኑንም ፡
ታቦት ፡ ተሸክመው ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አለፉ ።
፮ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡— ከሙሴ ፡ ጋር ፡
እንደ ፡ ሆንሁ ፡ እንዲሁ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ መሆ
ኔን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡
ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግህ ፡ ዘንድ ፡ እጀ
ምራለሁ ። አንተም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡
የሚሸከሙትን ፡ ካህናት ፡— በዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡
ዳር ፡ ስትደርሱ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውስጥ ፡ ቁሙ ፡
ብለህ ፡ እዘዝ ፡ አለው ።

፯ ኢያሱም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡— ወደዚህ ፡
ቀርባችሁ ፡ የአምላካችሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ ስሙ ፡ አለ ። ኢያሱም ፡ አለ ፡— ሕያው ፡
አምላክ ፡ በመካከላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ እርሱም ፡
ከፊታችሁ ፡ ከነዓናዊውን ፡ ኬጢያዊውንም ፡
ኤዊያዊውንም ፡ ፈሪዛዊውንም ፡ ጊርጌሳዊው
ንም ፡ አሞራዊውንም ፡ ኢያቡሳዊውንም ፡
ፈጽሞ ፡ እንዲያወጣ ፡ በዚህ ፡ ታውቃላችሁ ።
፰ እነሆ ÷ የምድር ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ታቦት ፡ በፊታችሁ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ያልፋል ።
አሁንም ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
ሰዎች ፡ ምረጡ ፤ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ይሁን ። እንዲህም ፡ ይሆናል ፤ የምድርን ፡ ሁሉ ፡
ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህ
ናት ፡ እግር ፡ ጫማ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡
ሲቆም ÷ ከላይ ፡ የሚወርደው ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡
ይቋረጣል ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ ሆኖ ፡ ይቆማል ።
፱ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሊሻ
ገሩ ፡ ከየድንኳናቸው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ÷ የቃል ፡
ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ በሕ
ዝቡ ፡ ፊት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። እንደ ፡ መከር ፡
፲፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እጅግ ፡ ሞልቶ ፡ ነበ
ርና ፡ ታቦት ፡ ተሸካሚዎቹ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡
ሲደርሱ ÷ ታቦቱንም ፡ የተሸከሙት ፡ የካህናቱ ፡
እግሮች ፡ በውኃው ፡ ዳር ፡ ሲጠልቁ ÷ ከላይ ፡
፲፩ የሚወርደው ፡ ውኃ ፡ ቆመ ፤ በጸርታን ፡ አጠ
ገብ ፡ ባለችው ፡ አዳም ፡ በምትባል ፡ ከተማ ፡
በሩቅ ፡ ቆሞ ፡ በአንድ ፡ ክምር ፡ ተነሣ ፤ ወደ ፡
ዓረባ ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ ጨው ፡ ባሕር ፡ የሚወር
ደው ፡ ውኃ ፡ ፈጽሞ ፡ ተቋረጠ ፤ ሕዝቡም ፡
በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሻገሩ ። የእግዚአ
፲፪ ብሔርንም ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡
ካህናት ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ በደረቅ ፡ መሬት ፡
ጸንተው ፡ ቆመው ፡ ነበር ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡
ዮርዳኖስን ፡ ፈጽመው ፡ እስኪሻገሩ ፡ ድረስ ፡
እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ በደረቅ ፡ መሬት ፡ ተሻገሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡
ፈጽመው ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡
ኢያሱን ፡— ከሕዝቡ ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡
፪ ሰው ÷ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ምረጥና ፡—
፫ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ የካህናት ፡ እግር ፡ ከቆ
መበት ፡ ስፍራ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ድንጋዮች ፡
አንሡ ፡ ተሸክማችሁም ፡ በዚህ ፡ ሌሊት ፡ በም
ታድሩበት ፡ ስፍራ ፡ አኑሩአቸው ፡ ብለህ ፡ እዘ
ዛቸው ፡ አለው ።

፬ ኢያሱም ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ÷
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያዘጋጃቸውን ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጠራ ። ፭ ኢያሱም ፡ አላቸው ፡— ፡
በአምላካችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡
ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ አለፉ ፤ ከእናንተም ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡
ቍጥር ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ድን
ጋይ ፡ ከዚያ ፡ ይሸከም ። ፮ ይህም ፡ በመካከላ
ችሁ ፡ ምልክት ፡ ይሆናል ፤ ልጆቻችሁም ፡ በሚ
መጣው ፡ ዘመን ፡— የእነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ነገር ፡
ምንድር ፡ ነው ? ብለው ፡ ሲጠይቁአችሁ ÷
እናንተ ፡— በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ፯
ታቦት ፡ ፊት ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡ ስለ ፡ ተቋ
ረጠ ፡ ነው ፤ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገረ ፡ ጊዜ ፡ የዮ
ርዳኖስ ፡ ውኃ ፡ ተቋረጠ ÷ እነዚህም ፡ ድንጋ
ዮች ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለዘላለም ፡ መታሰ
ቢያ ፡ ይሆናሉ ፡ ትሉአቸዋላችሁ ።

፰ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኢያሱ ፡ እንዳዘዘ ፡
አደረጉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ እንደ ፡
ተናገረው ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ቍጥር ፡ ከዮር

ዳናስ ፡ መካከል ፡ አሥሬ ፡ ሁለት ፡ ድንጋዮች ፡ አንሥተው ፡ ወደሚያድሩበት ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱ ፡ ፡
፱ በዚያም ፡ አኖሩአቸው ። ኢያሱም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ እግሮች ፡ በቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ሌሎችን ፡ አሥሬ ፡ ሁለት ፡ ድንጋዮች ፡ ተከለ ! እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ አሉ ።
፲ ሙሴም ፡ ኢያሱን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲነግር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ታቦቱን ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ቆመው ፡ ነበርና ፡ ሕዝቡም ፡ ፈጥነው ፡
፲፩ ተሻገሩ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እያዩ ፡ የእግዚአብሔር ፡
፲፪ ታቦትና ፡ ካህናቱ ፡ ተሻገሩ ። ሙሴም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ የጋድም ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ተሰልፈው ፡ በእ
፲፫ ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ተሻገሩ ። እርባ ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ጋሻና ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ለሰልፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡
፲፬ ኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ ተሻገሩ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፡ በእስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፡ ሙሴንም ፡ እንደ ፡ ፈሩ ፡ በዕድሜው ፡ ሁሉ ፡ ፈሩት ።
፲፭፡፡፲፮ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡— የምስክሩን ፡ ታቦት ፡ የሚሸከሙትን ፡ ካህናት ፡ ከዮርዳኖስ ፡
፲፯ እንዲወጡ ፡ እዘዝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። ኢያሱም ፡ ካህናትን ፡— ከዮርዳኖስ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡
፲፰ አዘዛቸው ። የእግዚአብሔርንም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ ከዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ የካህናቱም ፡ እግር ፡ ጫማ ፡ ደረቅ ፡ መሬት ፡ መርገጥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ፡ ፡
ቀድሞም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በዳሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሄደ ።
፲፱ ሕዝቡም ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ወጡ ፡ በኢያሪኮም ፡ ዳር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በጌልገላ ፡ ሰፈሩ ።
፳ ከዮርዳኖስም ፡ ውስጥ ፡ የወሰዱአቸውን ፡ እነዚያን ፡ አሥሬ ፡ ሁለቱን ፡ ድንጋዮች ፡ ኢያሱ ፡
፳፡፡፳፩ በጌልገላ ፡ አቆማቸው ። ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡— በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ልጆቻችሁ ፡ አባቶቻቸውን ፡— እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ? ብለው ፡ ሲጠ
፳፡፡፳፪ ይቁ ፡ ለልጆቻችሁ ፡ እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡ ታስታውቃላችሁ ፡— እስራኤል ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡
፳፫ በደረቅ ፡ ተሻገረ ፡ እስክንሻገር ፡ ድረስ ፡ አምላካችሁ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ከፈታችን ፡ እንዳ ፡ ደረቀ ፡ እንዲሁ ፡ እስከተሻገሩ ፡ ድረስ ፡ አምላ ፡ ካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዮርዳኖስን ፡ ውኃ ፡
፳፡፡፳፬ ከፈታችሁ ፡ አደረቀ ። ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ጠንካራ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቁ ፡ አምላካችሁንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለዘላለሙ ፡ እንድትፈሩ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፡፡፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የነበሩት ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ፡ በባሕሩም ፡ አጠገብ ፡ የነበሩ ፡ የከነዓናውያን ፡ ነገሥት ፡ ሁሉ ፡ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የዮርዳኖስን ፡ ውኃ ፡ እስኪሻገሩት ፡ ድረስ ፡ እንዳደረቀ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፡ ልባቸው ፡ ቀለጠ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ነፍስ ፡ ከዚያ ፡ ወዳያ ፡ አልቀረላቸውም ።
፡፡፪ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፡— የባልፊጩት ፡ መቀሪያ ፡ ሠርተህ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ግረዛቸው ፡ አለው ።
፡፡፫ ኢያሱም ፡ የባልፊጩት ፡ መቀሪያ ፡ ሠርቶ ፡ የግርዛት ፡ ኮረብታ ፡ በተባለ ፡ ስፍራ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ገረዘ ።
፡፡፬ ኢያሱ ፡ የገረዘበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከግብፅ ፡ የወጡት ፡ ሕዝብ ፡ ወንዶች ፡ ሰልፈኞች ፡ ሁሉ ፡ ከግብፅ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞቱ ።
፡፡፭ የወጡት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ተገርዘው ፡ ነበር ፡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከግብፅ ፡ በወጡበት ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የተወለዱት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ አልተገረዙም ፡ ነበር ።
፡፡፮ እግዚአብሔርም ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈስሰውን ፡ ምድር ፡ ለእኛ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልላቸውን ፡ ምድር ፡ እንዳያሳያቸው ፡ የማልላቸው ፡ ከግብፅ ፡ የወጡ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ያልሰሙ ፡ ፡ እነዚያ ፡ ሰልፈኞች ፡ ሁሉ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ።
፡፡፯ ልጆቻቸውን ፡ በእነርሱ ፡ ፋንታ ፡ አስነሣ ፡ እነዚህንም ፡ ኢያሱ ፡ ገረዛቸው ፡ በመንገድ ፡ ሳሉ ፡ ስላልገረዙአቸው ፡ ሸለፈታዎች ፡ ነበሩና ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ በተገረዙ ፡ ጊዜ ፡ እስኪድኑ ፡ ድረስ ፡ በሰፈር ፡ ውስጥ ፡ በየስፍራቸው ፡ ተቀመጡ ።
፡፡፰ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡— ዛሬ ፡ የግብፅን ፡ ነውር ፡ ከእናንተ ፡ ላይ ፡ አንከባልያለሁ ፡ አለው ፡ ስለዚህ ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ጌልገላ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።
፡፡፱ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በጌልገላ ፡ ሰፈሩ ፡ ከወሩም ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ ፋሲካ ፡ አደረጉ ።
፡፡፲ ከፋሲካውም ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡ የምድሪቱን ፡ ፍሬ ፡ የቂጣ ፡ እንጎቻ ፡ ቆሎም ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ በሉ ።
፡፡፲፡፡፲፩ በነጋውም ፡ ከምድሪቱ ፡ ፍሬ ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ መናው ፡ ቀረ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መና ፡ አልመጣላቸውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ ዓመት ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ ፍሬ ፡ በሉ ።
፡፡፲፡፡፲፪ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ኢያሱ ፡ በኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ ፡ ዓይኑን ፡ አንሥቶ ፡ ተመለከተ ፡ እነሆም ፡ የተመዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፡ ኢያሱም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀርቦ ፡— ከእኛ ፡ ወገን ፡ ወይስ ፡ ከጠላቶቻችን ፡

፡፡፲፡፡፲፫ ወገን ፡ ነህን ? አለው ። እርሱም ፡— አይደለሁም ፡ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ሆኜ ፡ አሁን ፡ መጥቼአለሁ ፡ አለ ። ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በግምባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰገደና ፡— ጌታዬ ፡ ለባሪያው ፡ የሚነግረው ፡ ምንድር ፡ ነው ? ፡
፡፡፲፡፡፲፬ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ኢያሱን ፡— አንተ ፡ የቆምህበት ፡ ስፍራ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፡ ጫማህን ፡ ከእግርህ ፡ አውልቅ ፡ አለው ። ኢያሱም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፡፡፩ ኢያሪኮም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ፈጽማ ፡ ተዘግታ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ የሚገባ ፡ ከእርስዋም ፡ የሚወጣ ፡ ማንም ፡ አልነበረም ።
፡፡፪ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ አለው ፡— ተመልከት ፡ ኢያሪኮንና ፡ ንጉሥዋን ፡ ጽኑዓን ፡ ኃያላንዋንም ፡ በእጅህ ፡ ሰጥቼአለሁ ።
፡፡፫ ሰልፈኞቻችሁ ፡ ሁሉ ፡ ከተማይቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዙሩአት ፡ እንዲሁም ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ አድርጉ ።
፡፡፬ ሰባትም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ይሸከሙ ፡ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ከተማይቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዙሩ ፡ ካህናቱም ፡
፡፡፭ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይንፉ ። ቀንደ ፡ መለከቱም ፡ ባለማቋረጥ ፡ ሲነፋ ፡ የመለከቱንም ፡ ድምፅ ፡ ስትሰሙ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ይጩኹ ፡ የከተማይቱም ፡ ቅጥር ፡ ይወድቃል ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ አቅንቶ ፡ ይገባባ ፡
ታል ። የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ካህናቱን ፡ ጠርቶ ፡— የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ተሸከሙ ፡ ፡ ሰባትም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ወስደው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይሂዱ ፡
፡፡፮ አላቸው ። ሕዝቡንም ፡— ሂዱ ፡ ከተማይቱንም ፡ ዙሩ ፡ ሰልፈኞችም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይሂዱ ፡ አለ ።
፡፡፯ ኢያሱም ፡ ለሕዝቡ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሰባቱ ፡ ካህናት ፡ ሰባቱን ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሄዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱንም ፡ ነፉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ይከተላቸው ፡ ነበር ።
፡፡፰ ሰልፈኞቹም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ በሚነፉ ፡ በካህናቱ ፡ ፊት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፡ የቀረውም ፡ ሕዝብ ፡ ከታቦቱ ፡ በኋላ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ ካህናቱም ፡ እየሄዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ።
፡፡፱ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፡— እኔ ፡— ጩኹ ፡ እስከምልበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አትጩኹ ፡ ድምፃችሁንም ፡ አታንሡ ፡ ከአፋችሁም ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አይውጣ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትጮኻላችሁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። እንዲሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተማይቱን ፡ አዞረው ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ተመልሰው ፡ አደሩ ።
፡፡፲ ኢያሱም ፡ ማለዳ ፡ ተነሣ ፡ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ተሸከሙ ። ሰባቱም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፡ ቀንደ ፡ መለከቱንም ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፡ ሰልፈኞቹም ፡ በፊታቸው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፡ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በኋላ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፡ ካህናቱም ፡ እየሄዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ።
፡፡፲፡፡፲፩ በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ ከተማይቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዞረው ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ተመለሱ ፡ ስድስት ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ።
፡፡፲፡፡፲፪ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፡ እንደዚህም ፡ ሥርዓት ፡ ከተማይቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዞሩ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ከተማይቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዞሩ ።
፡፡፲፡፡፲፣ በሰባተኛውም ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ሲነፉ ፡ ኢያሱ ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፡— እግዚአብሔር ፡ ከተማይቱን ፡ ሰጥቶአችኋልና ፡ ጩኹ ።
፡፡፲፡፡፲፤ ከተማይቱም ፡ በእርስዋም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እርም ፡ ይሆናሉ ፡ የላከናቸውን ፡ መልከተኞች ፡ ስለ ፡ ሸሸገች ፡ ጋለሞታይቱ ፡ ረዓብ ፡ ከእርስዋም ፡ ጋር ፡ በቤትዋ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ብቻ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ። እናንተ ፡ ግን ፡
፡፡፲፡፡፲፣ እርም ፡ ከደረጋችሁት ፡ በኋላ ፡ እርም ፡ ከሆነው ፡ ነገር ፡ ራሳችሁን ፡ ጠብቁ ፡ እርም ፡ ከሆነው ፡ አንዳች ፡ የወሰዳችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእስራኤልን ፡ ሰፈር ፡ የተረገመ ፡ ታደርጉታላችሁ ፡ ፡
ታስጨንቁትማላችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ብርና ፡
፡፡፲፡፡፲፣ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ የናስና ፡ የብረትም ፡ ዕቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይሁን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይግባ ።
፡፡፲፡፡፲፡ ሕዝቡም ፡ ጮኹ ፡ ካህናቱም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ነፉ ፡ ሕዝቡም ፡ የቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ጩኹት ፡ ጮኹ ፡ ቅጥሩም ፡ ወደቀ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ አቅንቶ ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ወጣ ፡ ከተማይቱንም ፡ ወሰዱ ።
፡፡፲፡፡፲፡ በከተማይቱም ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ ሕፃኑንና ፡ ሽማግሌውን ፡ በሬውንም ፡ በጉንም ፡ አህያውንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ፈጽመው ፡ አጠፉ ።
፡፡፲፡፡፲፡ ኢያሱም ፡ ምድሪቱን ፡ የሰለሉ ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡— ወደ ፡ ጋለሞታይቱ ፡ ቤት ፡ ግቡ ፡ ከዚያም ፡ ሴቲቱንና ፡ ያላትን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ማላ ፡
ሁላት ፡ አውጡ ፡ አላቸው ።
፡፡፲፡፡፲፡ ሰላዮቹም ፡ ብላ ፡ ቴናዎች ፡ ገብተው ፡ ረዓብን ፡ አባትዋንና ፡ እናትዋን ፡ ወንድሞችዋንም ፡ ያላትንም ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶችዋንም ፡ ሁሉ ፡ አወጡ ፡ ከእስራኤልም ፡ ሰፈር ፡ በውጭ ፡ አስቀመጡአቸው ።
ከተማይቱንም ፡ በእርስዋም ፡ የነበረውን ፡
፡፡፲፡፡፲፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ የናሱንና ፡ የብረቱንም ፡ ዕቃ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አደረጉት ።
፡፡፲፡፡፲፡ ኢያሪኮን ፡ ሊሰልሉ ፡ ኢያሱ ፡ የሰደዳቸውንም ፡ መልከተኞች ፡ ስለ ፡ ሸሸገች ፡ ጋለሞታይቱን ፡ ረዓብን ፡ የአባትዋንም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ያላትንም ፡ ሁሉ ፡ ኢያሱ ፡ አዳናቸው ፡ እርስዋም ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተቀምጣለች ።
፡፡፲፡፡፲፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡— ይህችን ፡ ከተማ ፡

ኢያሪኮን ፡ ለመሥራት ፡ የሚነሣ ፡ ሰው ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፤ መሠረት
ዋን ፡ ሲጥምር ፡ በሙር ፡ ልጁ ፡ ይጥፋ ÷ በርዋ
ንም ፡ ሲያቆም ፡ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ይጥፋ ፡ ብሎ ፡
ማለ ። ፴፯ እግዚአብሔርም ፡ ከኢያሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፤
ዝናውም ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ እርም ፡ በሆነው ፡
ነገር ፡ በደሉ ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የሆነ ፡ አካን ÷
እርሱም ፡ የከርሚ ፡ ልጅ ÷ የዘንበሪ ፡ ልጅ ÷
የዛራ ፡ ልጅ ÷ እርም ፡ ከሆነው ፡ ነገር ፡ ወሰደ ፤
የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ላይ ፡ ነደደ ።
፪ ኢያሱም ፡ ከቤቴል ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡
በቤትአዌን ፡ አጠገብ ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡
ሰዎችን ፡ ከኢያሪኮ ፡ ልከ ፥ — ውጡ ፡ ምድሪቱ
ንም ፡ ሰልሉ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፤ ሰዎቹም ፡
ወጡ ÷ ጋይንም ፡ ሰለሉ ። ፫ ወደ ፡ ኢያሱም ፡
ተመልሰው ፥ — ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡
ያህል ፡ ሰው ፡ ወጥተው ፡ ጋይን ፡ ይምቱ ፡
እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አይውጣ ፡ ጥቂቶች ፡
ናቸውና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ወደዚያ ፡ ለመሄድ ፡
አይድከም ፡ አሉት ። ፴ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሰዎ
ችም ፡ ወደዚያ ፡ ወጡ ፡ ከጋይም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡
ሸሹ ። ፭ የጋይም ፡ ሰዎች ፡ ከእነርሱ ፡ ሠላሳ ፡ ስድ
ስት ፡ ያህል ፡ ሰዎችን ፡ መቱ ፤ ከበሩ ፡ እስከ ፡
ሽባረም ፡ ድረስ ፡ አባረሩአቸው ፡ በቍልቍለ
ቱም ፡ መቱአቸው ፡ የሕዝቡም ፡ ልብ ፡ ቀለጠ ÷
እንደ ፡ ውኃም ፡ ሆነ ።
፮ ኢያሱም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ÷ እርሱና ፡ የአ
ስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡
ታቦት ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በግምባራ
ቸው ፡ ተደፉ ፡ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡
፯ ነሰነሱ ። ኢያሱም ፡ አለ ፥ — ዋይ ! ጌታ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሆይ ÷ በእሞራውያን ፡ እጅ ፡ አሳ
ልፈህ ፡ ትሰጠን ፡ ታጠፋንም ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡
ሕዝብ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ለምን ፡ አሻገርኸው ? በዮ
ርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ መቀመጥን ፡ በወደድን ፡ ነበር ፡
እኮ ! ጌታ ፡ ሆይ ÷ እስራኤል ፡ በጠላቶቻቸው ፡
፱ ፊት ፡ ከሸሹ ፡ ምን ፡ እላለሁ ? ከነዓናውያንም ፡
በምድሪቱም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰምተው ፡ ይከ
ብቡናል ÷ ስማችንንም ፡ ከምድር ፡ ያጠፋሉ ፤
ለታላቁ ፡ ስምህም ፡ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡
ነው ?
፱ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ አለው ፥ — ለምን ፡
በምንባርህ ፡ ተደፍተሃል ? ቁም ! እስራኤል ፡
፲፩ በድሉአል ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡
አፍርሰዋል ፤ እርም ፡ የሆነውንም ፡ ነገር ፡ ወሰዱ ÷
ሰረቁም ÷ ዋሹም ÷ በዕቃቸውም ፡ ውስጥ ፡ ሸሸ
፲፪ ጉት ። ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጠ
ላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይችሉም ፤ የተ
ረገሙ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ይሸ
ሻሉ ፤ እርም ፡ የሆነውንም ፡ ነገር ፡ ከመካከላ
ችሁ ፡ ካላጠፋችሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክእናንተ ፡
ጋር ፡ አልሆንም ። ተነሣና ፡ ሕዝቡን ፡ ቀድስ ÷ ፲፫
እንዲህም ፡ በላቸው ፥ — እስራኤል ፡ ሆይ ÷
እርም ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በመካከልህ ፡ አለ ፡ እር
ም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ከመካከላችሁ ፡ እስከ
ታጠፋ ፡ ድረስ ፡ በጠላቶቻችሁ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡
አትችሉም ፡ ብሎ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ተናግሮአልና ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ተቀደሱ ።
ነገም ፡ በየነገዳችሁ ፡ ትቀርባላችሁ ፤ እግዚአ ፲፬
ብሔርም ፡ የሚለየው ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቹ ፡ ይቀ
ርባል ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚለየው ፡ ወገን ፡
በየቤተ ፡ ሰበቦ ፡ ይቀርባል ፤ እግዚአብሔርም ፡
የሚለየው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በየሰዉ ፡ ይቀርባል ።
እርም ፡ የሆነውም ፡ ነገር ፡ የተገኘበት ፡ ሰው ፡ ፲፭
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሶአልና ÷
በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ በደል ፡ አድርጎአልና ፡
እርሱና ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ።
፲፮ ኢያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ÷ እስራኤልንም ፡
በየነገዶቻቸው ፡ አቀረበ ፤ የይሁዳም ፡ ነገድ ፡
ተለየ ፤ የይሁዳንም ፡ ወገን ፡ አቀረበ ፡ የዛራ
ንም ፡ ወገን ፡ ለየ ፤ የዛራንም ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡
አቀረበ ፡ ዘንበሪም ፡ ተለየ ፤ የቤቱንም ፡ ሰዎች ፡ ፲፯
አቀረበ ፤ ከይሁዳም ፡ ነገድ ፡ የሆነ ፡ የከርሚ ፡
ልጅ ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ አካን ፡
ተለየ ። ኢያሱም ፡ አካንን ፥ — ልጄ ፡ ሆይ ÷ ፲፰
ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡
ስጥ ÷ ለእርሱም ፡ ተናዘዝ ፤ ያደረግኸውንም ፡
ንገረኝ ፤ አትሸሽገኝ ፡ አለው ። አካንም ፡ መልሶ ፡ ፲፱
ኢያሱን ፥ — በእውነት ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔርን ፡ በድያለሁ ፡ እንዲህና ፡ እንዲ
ህም ፡ አድርጌአለሁ ። በዘረፋ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ፳
ያማረ ፡ የሰናዖር ፡ ካባ ÷ ሁለት ፡ መቶም ፡ ሰቅል ፡
ብር ÷ ሚዛኑም ፡ አምሳ ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ ወርቅ ፡
አይቼ ፡ ተመኘኋቸው ÷ ወሰድኋቸውም ፤ እነ
ሆም ÷ በድንኳኔ ፡ ውስጥ ፡ በመሬት ፡ ተሸሽገ
ዋል ÷ ብሩም ፡ ከሁሉ ፡ በታች ፡ ነው ፡ አለው ።
፳፩ ኢያሱም ፡ መልክተኞች ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ድን
ኳኑም ፡ ሮጡ ፤ እነሆም ÷ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ተሸ
ሽጎ ፡ ነበር ÷ ብሩም ፡ በበታቹ ፡ ነበረ ። ከድን ፳፪
ኳኑም ፡ ውስጥ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ኢያሱና ፡ ወደ ፡
እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አመጡት ! በእግ
ዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ አኖሩት ። ኢያሱና ፡ እስ ፳፫
ራኤል ፡ ሁሉ ፡ የዛራን ፡ ልጅ ፡ አካንን ÷ ብሩ
ንም ÷ ካባውንም ÷ ወርቁንም ÷ ወንዶችና ፡
ሴቶች ፡ ልጆቹንም ÷ በሬዎቹንም ÷ አህያዎቹ
ንም ÷ በጎቹንም ÷ ድንኳኑንም ÷ ያለውንም ፡
ሁሉ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ አኮር ፡ ሸለቆ ፡ አመጡ
አቸው ። ኢያሱም ፥ — ለምን ፡ አስጨነቅኸን ? ፳፬
እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ያስጨንቅሃል ፡ አለው ፤
እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ፤ በእ
ሳትም ፡ አቃጠሉአቸው ÷ በድንጋይም ፡ ወገሩ
አቸው ። በላዩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡ ፳፭
ታላቅ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ከመሩ ፤ እግዚአብ
ሔርም ፡ ከቍጣው ፡ ትኵሳት ፡ ተመለሰ ። ስለ

ዚህም ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ድረስ ፡ የአኮር ፡ ሸለቆ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፥ — አትፍራ ÷
አትደንግጥ ፤ ሰልፈኞችን ፡ ሁሉ ፡ ከእንተ ፡
ጋር ፡ ውሰድ ÷ ተነሥተህም ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡
ውጣ ፤ እይ ÷ የጋይን ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቡንም ፡
ከተማውንም ፡ ምድሩንም ፡ በእጅህ ፡ ሰጥቼሃ
ለሁ ። በእያሪኮና ፡ በንጉሥዋም ፡ እንዳደረ
ግህ ፡ እንዲሁ ፡ በጋይና ፡ በንጉሥዋ ፡ ታደርጋ
ለህ ፤ ምርኮዋንና ፡ ከብትዋን ፡ ግን ፡ ለራሳችሁ ፡
ትዘርፋላችሁ ፤ ከከተማይቱም ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡
ድብቅ ፡ ጦር ፡ አስቀምጥ ፡ አለው ።
፪ ኢያሱም ፡ ሰልፈኞቹም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡
ሊወጡ ፡ ተነሡ ፤ ኢያሱም ፡ ጽኑዓን ፡ ኃያላን ፡
የሆኑትን ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ መረጠ ፡ በሌ
ሊትም ፡ ሰደዳቸው ። እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዘ
ቸው ፥ — እነሆ ÷ ከከተማይቱ ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡
ተደበቁ ፤ ከከተማይቱ ፡ አትራቁ ÷ ሁላችሁም ፡
ተዘጋጁ ፤ እኔ ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ እንቀርባለን ፤ እኛንም ፡
ሊገናኙ ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ከፊታ
ቸው ፡ እንሸሻለን ፤ እስቀድመን ፡ እንደ ፡ ሸሽን ፡
የምንሸሽ ፡ ይመስላቸዋልና ፡ ከከተማይቱ ፡ እስ
እኛም ፡ ከፊታቸው ፡ እንሸሻለን ። እናንተም ፡
ከተደበቃችሁበት ፡ ስፍራ ፡ ተነሡ ፡ አምላካች
ሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ እርስዋን ፡ በእጃችሁ ፡
ሰጣልር ፡ ይሰጣልና ፡ ከተማይቱን ፡ ያዙ ። በያ
ዝችኋትም ፡ ጊዜ ፡ ከተማይቱን ፡ በእሳት ፡ አቃ
ጥሉአት ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አድ
ርጉ ፤ እነሆ ÷ አዝዣችኋለሁ ። ኢያሱም ፡ ሰደ
ዳቸው ፤ ወደሚደበቁበትም ፡ ስፍራ ፡ ሄዱ ÷
በጋይና ፡ በቤቴል ፡ መካከልም ፡ በጋይ ፡ በምዕ
ራብ ፡ በኩል ፡ ተቀመጡ ፡ ኢያሱ ፡ ግን ፡ በዚ
ያች ፡ ሌሊት ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አደረ ።
፭ ኢያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ÷ ሕዝቡንም ፡ አሰ
ለፈ ፤ እርሱም ፡ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡
ከሕዝቡ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ወጡ ። ከእር
ሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሰልፈኞች ፡ ሁሉ ፡ ወጥ
ተው ፡ ቀረቡ ÷ ወደ ፡ ከተማይቱም ፡ ፊት ፡
ደረሱ ÷ በጋይም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ሰፈሩ ፤
ስእነርሱና ፡ በጋይም ፡ መካከል ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ።
፮ አምስት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሰዎችንም ፡ ወስዶ ፡
ስቤቴልና ፡ በጋይ ፡ መካከል ፡ በከተማይቱም ፡
ስምዕራብ ፡ በኩል ፡ ደብቆ ፡ አስቀመጣቸው ።
በከተማይቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ የነበሩትን ፡
ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ በከተማይቱም ፡ በምዕራብ ፡
በኩል ፡ የተደበቁትን ፡ ሕዝብ ፡ አኖሩ ፡ ኢያ
ሱም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ሸለቆው ፡ መካ
ከል ፡ ሄደ ። ፯ የጋይም ፡ ንጉሥ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
የከተማይቱ ፡ ሰዎች ፡ ቸኰሉው ፡ በማለዳ ፡
ተነሡ ፤ እርሱና ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በተወሰነው ፡
ጊዜ ፡ በዓረባ ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡
ስፍራ ፡ እስራኤልን ፡ በሰልፍ ፡ ለመገናኘት ፡
ወጡ ፤ ከከተማይቱ ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ድብቅ ፡
ጦር ፡ እንዳለ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ፰ ኢያሱም ፡ ፲፭
እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ የተነሡ ፡ መስለው ፡
ከፊታቸው ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ መንገድ ፡ ሸሹ ።
በከተማይቱም ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሊያሳ ፡ ፲፮
ድዱአቸው ፡ ተጠሩ ፤ ኢያሱንም ፡ አሳደዱት ÷
ከከተማይቱም ፡ እንዲርቁ ፡ አደረጓቸው ። በጋ ፲፯
ይና ፡ በቤቴልም ፡ ውስጥ ፡ እስራኤልን ፡ ለማሳ
ደድ ፡ ያልወጣ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ከተማይቱ
ንም ፡ ከፍተው ፡ ተዉ ÷ እስራኤልንም ፡ አሳደ
ዱት ።
፲፰ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፥ — ጋይን ፡ በእጅህ ፡ ፲፱
አሳልፌ ፡ እሰጥሃለሁና ፡ በእጅህ ፡ ያለውን ፡
ጦር ፡ በላይዋ ፡ ዘርጋ ፡ አለው ፤ ኢያሱም ፡
በእጁ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ በከተማይቱ ፡ ላይ ፡
ዘረጋ ። ፲፱ የተደበቁትም ፡ ፈጥነው ፡ ከስፍራቸው ፡
ተነሡ ÷ ኢያሱም ፡ እጁን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፡ ሮጡ ÷
ወደ ፡ ከተማይቱም ፡ ገብተው ፡ ያዙአት ፤ ፈጥነ
ውም ፡ ከተማይቱን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉአት ።
፳ የጋይም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ዘረው ፡ የከ ፳
ተማይቱ ፡ ጢስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ አዩ ÷
ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ መሸሽ ፡ አልቻሉም ፤ ወደ ፡
ምድረ ፡ በዳም ፡ የሸሹ ፡ ሕዝብ ፡ በሚያሳድዱ ፡
አቸው ፡ ላይ ፡ ተመለሱ ። ኢያሱም ፡ እስራ ፳፩
ኤልም ፡ ሁሉ ፡ ተደብቀው ፡ የነበሩት ፡ ከተማ
ይቱን ፡ እንደ ፡ ያዙ ÷ የከተማይቱም ፡ ጢስ ፡
እንደ ፡ ተነሣ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመል
ሰው ፡ የጋይን ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ። ሌሎቹም ፡ በላ ፳፪
ያቸው ፡ ከከተማይቱ ፡ ወጡ ፡ የጋይም ፡ ሰዎች ፡
በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ሆኑ ÷ እስራኤልም ፡ ከበ
ቡአቸው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ሳያመልጥም ፡
ገደሉአቸው ። ፳፫ የጋይንም ፡ ንጉሥ ፡ ሰይሞት ፡ ፳፫
ይዘው ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ አመጡት ።
፳፬ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ እስራኤልን ፡ ሊያሳድዱ ፡
ሄደው ፡ የነበሩትን ፡ የጋይን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በሜዳና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ከገደሉአቸው ፡
በኋላ ÷ እነርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ እስኪያ
ልቁ ፡ ድረስ ፡ ከወደቁ ፡ በኋላ ÷ እስራኤል ፡
ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ተመለሱ ÷ በሰይፍም ፡ ስለት ፡
መቱአት ። ፳፭ በዚያም ፡ ቀን ፡ የወደቁት ፡ ሁሉ ፡ ፳፭
ወንድም ፡ ሴትም ፡ የጋይ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ሺህ ፡ ነፍስ ፡ ነበሩ ። ፳፮ ኢያሱም ፡ በጋይ ፡ ፳፮
የሚኖሩትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያጠፋ ፡
ድረስ ፡ ጦር ፡ የዘረጋበትን ፡ እጁን ፡ አላጠፈም ። ፳፯
ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፡ እንዳዘ
ዘው ፡ ቃል ፡ የዚያችን ፡ ከተማ ፡ ከብትና ፡
ምርኮ ፡ እስራኤል ፡ ለራሳቸው ፡ ዘረፉ ። ፳፰ ኢያ ፳፰
ሱም ፡ ጋይን ፡ አቃጠላት ÷ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡
ድብደባና ፡ በረሃ ፡ ለዘላለም ፡ አደረጋት ። ፳፱ የጋ ፳፱
ይንም ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በዛፍ ፡
ላይ ፡ ሰቀለው ፤ ፀሐይም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡
አዘዘ ÷ ሬሳውንም ፡ ከዛፍ ፡ አወረዱት ÷ በከተ

ማይቱም ፡ በር ፡ እደባባይ ፡ ጣሉት ÷ በላዩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፡ የድን ጋይ ፡ ከምር ፡ ከመሩበት ።

፴፩ ፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
፴፪ ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዳዘዘ ÷ በሙ ሴም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ÷ መሠዊ ያው ፡ ከልተወቀረና ፡ ብረት ፡ ካልነከው ፡ ድን ጋይ ፡ ነበረ ፡ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ÷ የደኅ
፴፫ ፡ ንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሲያዩ ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ በድንጋዮቹ ፡
፴፫ ፡ ላይ ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ ጻፈባቸው ። የእስራኤ ልንም ፡ ሕዝብ ፡ አስቀድሞ ፡ ይባርኩ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘ ÷ እስ ራኤል ፡ ሁሉ ÷ ሽማግሌዎቻቸውም ÷ አለቆቻቸ ውም ÷ ፈራጆቻቸውም ÷ የእነሩ ፡ ልጆችም ÷ መጻተኞችም ÷ እኩሌቶቹ ፡ በገሪዛን ፡ ተራራ ፡ ፊት ፡ እኩሌቶቹም ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ፊት ፡ ሆነው ÷ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በተሸከሙት ፡ በሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ፊት ፡ ለፊት ÷ በታቦቱም ፡ ፊት ፡ በወዲህና ፡
፴፬ ፡ በወዲያ ፡ ቆመው ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሁሉ ÷ የሕ ጉን ፡ ቃሉት ፡ ሁሉ ፡ በረከቱንና ፡ እርግማኑን ፡
፴፭ ፡ አነበበ ። ኢያሱም ፡ በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ በሴቶቹም ፡ በሕፃናቱም ፡ በመከከላቸ ውም ፡ በሚኖሩት ፡ መጻተኞች ፡ ፊት ፡ ሁሉን ፡ አነበበ ፡ እንጂ ፡ ሙሴ ፡ ከዘዘው ፡ እንዲት ፡ ቃል ፡ አላስቀረም ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በተራራ ማው ፡ በቄላውም ፡ በታላቁ ፡ በሕር ፡ ዳር ፡ በሊ ባናስም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የነበሩ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ÷ ኬጢያዊ ፡ አሞራዊም ፡ ከነዓናዊም ፡ ፈርዛዊም ፡ ኤዊያዊም ፡ ኢያቡሳዊም ÷ ይህን ፡
፪ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ÷ ኢያሱንና ፡ እስራኤልን ፡ ሊወጉ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ተሰበሰቡ ።

፫ ፡ የገባዖን ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ኢያሱ ፡ በኢያሪኮና ፡
፬ ፡ በጋይ ፡ ያደረገውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ÷ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ተንኰል ፡ አደረጉ ፡ ለራሳቸውም ፡ ስንቅ ፡ ያዙ ÷ በአህዮቻቸውም ፡ ላይ ፡ አሮጌ ፡ ዓይበትና ፡ ያረጀና ፡ የተቀደደ ፡ የተጠቀመም ፡
፭ ፡ የጠጅ ፡ አቁማዳ ፡ ጫኑ ። ያረጀ ፡ የተጠቀመም ፡ ጫማ ፡ በእግራቸው ፡ አደረጉ ፡ አሮጌም ፡ ልብስ ፡ ለበሱ ፡ ለስንቅም ፡ የያዙት ፡ እንጀራ ፡ ሁሉ ፡
፮ ፡ የደረቀና ፡ የሻገተ ፡ ነበረ ። ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ሄደው ፡ ለእርሱና ፡ ለእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ — ከሩቅ ፡ አገር ፡ መጥተ ናል ፡ አሁንም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ኪዳን ፡ አድርጉ ፡
፯ ፡ አሉ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኤዊያውያ ንን ፡ — ምናልባት ፡ በመካከላችን ፡ የምትቀ መጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዴትስ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እናደርጋለን ? አሉአቸው ። ኢያሱ ፡ ፰ ፡
ንም ፡ — እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ነን ፡ አሉት ። ኢያ ሱም ፡ — እናንተ ፡ እነማን ፡ ናችሁ ? ከወዴትስ ፡ መጣችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፡ አሉት ፡ — ከአ ፱ ፡ ምላክህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ከራቀ ፡ አገር ፡ ባሪያዎችህ ፡ መጥተናል ፡ ዝናውንም ÷ በግብፅም ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ÷ በዮርዳኖስ ፡ ማዶም ፡ በነበሩት ፡ በሁለቱ ፡ በአ ፱ ፡ ሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ በሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ በአስታሮትም ፡ በነበረው ፡ በባሳን ፡ ንጉሥ ፡ በዐግ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ሰምተናል ። ሽማግሌዎቻችንም ፡ በምድራችንም ፡ የሚኖ ፡ ፲ ፡ ሩት ፡ ሁሉ ፡ — ለመንገድ ፡ ስንቅ ፡ በእጃችሁ ፡ ያዙ ÷ ልትገናኙአቸውም ፡ ሂዱ ፡ — እኛ ፡ ባሪያ ዎቻችሁ ፡ ነን ፤ አሁንም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጉ ፡ በሉአቸው ፡ አሉን ። ወደ ፡ ፲ ፡ እናንተ ፡ ለመምጣት ፡ በተነሣንበት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ እንጀራ ፡ ትኩሱን ፡ ለስንቅ ፡ በእጃችሁ ፡ ወሰድነው ፡ አሁንም ፡ እነሆ ÷ ደርቆአል ÷ ሻግ ቶአልም ። እነዚህም ፡ የጠጅ ፡ አቁማዳዎች ፡ ፲ ፡ አዲስ ፡ ሳሉ ፡ ሞላንባቸው ፤ እነሆም ÷ ተቀድደ ዋል ፤ መንገዳችንም ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ራቀብን ፡ እነዚህ ፡ ልብሶቻችንና ፡ ጫማዎቻችን ፡ አርጅ ተዋል ። ሰዎቹም ፡ ከስንቃቸው ፡ ወሰዱ ÷ እግ ፲ ፡ ዚአብሔርንም ፡ አልጠየቁም ። ኢያሱም ፡ ከእነ ፲ ፡ ርሱ ፡ ጋር ፡ ሰላም ፡ አደረገ ÷ በሕይወት ፡ አንዲ ተዋቸውም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደ ረገ ፤ የማኅበሩም ፡ አለቆች ፡ ማሉላቸው ።

ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከደረጉ ፡ ከሦ ስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጎረቤቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ፲ ፡ በመከከላቸውም ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡ ሰሙ ። የእስራ ፲ ፡ ኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጉዘው ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ከተሞቻቸው ፡ መጡ ፤ የከተሞቻቸውም ፡ ስም ፡ ገባዖን ÷ ከፊራ ÷ ብኤሮት ÷ ቂርያትይዓሪም ፡ ነበረ ። የሕዝቡም ፡ አለቆች ፡ በእስራኤል ፡ ፲ ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ማሉላቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አልመቱአቸውም ። ማኅበ ራም ፡ ሁሉ ፡ በአለቆቹ ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ። አለ ፲ ፡ ቆቹም ፡ ሁሉ ፡ ለማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ — በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለንላቸዋል ፡ ስለ ዚህም ፡ እንነካቸው ፡ ዘንድ ፡ አይገባንም ። ስለ ፡ ማልንላቸው ፡ መሐላ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይወር ፡ ፲ ፡ ድብን ፡ ይህን ፡ እናድርግባቸው ÷ በሕይወትም ፡ እንተዋቸው ፡ አሉአቸው ። አለቆቹም ፡ — በሕ ፲ ፡ ይወት ፡ ይኑሩ ፡ አሉአቸው ፤ አለቆቹም ፡ እንደ ፡ ተናገሩአቸው ፡ ለማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ እንጨት ፡ ቆራጮች ፡ ውኃም ፡ ቀዂዎች ፡ ሆኑ ።

ኢያሱም ፡ ጠርቶ ፡ — እናንተ ፡ በመካከላችን ፡ ፲ ፡ ስትኖሩ ፡ — ከእናንተ ፡ እጅግ ፡ የራቅን ፡ ነን ፡ ብላችሁ ፡ ለምን ፡ አታለላችሁን ? አሁንም ፡ የተ ፲ ፡ ረገማችሁ ፡ ናችሁ ፡ ለአምላኬም ፡ ቤት ፡ እን ጨት ፡ ቈራጭ ፡ ውኃም ፡ ቀዂ ፡ የሆነ ፡ ባሪያ ፡ ከእናንተ ፡ ለዘላለም ፡ አይጠፋም ፡ አላቸው ።

፲፩ ፡ መልሰውም ፡ ኢያሱን ፡ — እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ምድሪቱን ፡ ሁሉ ፡ ይሰማችሁ ፡ ዘንድ ÷ በእርስ ዋም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሁሉ ፡ ከፊታችሁ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሪያውን ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ በእውነት ፡ ሰምተናል ÷ ስለዚህም ፡ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ነፍሳችን ፡ እጅግ ፡ ፈራን ÷ ይህንንም ፡ ነገር ፡ አድርገናል ። ፲፪ ፡ አሁንም ÷ እነሆ ÷ በእጅህ ፡ ውስጥ ፡ ነን ፤ ለዓይ ንህም ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ የመሰለውን ፡ ነገር ፡ ፲፫ ፡ አድርግብን ፡ አሉት ። እንዲሁም ፡ አደረገባ ቸው ÷ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አዳና ቸው ÷ አልገደሉአቸውምም ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ ለማኅበሩ ፡ በመረጠውም ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ እንጨት ፡ ቈራጮች ፡ ውኃም ፡ ቀዂዎች ፡ አደ ረጋቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ አዶ ኒጼዲቅ ፡ ኢያሱ ፡ ጋይን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ፈጽ ሞም ፡ እንዳጠፋት ÷ በእያሪኮና ፡ በንጉሥ ዋም ፡ ያደረገውን ፡ እንዲሁ ፡ በጋይና ፡ በንጉ ሥዋ ፡ እንዳደረገ ÷ የገባዖንም ፡ ሰዎች ፡ ከእስ ራኤል ፡ ጋር ፡ ሰላም ፡ እንዳደረጉ ፡ በመካከላ ቸውም ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ÷ ገባዖን ፡ ከመ ንግሥታት ፡ ከተሞች ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ሆነች ÷ ከጋይም ፡ ስለ ፡ በለጠች ÷ ሰዎችዋም ፡ ሁሉ ፡ ኃያላን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ÷ እጅግ ፡ ፈራ ። ስለዚህም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ አዶኒጼዲቅ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሆሃም ÷ ወደ ፡ የርሙት ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ጲርአም ÷ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ያፌዓ ÷ ወደ ፡ አዖላም ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ዳቤር ፡ ልኩ ፡ — ወደ ፡ እኔ ፡ ውጡ ÷ ከኢያሱና ፡ ከእ ስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሰላም ፡ አድርገዋ ልና ፡ ገባዖንን ፡ ለመምታት ፡ እግዜኝ ፡ አለ ። ፴ ፡ አምስቱም ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ÷ የኢየሩ ሳሌም ፡ ንጉሥ ÷ የኬብሮን ፡ ንጉሥ ÷ የየርሙት ፡ ንጉሥ ÷ የለኪሶ ፡ ንጉሥ ÷ የአዖላም ፡ ንጉሥ ÷ ከሠራዊቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ተሰብስበው ፡ ወጡ ÷ ከገባዖንም ፡ ጋር ፡ ሊጋጠሙ ፡ ከበቡአት ።

የገባዖንም ፡ ሰዎች ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ፴ ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ልከው ፡ — ባሪያዎችህን ፡ ለመ ርዳት ፡ እጅህን ፡ አትመልስ ፤ በተራራማው ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበውብናልና ፡ ፈጥነህ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ውጣ ፡ አድነንም ፡ እርዳንም ፡ አሉት ። ኢያ ሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሰልፈኞች ፡ ሁሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ኃያላኑም ፡ ሁሉ ፡ ከጌልገላ ፡ ወጡ ። ፴ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ — በእጅህ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቼአቸዋለሁና ፡ አትፍራቸው ፡ ከእነ ርሱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚቋቋምህ ፡ የለም ፡ አለው ። ኢያሱም ፡ ከጌልገላ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ገሥግሦ ፡ በድንገት ፡ መጣባቸው ። ፴ ፡ እግዚአብሔ ርም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ አስደነገጣቸው ፤ በገባዖ ንም ፡ ታላቅ ፡ መምታት ፡ መታቸው ÷ በቤትሖሮ ንም ፡ በቀበት ፡ በመንገድ ፡ አሳደዳቸው ÷ እስከ ፡ ዓዜቃና ፡ እስከ ፡ መቄዳ ፡ ድረስ ፡ መታቸው ። ፴ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እየሸሹ ፡ በቤት ፡ ሖሮን ፡ ቍልቍለት ፡ ሲወርዱ ÷ ወደ ፡ ዓዜቃ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ታላላቅ ፡ የበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ አወረደባቸውና ፡ ሞቱ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሰይፍ ፡ ከገደሉ ፡ አቸው ፡ ይልቅ ፡ በበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ የሞቱት ፡ በለጡ ።

፴ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፲፪ ፡ እጅ ፡ አሞራውያንን ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠ ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተናገረ ፤ በእስራኤ ልም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — በገባዖን ፡ ላይ ፡ ፀሐይ ፡ ትቁም ÷ በኤሎንም ፡ ሸለቆ ፡ ጨረቃ ፤ ሕዝቡም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ እስኪበቀሉ ፡ ድረስ ፡ ፲፫ ፡ ፀሐይ ፡ ቆመ ÷ ጨረቃም ፡ ዘገየ ። ይህስ ፡ በያ ሻር ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ? ፀሐ ይም ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ ዘገየ ፤ እንድ ፡ ቀንም ፡ ሙሉ ፡ ያህል ፡ ለመግባት ፡ አልቸኰለም ። እግ ፲፬ ፡ ዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ይዋጋ ፡ ነበርና ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሰውን ፡ ቃል ፡ የሰማበት ፡ እንደ ዚያ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አልነበረም ።

ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ፲፭ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ወደ ፡ ጌልገላ ፡ ተመለሱ ።

እነዚህም ፡ አምስት ፡ ነገሥታት ፡ ሸሽተው ፡ ፲፮ ፡ በመቄዳ ፡ ዋሻ ፡ ተሸሽገ ። ለኢያሱም ፡ — አም ፲፯ ፡ ስቱ ፡ ነገሥታት ፡ በመቄዳ ፡ ዋሻ ፡ ተሸሽገው ፡ ተገኙ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ኢያሱም ፡ እንዲህ ፡ ፲፰ ፡ አለ ፡ — ወደ ፡ ዋሻው ፡ አፍ ፡ ታላላቅ ፡ ድንጋይ ፡ አንከባልላችሁ ÷ ይጠብቁአቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰዎ ችን ፡ በዚያ ፡ አኑሩ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ አትዘግዩ ÷ ፲፱ ፡ ጠላቶቻችሁንም ፡ አባርሩአቸው ÷ በኋላም ፡ ያሉ ትን ፡ ግደሉ ፤ አምላካችሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጃችሁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአቸዋልና ፡ ወደ ፡ ከተሞቻቸው ፡ እንዳያገቡ ፡ ከልከሉአቸው ፡ አለ ። እስኪጠፉም ፡ ድረስ ፡ ኢያሱና ፡ የእስራ ፲ ፡ ኤል ፡ ልጆች ፡ በታላቅ ፡ መምታት ፡ መምታታ ቸውን ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ÷ ከእነርሱም ፡ ያመለ ጡት ፡ ወደ ፡ ተመሸገ ፡ ከተማ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ÷ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ወደ ፲፪ ፡ መቄዳ ፡ በደኅና ፡ ተመለሱ ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ምላሱን ፡ ማንቀሳቀስ ፡ የደፈረ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የለም ።

ኢያሱም ፡ — የዋሻውን ፡ አፍ ፡ ከፈቱ ÷ እነዚ ፲፭ ፡ ያንም ፡ አምስት ፡ ነገሥታት ፡ ከዋሻው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አውጡአቸው ፡ አለ ። እንዲህም ፡ አደ ፲፮ ፡ ረጉ ፤ አምስቱንም ፡ ነገሥታት ÷ የኢየሩሳሌ ምን ፡ ንጉሥ ፡ የኬብሮንንም ፡ ንጉሥ ፡ የየርሙ ትንም ፡ ንጉሥ ፡ የለኪሶንም ፡ ንጉሥ ፡ የአዖላ ምንም ፡ ንጉሥ ÷ ከዋሻው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አወ ጡአቸው ። እነዚያንም ፡ ነገሥታት ፡ ወደ ፲፱ ፡

ኢያሱ ፡ በወጡአቸው ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጠራ ፥ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የሄ
ዱትን ፡ የሰልፈኞች ፡ አለቆች ፦ ቅረቡ ፥ በእነ
ዚህም ፡ ነገሥታት ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ እግራችሁን ፡
አኑሩ ፡ አላቸው ። ቀረቡም ፡ በአንገታቸውም ፡
ላይ ፡ እግራቸውን ፡ አኖሩ ። ፳ ኢያሱም ፦ እግ
ዚአብሔር ፡ በምትወጉአቸው ፡ በጠላቶቻችሁ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያደርጋልና ፡ አትፍሩ ፥
አትደንግጡ ፤ ጽኑ ፥ አይዞአችሁ ፡ አላቸው ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መትተው ፡ ገደሉአቸው ፥ በአ
ምስቱም ፡ ዛፎች ፡ ላይ ፡ ሰቀሉአቸው ፤ እስከ ፡
ማታም ፡ ድረስ ፡ በዛፎቹ ፡ ተሰቅለው ፡ ቈዩ ።
፳፩ ፡ ፀሐይም ፡ ልትገባ ፡ በቀረበች ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡
አዘዘ ፥ ከዛፎችም ፡ አወረዱአቸው ፥ ተሸሽገ
ውም ፡ በነበሩበት ፡ ዋሻ ፡ ጣሉአቸው ፥ እስከ ፡
ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዋሻው ፡ አፍ ፡ ታላላቅ ፡ ድን
ጋይ ፡ ተደርጎአል ።
፳፪ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ መቄዳን ፡ ያዛት ፥
እርስዋንና ፡ ንጉሥዋንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡
መታ ፤ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ሁሉ ፡
ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ፥ ከእነርሱም ፡ አንዱን ፡
ስንኳ ፡ አላስቀረም ፤ በኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡ እን
ዳደረገ ፡ በመቄዳ ፡ ንጉሥ ፡ አደረገ ።
፳፫ ፡ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ከመቄዳ ፡ ወደ ፡ ልብና ፡ አለፉ ፥ ልብናንም ፡
፳፬ ፡ ወጉ ። እግዚአብሔርም ፡ እርስዋንና ፡ ንጉሥ
ዋን ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ እር
ስዋንም ፡ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ሁሉ ፡
በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መታ ፥ በእርስዋም ፡ አንዱን ፡
ስንኳ ፡ አላስቀረም ፤ በኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡ እን
ዳደረገው ፡ በልብና ፡ ንጉሥ ፡ አደረገ ።
፳፭ ፡ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ከልብና ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ አለፉ ፥ ከበቡአትም ፥
፳፮ ፡ ወጉአትም ። እግዚአብሔርም ፡ ለኪሶን ፡ በእ
ስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣት ፥ በሁለተኛ
ውም ፡ ቀን ፡ ያዙአት ፤ በልብናም ፡ እንዳደረ
ጉት ፡ ሁሉ ፥ እርስዋን ፡ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡
ነፍሳት ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱአቸው ።
፳፯ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የጌዝር ፡ ንጉሥ ፡ ሆራም ፡
ለኪሶን ፡ ለመርዳት ፡ ወጣ ፤ ኢያሱም ፡ አንድ ፡
ስንኳ ፡ ሳይቀር ፡ እርሱንና ፡ ሕዝቡን ፡ መታ ።
፳፰ ፡ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ከለኪሶ ፡ ወደ ፡ አዶላም ፡ አለፉ ፥ ከበቡአትም ፥
፳፱ ፡ ወጉአትም ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ያዙአት ፥ በሰይ
ፍም ፡ ስለት ፡ መቱአት ፤ በለኪሶም ፡ እንዳደረ
ገው ፡ ሁሉ ፥ በእርስዋ ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡
ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ።
፴ ፡ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ከአዶላም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ወጡ ፥ ወጉአትም ፥
፴፩ ፡ ያዙአትም ፤ እርስዋንም ፡ ንጉሥዋንም ፡ ከተሞ
ችዋንም ፡ ሁሉ ፡ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ነፍ
ሳት ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፤ በአዶላም ፡
እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤
እርስዋንም ፡ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡
ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ።
፴፪ ፡ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ዳቤር ፡ ተመለሰ ፥ ወጉአትም ፥ እርስዋ
ንም ፡ ንጉሥዋንም ፡ ከተሞችዋንም ፡ ያዙ ፤ በሰ
ይፍም ፡ ስለት ፡ መቱአቸው ፥ በእነርሱም ፡
ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡
አጠፋ ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤ በኬብሮን ፥
ደግሞ ፡ በልብናና ፡ በንጉሥዋ ፡ እንዳደረገው ፡
እንዲሁ ፡ በዳቤርና ፡ በንጉሥዋ ፡ አደረገ ።
፴፫ ፡ እንዲሁም ፡ ኢያሱ ፡ ምድሪቱን ፡ ሁሉ ፡ ተራ
ራማውን ፡ አገር ፡ ደቡቡንም ፡ ቈላውንም ፡
ቁልቁለቶችንም ፡ ነገሥታቶቻቸውንም ፡ ሁሉ ፡
መታ ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤ የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘውም ፡ ነፍስ ፡
ያለበትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ። ፴፬ ኢያሱም ፡
ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ እስከ ፡ ጋዛ ፡ ድረስ ፡ የጎሰም
ንም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ገባዖን ፡ ድረስ ፡
መታ ። የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ስለ ፡ ተዋጋላቸው ፡ ኢያሱ ፡
እነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ምድራቸውንም ፡
በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ያዘ ። ፴፭ ኢያሱም ፡ ከእርሱም ፡
ጋር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ወደ ፡
ጌልገላ ፡ ተመለሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስ ፡
ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማዶን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡
ዮባብ ፥ ወደ ፡ ሺምሮንም ፡ ንጉሥ ፥ ወደ ፡ አዚ
ፍም ፡ ንጉሥ ፥ በሰሜንም ፡ በተራራማው ፡ አገር ፥
፪ ፡ በከኔሬትም ፡ ደቡብ ፡ በዓረባ ፥ በቈላውም ፥ በም
ዕራብም ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ በዶር ፡ ኮረብታ ፡ ወደ ፡
ነበሩ ፡ ነገሥታት ፥ በምሥራቅና ፡ በምዕራብም ፡
ወዳለው ፡ ወደ ፡ ከነዓናዊው ፥ ወደ ፡ አሞራዊ
ውም ፥ ወደ ፡ ኬጢያዊውም ፥ ወደ ፡ ፈሪዛዊ
ውም ፥ በተራራማውም ፡ አገር ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡
ኢያቡሳዊው ፥ ከአርሞንዔምም ፡ በታች ፡ በም
ጽፋ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ኤዊያዊው ፡ ላከ ። ፫ እነዚ
ህም ፡ ከሠራዊቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ከእጅግ ፡ ብዙ ፡
ፈረሰኞችና ፡ ሰረገሎች ፡ ጋር ፡ ወጡ ፤ በባሕር ፡
ዳርም ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበረ ። ፬
እነዚህም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡
እስራኤልን ፡ ለመውጋት ፡ መጥተው ፡ በማሮን ፡
ውኃ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ሰፈሩ ።
፭ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አድርጌ ፡ በእስራ
ኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁና ፡ አትፍ
ራቸው ፤ የፈረሰኞቻቸውንም ፡ ቋንጃ ፡ ትቈርጣ
ለህ ፥ ሰረገሎቻቸውንም ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላ
ለህ ፡ አለው ። ፮ ኢያሱም ፡ ከሰልፈኞቹ ፡ ሁሉ ፡
ጋር ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ ማሮን ፡ ውኃ ፡ መጣባ
ቸው ፥ ወደቁባቸውም ። ፯ እግዚአብሔርም ፡
በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ መቱ
አቸውም ፥ ወደ ፡ ታላቂቱም ፡ ሲዶና ፥ ወደ ፡
ማሴሮንም ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡

ወደ ፡ ምጽፃ ፡ ሸለቆ ፡ አሳደዱአቸው ፤ ማንንም ፡
ሳያስቀሩ ፡ መቱአቸው ። ፰ ኢያሱም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገባቸው ፤ የፈረሰኞቻ
ውንም ፡ ቋንጃ ፡ ቈረጠ ፥ ሰረገሎቻቸውንም ፡
በእሳት ፡ አቃጠለ ።
፱ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ ተመልሶ ፡ አሶርን ፡
ያዘ ፥ ንጉሥዋንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደለ ፤ አሶርም ፡ አስ
ቀድሞ ፡ የእነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡
ነበረች ። ፱ በእርስዋም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ሁሉ ፡
በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፥ ፈጽመውም ፡ አጠፉ ፡
አቸው ፤ እስትንፋስ ፡ ያለውንም ፡ አላስቀሩም ፤
አሶርንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠላት ። ፲ የእግዚአብ
ሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘው ፥ ኢያሱ ፡
የእነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፥ ነገ
ሥታቶቻቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያዘ ፥ በሰይፍም ፡
ስለት ፡ መታቸው ፥ ፈጽሞም ፡ አጠፋቸው ።
እስራኤልም ፡ በኮረብቶቹ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡
ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ አላቃጠሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡
እስራኤል ፡ አሶርን ፡ ብቻ ፡ አቃጠሉአት ። ፲፩ የእ
ስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የእነዚህን ፡ ከተሞች ፡
ምርኮ ፡ ሁሉ ፡ ከብቶቹንም ፡ ለራሳቸው ፡ ዘረፉ ፤
ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በሰ
ይፍ ፡ ስለት ፡ መቱአቸው ፥ እስትንፋስ ፡ ያለው
ንም ፡ ሁሉ ፡ አላስቀሩም ። ፲፪ እግዚአብሔርም ፡
ባሪያውን ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ ሙሴ ፡
ኢያሱን ፡ አዝዞት ፡ ነበር ፥ ኢያሱም ፡ እንዲሁ ፡
አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ከዘዘው ፡ ሁሉ ፡
ምንም ፡ አላስቀረም ።
፲፫ ፡ ኢያሱም ፡ ያን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፥ ተራራማ
ውን ፥ ደቡቡንም ፡ ሁሉ ፥ የጎሰምንም ፡ ምድር ፡
ሁሉ ፥ ቈላውንም ፥ ዓረባንም ፥ የእስራኤል
ንም ፡ ተራራማውንና ፡ ቈላውን ፡ ያዘ ፥ እስከ ፡
ሴይርም ፡ ከሚያወጣው ፡ ወና ፡ ከሆነው ፡ ተራራ ፡
ጀምሮ ፡ ከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ በሊ
ባኖስም ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ያለ ፡ ጋድ ፡ ድረስ ፤ ነገሥታቶቻቸውንም ፡
ሁሉ ፡ ይዞ ፡ መታቸው ፡ ገደላቸውም ። ፲፬ ኢያ
ሱም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከእነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡
ጋር ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። ፲፭ በገባዖን ፡ ከሚኖሩ ፡ ከኤ
ዊያውያን ፡ በቀር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡
ሰላም ፡ ያደረገች ፡ አንዲት ፡ ከተማ ፡ አልነበረ
ችም ፤ ሁሉን ፡ በሰልፍ ፡ ያዙ ። ፲፮ እግዚአብሔር ፡
ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፥ ያጠፋአቸው ፡ ዘንድ ፡ ሞገ
ስንም ፡ እንዳያገኙ ፡ ፈጽመውም ፡ እንዳያጠፉ ፡
አቸው ፥ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡ ይጋጠሙ ፡ ዘንድ ፡
ልባቸውን ፡ እንዲያደነድኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡ ሆነ ።
፲፯ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ መጣ ፥ ከተራራ
ማውም ፡ አገር ፡ ከኬብሮንም ፡ ከዳቤርም ፡ ከአ
ናብም ፡ ከእስራኤልም ፡ ተራራማ ፡ ሁሉ ፡ ከይ
ሁዳም ፡ ተራራማ ፡ ሁሉ ፡ የሄናቅን ፡ ልጆች ፡
ገደለ ፤ ኢያሱም ፡ ከከተሞቻቸው ፡ ጋር ፡ ፈጽሞ ፡
አጠፋቸው ። ፲፰ በጋዛ ፡ በጌትም ፡ በአዛጦንም ፡
ጥቂቶች ፡ ቀሩ ፤ እንጂ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ምድር ፡ ከሄናቅ ፡ ልጆች ፡ ማንም ፡ ሳልቀረም ።
፲፱ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ሁሉ ፡
ኢያሱ ፡ ምድሪቱን ፡ ሁሉ ፡ ያዘ ፤ ኢያሱም ፡ ለእ
ስራኤል ፡ እንደ ፡ ክፍላቸውና ፡ እንደ ፡ ነገዳቸው ፡
ርስት ፡ አድርጎ ፡ ምድሪቱን ፡ ሰጣቸው ፤ ምድ
ሪቱም ፡ ከሰልፍ ፡ ዐረፈች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የመቱአቸው ፥ ከአ
ሮኖንም ፡ ሸለቆ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አርሞንዔም ፡
ተራራ ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ ዓረባ ፡
ሁሉ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡
ያለውን ፡ አገራቸውን ፡ የወረሱአቸው ፡ ነገሥ
ታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ በሐሴቦን ፡ የተቀመ
ጠው ፥ በአሮዔንም ፡ ሸለቆ ፡ አጠገብ ፡ ከሸለቆ ፡
ከአሮዔር ፥ ከሸለቆውም ፡ መካከል ፡ ጀምሮ ፡ የገ
ለዓድን ፡ እኩሌታ ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡
አሞን ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥ በምሥራቅም ፡
፪ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ዓረባ ፡ እስከ ፡ ኪኔሬት ፡ ባሕር ፡
ድረስ ፥ በቤትየሺሞት ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ እስከ
ሰው ፡ እስከ ፡ ዓረባ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ጨው ፡ ባሕር ፡
ድረስ ፥ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡
አፋፍ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ምድር ፡ የገዛው ፡
የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎን ፡ ከራፋይምም ፡
፫ ፡ ወገን ፡ የቀረ ፥ በአስታሮትና ፡ በኤድራይ ፡ የተ
ቀመጠው ፥ የአርሞንዔምንም ፡ ተራራ ፥ ሰል
ካን ፥ ባሳንንም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ጌሹራውያንና ፡
እስከ ፡ ማዕካታውያን ፡ ዳርቻ ፥ የገለዓድንም ፡
እኩሌታ ፡ እስከ ፡ ሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡
ሴዎን ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ የገዛው ፡ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡
ዐግ ። ፬ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴና ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ መቱአቸው ፤ የእግዚአብሔ
ርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ለሮቤል
ልጆች ፡ ለጋድም ፡ ልጆች ፡ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡
እኩሌታ ፡ ምድሪቱን ፡ ሰጣቸው ።
፭ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡
በሊባኖስ ፡ ሸለቆ ፡ ካለችው ፡ ከበላል ፡ ጋድ ፡
ወደ ፡ ሴይር ፡ እስከሚያወጣው ፡ ወና ፡ እስከ ፡
ሆነው ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ኢያሱ ፡ በየክፍላቸው ፡
ርስት ፡ አድርጎ ፡ ለእስራኤል ፡ ነገድ ፡ በሰጣት ፡
ምድር ፥ በተራራማው ፡ አገር ፥ በቈላውም ፥
በዓረባም ፥ በቀኑልቁላትም ፥ በምድረ ፡ በዳ
ውም ፥ በደጉቡም ፡ ያሉ ፡ ኬጢያውያን ፡ አሞ
ራውያንም ፡ ከነዓናውያንም ፡ ፈሪዛውያንም ፡
ኤዊያውያንም ፡ ኢያቡሳውያንም ፡ የሆኑ ፡ ኢያ
ሱና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የመቱአቸው ፡ የም
ድር ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የኢያሪኮ ፡ ፮
ንጉሥ ፥ በቤቴል ፡ አጠገብ ፡ ያለችው ፡ የጋይ ፡
ንጉሥ ፥ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፥ የኬብሮን ፡ ፯
ንጉሥ ፥ የየርሙት ፡ ንጉሥ ፥ የለኪሶ ፡ ንጉሥ ፥ ፰
የአዶላም ፡ ንጉሥ ፥ የጌዝር ፡ ንጉሥ ፥ የዳቤር ፡ ፱፡፲፡
ንጉሥ ፥ የጌድር ፡ ንጉሥ ፥ የሔርማ ፡ ንጉሥ ፥ ፲፡
የዓራድ ፡ ንጉሥ ፥ የልብና ፡ ንጉሥ ፥ የዓዶላም ፡ ፲፡
ንጉሥ ፥ የመቄዳ ፡ ንጉሥ ፥ የቤቴል ፡ ንጉሥ ፥ ፲፡

፲፯ የታጴዋ ፡ ንጉሥ ፡ የአፌር ፡ ንጉሥ ፡ የአፌቅ ፡
፲፰ ንጉሥ ፡ የለሸሮን ፡ ንጉሥ ፡ የማዶን ፡ ንጉሥ ፡
፲፱ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የሺምሮን ፡ ሚሮን ፡ ንጉሥ ፡
፳ የአዚፍ ፡ ንጉሥ ፡ የታዕናክ ፡ ንጉሥ ፡ የመ
፳፩ ጊዶ ፡ ንጉሥ ፡ የቃዴስ ፡ ንጉሥ ፡ በቀርሜ
፳፪ ሎስ ፡ የነበረ ፡ የዮቅንዓም ፡ ንጉሥ ፡ በዶር ፡ ከረ
፳፫ ብታ ፡ የነበረ ፡ የዶር ፡ ንጉሥ ፡ የጌልገላ ፡ አሕ
፳፬ ዛብ ፡ ንጉሥ ፡ የቲርሳ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥታቱ ፡
ሁሉ ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ኢያሱም ፡ ሸመገለ ፡ በዕድሜም ፡ አረጀ ፡ እግ
ዚአብሔርም ፡ አለው ፦ — አንተ ፡ ሸመገልህ ፡
በዕድሜህም ፡ አረጀህ ፡ ያልተወረሰች ፡ እጅግ ፡
፪ ብዙ ፡ ምድር ፡ ገና ፡ ቀርታለች ፡ የቀረችውም ፡
ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፡ የፍልስጥኤማውያንና ፡
የጌሹራውያን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በግብፅ ፡ ፊት ፡
ካለው ፡ ከሺሖር ፡ ወንዝ ፡ ጀምሮ ፡ በሰሜን ፡
በኩል ፡ እስከለችው ፡ የከነዓናውያን ፡ ሀገና ፡
እስከ ፡ ተቁጠረችው ፡ እስከ ፡ አቃሮን ፡ ዳርቻ ፡
ድረስ ፡ የጋዛ ፡ የአዛጦን ፡ የአስቀሎና ፡ የጌት ፡
የአቃሮን ፡ አምስቱ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ መኳ
፫ ንንት ፡ በደቡብም ፡ በኩል ፡ የኤዋውያን ፡ የከነ
ዓናውያንም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ለሲዶናውያንም ፡
የምትሆን ፡ መዓራ ፡ እስከ ፡ አሞራውያን ፡ ዳርቻ ፡
፬ እስከ ፡ አፌቅ ፡ ድረስ ፡ የጌባላውያውንም ፡
ምድር ፤ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ከአርሞንዔም ፡
ተራራ ፡ በታች ፡ ካለችው ፡ በአልጋድ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ሐማት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ያለችው ፡
፭ ሊባኖስ ፡ ሁሉ ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ የሚኖ
ሩትን ፡ ሁሉ ፡ ከሊባኖስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማሴ
ሮን ፡ ድረስ ፡ ሲዶናውያን ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ አባርራቸዋለሁ ፡
እንዳዘዝሁህም ፡ ምድራቸውን ፡ ለእስራኤል ፡
፮ ርስት ፡ አድርገህ ፡ አካፍላቸው ። አሁንም ፡
ይህን ፡ ምድር ፡ ለዘጠኙ ፡ ነገድ ፡ ለምናሴም ፡
ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስት ፡ አድርገህ ፡ ክፈለው ። ፡
፯ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ሰጣ
ቸው ፡ ከእርሱ ፡ ከምናሴ ፡ ጋር ፡ የሮቤልና ፡
የጋድ ፡ ልጆች ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በዮርዳ
ኖስ ፡ ማዶ ፡ ሙሴ ፡ የሰጣቸውን ፡ ርስታቸውን ፡
፰ ተቀበሉ ። በእርሳን ፡ ሸለቆ ፡ ዳር ፡ ካለችው ፡
ከአሮዔር ፡ በሸለቆውም ፡ መካከል ፡ ካለችው ፡
ከተማ ፡ ጀምሮ ፡ የሜድባን ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
፱ ዲቦን ፡ ድረስ ፡ በሐሴቦንም ፡ የነገሠ ፡ የአሞራ
ውያን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡
፲ እስከ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ገለዓ
ድንም ፡ የጌሹራውያንንና ፡ የማዕከታውያንን ፡
ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ የአርሞንዔምንም ፡ ተራራ ፡ ሁሉ ፡
፲፩ ባሳንንም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ሰልካ ፡ ድረስ ፡ በባ
ሳን ፡ የነበረውን ፡ በአስታሮትና ፡ በኤድራይ ፡
የነገሠውን ፡ የዐግን ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ እር
ሱም ፡ ከራፋይም ፡ የቀረ ፡ ነበረ ፡ እነዚህንም ፡
፲፫ ሙሴ ፡ መታቸው ፡ አጠፋቸውም ። የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ጌሹራውያንንና ፡ ማዕከታ
ውያንን ፡ አላወጡም ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ጌሹ
ርና ፡ ማዕከት ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ይኖራሉ ። ፡
ለሌዊ ፡ ነገድ ፡ ግን ፡ ርስት ፡ አልሰጠም ፤ ለእስ ፡ ፲፬
ራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቀረበው ፡
በእሳት ፡ የተደረገ ፡ መሥዋዕት ፡ ርስታቸው ፡
ነው ፥ እርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ።

ሙሴም ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገና ፡ ፲፭
ቸው ፡ ርስትን ፡ ሰጣቸው ። ድንበራቸውም ፡
በአሮዔር ፡ ሸለቆ ፡ ዳር ፡ ካለችው ፡ ከአሮዔር ፡
ጀምሮ ፡ በሸለቆው ፡ መካከል ፡ ያለችው ፡ ከተማ ፡
የሚደብ ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ ሐሴቦንም ፡ በሜዳውም ፡ ፲፮
ያሉት ፡ ከተሞችዋ ፡ ሁሉ ፥ ዲቦን ፡ ባሞትበ
ኣል ፡ ቤትበኣልምዖን ፡ ያዛጽ ፡ ቅዲሞት ፥ ፲፯
ሜፋዓት ፡ ቂርያታይም ፡ ሲብማ ፥ በሸለቆውም ፡ ፲፰
ተራራ ፡ ያለችው ፡ ጼሬትሻሐር ፡ ቤተ ፡ ፈጎር ፥ ፡ ፲፱
ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ምድር ፥ ፡
ቤትየሺሞት ፡ የሚዳውም ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፥ ፡ ፳
በሐሴቦንም ፡ የነገሠው ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡
የሴዎን ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ነበረ ፡ ሙሴም ፡
እርሱንና ፡ በምድሪቱ ፡ የተቀመጡትን ፡ የሴ
ዎንን ፡ መስፍናንት ፥ የምድያምን ፡ አለቆች ፡
ኤዊን ፡ ሮቆምን ፡ ሱሪን ፥ ሑሪን ፡ ሬባን ፡ መታ
ቸው ። ከገደሉአቸውም ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ የአስ ፡ ፳፪
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ምዋርተኛውን ፡ የቢዖርን ፡
ልጅ ፡ በለዓምን ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ። የሮቤ ፡ ፳፫
ልም ፡ ልጆች ፡ ድንበር ፡ የዮርዳኖስ ፡ ወንዝና ፡
ዳርቻው ፡ ነበረ ። የሮቤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡
ከተሞቻቸውም ፡ መንደሮቻቸውም ፡ በየወገና ፡
ቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ሙሴም ፡ ለጋድ ፡ ነገድ ፡ ለጋድም ፡ ልጆች ፡ ፳፬
በየወገናቸው ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።
ድንበራቸውም ፡ ኢያዜርና ፡ የገለዓድ ፡ ከተ ፡ ፳፭
ሞች ፡ ሁሉ ፥ የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ እኩ
ሌታ ፡ በረባት ፡ ፊት ፡ እስከለችው ፡ እስከ ፡ አሮ
ዔር ፡ ድረስ ፡ ከሐሴቦን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ራማት ፡ ፳፮
ምጽጴ ፡ እስከ ፡ ብጦኒም ፡ ድረስ ፡ ከመሃናይም ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዳቤር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥ በሸለ ፡ ፳፯
ቆውም ፡ ቤትሀራም ፡ ቤትኒምራ ፡ ሱኩት ፡
ጻፎን ፡ የሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ መንግ
ሥት ፡ ቅሬታ ፡ ነበረ ። ድንበሩም ፡ ዮርዳኖስና ፡
በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡
የኪኔሬት ፡ ባሕር ፡ ወዲያኛው ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ። ፡
የጋድ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ከተሞቻቸውም ፡ መን ፡ ፳፰
ደሮቻቸውም ፡ በየወገናቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ፡
ሙሴም ፡ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስት ፡ ፳፱
ሰጣቸው ፡ ለምናሴም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ እኩ
ሌታ ፡ በየወገናቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ድንበራቸ ፡ ፴
ውም ፡ ከመሃናይም ፡ ጀምሮ ፡ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡
የዐግ ፡ መንግሥት ፡ ባሳን ፡ ሁሉ ፡ በባሳንም ፡
ያሉት ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡ ሁሉ ፡ ስድሳው ፡
ከተሞች ፡ የገለዓድም ፡ እኩሌታ ፡ በባሳንም ፡ ፴፩
ያሉት ፡ የዐግ ፡ መንግሥት ፡ ከተሞች ፡ እስታ
ሮትና ፡ አድራይ ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡ ለምናሴ ፡

ልጅ ፡ ለማኪር ፡ ልጆች ፡ ሆኑ ፡ ለማኪር ፡ ልጆች ፡
እኩሌታ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ሙሴ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በኢያሪኮ ፡ አን
ጻር ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ሰለ ፡
የከፈለው ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ። ለሌዊ ፡ ነገድ ፡
ግን ፡ ሙሴ ፡ ርስት ፡ አልሰጠም ፤ የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳላቸው ፡ ርስታ
ቸው ፡ እርሱ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡
የወረሱት ፥ ከህኑ ፡ አልዓዛርና ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡
ኢያሱ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ የአባቶቻ
ቸው ፡ አለቆች ፡ ያከፈሉአቸው ፡ ርስት ፡ ይህ ፡
ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡
ለዘጠኙ ፡ ነገድና ፡ ለእኩሌታው ፡ በየርስታቸው ፡
በዕጣ ፡ አካፈሉአቸው ። ለሁለቱ ፡ ነገድና ፡ ለእ
ኩሌታው ፡ ነገድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሙሴ ፡
ርስት ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመካከላ
ቸው ፡ ለሌዋውያን ፡ ርስት ፡ አልሰጣቸውም ። ፡
የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ፡ ሁለት ፡
ነገዶች ፡ ነበሩ ፤ ለሌዋውያንም ፡ ከሚቀመጡባ
ቸው ፡ ከተሞች ፡ ለእንስሶቻቸውና ፡ ለከብቶቻ
ቸውም ፡ ከሚሆን ፡ መሰምርያቸው ፡ በቀር ፡
በምድሩ ፡ ውስጥ ፡ ድርሻ ፡ አልሰጡአቸውም ። ፡
እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አደረጉ ፥ ምድሪቱንም ፡
ተካፈሉ ።

የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በጌልገላ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡
ቀረቡ ፡ ቄኔዛዊውም ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡
አለው ፦ — ለእምላክ ፡ ሰው ፡ ለሙሴ ፡ ስለ ፡ እኔና ፡
ስለ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃዴስ ፡ በርኔ ፡
የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ታውቃለህ ። የእግዚአብ
ሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ምድርን ፡ እሰልል ፡ ዘንድ ፡
ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በላከኝ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የአርባ ፡
ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበርሁ ፡ እኔም ፡ በልቤ ፡ የነበረ ፡
ውን ፡ ቃል ፡ መለስኩለት ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ የወጡ ፡
ወንድሞቼ ፡ ግን ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ አቀለጡ ፤
እኔ ፡ ግን ፡ አምላኬን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሜ ፡
ተከተልሁ ። ሙሴም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፦ — አምላ
ኬን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽመህ ፡ ተከትለሃ
ልና ፡ እግርህ ፡ የረገጠው ፡ ምድር ፡ ለአንተና ፡
ለልጆችህ ፡ ለዘላለም ፡ በእርግጥ ፡ ርስት ፡ ይሆ ፡
ናል ፡ ብሎ ፡ ማለ ። አሁንም ፥ እነሆ ፥ እግዚአ
ብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥
እስራኤል ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሲዘሩ ፥ እርሱ ፡
እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡
አርባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሕይወት ፡ አኖረኝ ፤
አሁንም ፥ እነሆ ፥ ለእኔ ፡ ዛሬ ፡ ሰማንያ ፡ አም
ስት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ። ሙሴም ፡ በላከኝ ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ ነበርሁ ፥ ዛሬ ፡ ጕልበታም ፡ ነኝ ፡ ጕል
በቴም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እንዲሁ ፡
ዛሬ ፡ ለመዋጋት ፡ ለመውጣትም ፡ ለመግባትም ፡
ጕልበቴ ፡ ያው ፡ ነው ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ በዚ
ያን ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ይህን ፡
ተራራማ ፡ አገር ፡ ስጠኝ ፤ አንተ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
ዔናቃውያን ፡ ታላላቆችና ፡ የተመሸጉ ፡ ከተሞ
ችም ፡ በዚያ ፡ እንዳሉ ፡ ሰምተህ ፡ ነበር ፡ ምና
ልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፥
እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ አሳድዳቸ
ዋለሁ ።

ኢያሱም ፡ ባረከው ፡ ለዮፎኒም ፡ ልጅ ፡ ለካ ፡ ፲፫
ሌብ ፡ ኬብሮንን ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጠው ።
ስለዚህም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብ ፡ ፲፬
ሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ ስለ ፡ ተከተለ ፡ ኬብሮን ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ለቄኔዛዊው ፡ ለዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡
ርስት ፡ ሆነች ። የኬብሮንም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ፲፭
ቂርያትአርቦቅ ፡ ትባል ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ አርባቅ ፡
በዔኖቅ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ነበረ ። ምድሪቱም ፡ ከውጊያ ፡ ዐረፈች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

ለይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ ፩
እስከ ፡ ጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡ መጨ
ረሻ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ዕጣ ፡
ሆነላቸው ። በደቡብም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድን ፪
በራቸው ፡ እስከ ፡ ጨው ፡ ባሕር ፡ መጨረሻ ፡
ወደ ፡ ደቡብ ፡ እስከሚያይ ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ልሳን ፡
ነበረ ። ከዚያም ፡ በአቅረቢም ፡ ወቀበት ፡ በደ ፫
ቡብ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ጺንም ፡ አለፈ ፥
በቃዴስ ፡ በርኔ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥
በሐጽሮንም ፡ በኩል ፡ አለፈ ፥ ወደ ፡ አዳርም ፡
ወጣ ፥ ወደ ፡ ቀርቃ ፡ ዘረ ፥ ወደ ፡ አጽሞንም ፡ ፬
አለፈ ፥ በግብፅም ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥ የድ
ንበሩም ፡ መውጫ ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፡
በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበራችሁ ፡ ይህ ፡
ነው ። በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድን ፫
በር ፡ እስከ ፡ ጨው ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስም ፡
መጨረሻ ፡ ነበረ ። በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡
ድንበር ፡ በዮርዳኖስ ፡ መጨረሻ ፡ እስካለው ፡
እስከ ፡ ባሕሩ ፡ ልሳን ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፡ ከዚያም ፡ ፮
ድንበሩ ፡ ወደ ፡ ቤትሖግላ ፡ ወጣ ፥ በቤትዓረባ ፡
በሰሜን ፡ በኩል ፡ አለፈ ፥ ወደ ፡ ሮቤልም ፡
ልጅ ፡ ወደ ፡ ቦሀን ፡ ድንጋይ ፡ ወጣ ፡ ድንበሩም ፡ ፯
ከአኮር ፡ ሸለቆ ፡ ወደ ፡ ዳቤር ፡ ወጣ ፥ በሰሜን ፡
በኩል ፡ በአዱሚም ፡ ወቀበት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፥
በወንዙም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡
ጌልገላ ፡ ተመለከተ ፡ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡
ሳሚስ ፡ ውኃ ፡ አለፈ ፥ መውጫውም ፡ በዓይን ፡
ሮጌል ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፡ ድንበሩም ፡ በጺዎም ፡ ፰
ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ አጠገብ ፡ ኢያቡሳዊም ፡ ወደ ፡ ደቡ ፡
ወገን ፡ ወጣ ፤ ድንበሩም ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡
ዳር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በጺዎም ፡ ሸለቆ ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ወዳለው ፡
ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ድንበሩም ፡ ከተራ ፡ ፱
ራው ፡ ራስ ፡ ወደ ፡ ኔፍቶ ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ደረሰ ፥
ወደ ፡ ዔፍሮንም ፡ ተራራ ፡ ከተሞች ፡ ወጣ ፡

ቂርያትዩዓሪም ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ በአላ ፡
ፍ ፡ የረሰ ። ድንበሩም ፡ ከበአላ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡
ወደ ፡ ሴይር ፡ ተራራ ፡ ዛረ ፡ ከሳሎን ፡ ወደምት
ባል ፡ ወደ ፡ ዩዓሪም ፡ ተራራ ፡ ወገን ፡ በሰሜን ፡
በኩል ፡ አሰፈ ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ወረደ ፡ በተ
፲፰ ፡ ምና ፡ በኩልም ፡ አለፈ ። ድንበሩም ፡ ወደ ፡
አቃሮን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ ጠጣ ፡ ወደ ፡
ሽከሮን ፡ ደረሰ ፡ ወደ ፡ በአላ ፡ ተራራ ፡ አሰፈ ፡
በየብኒኤል ፡ በኩልም ፡ ወጣ ፡ የድንበሩም ፡
፲፱ ፡ መጨሪያ ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። በምዕራ
ቡም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበር ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡
ባሕርና ፡ እስከ ፡ ዳርቻው ፡ ድረስ ፡ ነበረ ። ለይ
ሁዳ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ በዘረያው ፡ ያለ ፡
ድንበራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲፫ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ እንዳዘዘው ፡ ለዮ
ፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ መካ
ከል ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ የምትባለውን ፡ ከተማ ፡
ድርሻ ፡ አደረጎ ፡ ሰጠው ፡ እርስዋም ፡ ኬብሮን ፡
ናት ። ይህም ፡ አርባቅ ፡ የዓናቅ ፡ አባት ፡ ነበረ ።
፲፪ ፡ ከሌብም ፡ ሦስቱን ፡ የዓናቅን ፡ ልጆች ፡ ሴሲ
ንና ፡ አኪመንን ፡ ተላሚንም ፡ ከዚያ ፡ አሳደደ ።
፲፫ ፡ ከዚያም ፡ በዳቤር ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ የዳ
ቤርም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ቂርያትሴፍርና ፡
፲፬ ፡ ትባል ፡ ነበር ። ከሌብም ፡ ፡ ቂርያትሴፍርን ፡
ለሚመታ ፡ ለሚይዛትም ፡ ልጁን ፡ ዓክሳን ፡
፲፭ ፡ አጋበዋለሁ ፡ አለ ። የካሌብ ፡ ወንድም ፡ የቄ
ኔዝ ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ያዛት ፡ ልጁንም ፡ ዓክ
፲፮ ፡ ሳን ፡ አጋባው ። እርስዋም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ በመ
ጣች ፡ ጊዜ ፡ ከአባትዋ ፡ እርሻ ፡ እንዲሰማን ፡
መከረችው ፡ እርስዋም ፡ ከአህያዋ ፡ ወረደች ፡
፲፱ ፡ ከሌብም ፡ — ምን ፡ ፈለግሽ ? አላት ። እርስ
ዋም ፡ — ስጦኝ ፡ ስጠኝ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡
ያለውን ፡ ምድር ፡ ሰጥተኸኛልና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡
የውኃውን ፡ ምንጭ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ። እር
ሱም ፡ የላይኛውንና ፡ የታችኛውን ፡ ምንጭ ፡
ሰጣት ።

፳ ፡ በየወገናቸውም ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡
ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፳፩ ፡ በደቡብም ፡ በኩል ፡ በምድራቸው ፡ ዳርቻ ፡
አጠገብ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ ድንበር ፡ ያሉት ፡
የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከተሞች ፡ እነዚህ ፡
፳፪ ፡ ነበሩ ፡ ቀብስኤል ፡ ኄዳር ፡ ያጉር ፡ ቂና ፡
፳፫ ፡ ዲሞና ፡ ዓድዓዳ ፡ ቃዲስ ፡ ሐጾር ፡ ዩት
፳፬፡፳፭ ፡ ናን ፡ ዚፍ ፡ ጢሌም ፡ በዓሎት ፡ ሐጾር ሐ
ዳታ ፡ ሐጾር ፡ የምትባለውም ፡ ቂርያትሐጾር ፡
፳፮፡፳፯ ፡ አማም ፡ ሽማዕ ፡ ሞላዳ ፡ ሐጾርጋዳ ፡ ሐሽሞን ፡
፳፰ ፡ ቤትጳሌጥ ፡ ሐጾርሹዓል ፡ ቤርሳቤህ ፡ ቢዝ
፳፱፡፴ ፡ ዮትያ ፡ በአላ ፡ ዒዩም ፡ ዓጼም ፡ ኤልቶላድ ፡
፴፩ ፡ ኪሲል ፡ ሔርማ ፡ ጺቅላግ ፡ ማድማና ፡ ሳን
፴፪ ፡ ሳና ፡ ልብዎት ፡ ሺልሂም ፡ ዓይን ፡ ሪሞን ፤ ዘያ
ዘጠኝ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

፴፫፡፴፬ ፡ በቈላው ፡ ኤሽቶኦል ፡ ጾርዓ ፡ አሽና ፡ ዛሣዋ ፡
፴፭ ፡ ዓይንገኒም ፡ ታጵዋ ፡ ዓይናም ፡ የርሙት ፡
፴፮ ፡ ዓዶላም ፡ ሰኮት ፡ ዓዜቃ ፡ ሸዓራይም ፡ ዓዲ
ታይም ፡ ግዴራ ፡ ግዴሮታይም ፡ አሥራ ፡
አራት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

፴፯ ፡ ጾናን ፡ ሐዳሻ ፡ ሚግዳልጋድ ፡ ዲልዓን ፡ ፴፰፡፴፱ ፡
ምጽጻ ፡ ዮቅትኤል ፡ ለኪሶ ፡ በጽቃት ፡ ፴፱ ፡
አዶላም ፡ ከበን ፡ ለሕማስ ፡ ኪትሊሽ ፡ ግዲ ፡ ፵፡፵፩ ፡
ሮት ፡ ቤትዳጎን ፡ ናዕማ ፡ መቄዳ ፡ አሥራ ፡
ስድስት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

፴፪ ፡ ልብና ፡ ዔቴር ፡ ዓሻን ፡ ይፍታሕ ፡ አሽና ፡ ፵፪፡፵፫ ፡
ንጺብ ፡ ቅዒላ ፡ አክዚብ ፡ መሪሳ ፤ ዘጠኝ ፡ ፵፬ ፡
ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

፴፫ ፡ አቃሮን ፡ ከተመሸጉና ፡ ከልተመሸጉ ፡ መን ፡ ፵፭ ፡
ደሮችዋ ፡ ጋር ፡ ከአቃሮንም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፵፮ ፡
ባሕር ፡ ድረስ ፡ በአዛሆን ፡ አጠገብ ፡ ያሉት ፡
ሁሉ ፡ ከመንደሮቻቸው ፡ ጋር ።

፴፬ ፡ አዛሆንና ፡ የተመሸጉና ፡ ያልተመሸጉ ፡ ፵፯ ፡
መንደሮችዋም ፡ ጋዛና ፡ የተመሸጉ ፡ ያልተመ
ሸጉም ፡ መንደሮችዋ ፡ እስከ ፡ ግብፅ ፡ ወን
ዝና ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ።

በተራራማውም ፡ አገር ፡ ሳምር ፡ የቲር ፡ ፡ ፵፱ ፡
ሶክ ፡ ዴና ፡ ዳቤር ፡ የምትባለው ፡ ቂርያትሰና ፡ ፡ ፵፡፵ ፡
ዓናብ ፡ አስትሞዓ ፡ ዓኒም ፡ ጎሶም ፡ ሖሎን ፡ ፡ ፵፡፵፩ ፡
ጊሎ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮ
ቻቸው ።

፵፪ ፡ አራብ ፡ ዱማ ፡ አሽዓን ፡ ያኒም ፡ ቤትታ ፡ ፵፡፵፫ ፡
ጹዋ ፡ አፈፋ ፡ ሐምማ ፡ ኬብሮን ፡ የምት ፡ ፵፬ ፡
ባል ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ ጺዖር ፡ ዘጠኝ ፡ ከተሞ
ችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ማዖን ፡ ቀርሜሎስ ፡ ዚፍ ፡ ዩጣ ፡ ኢዲ ፡ ፵፡፵፭ ፡
ዝራኤል ፡ ዮቅዲዓም ፡ ዛኖዋሕ ፡ ቃይን ፡ ፡ ፵፮ ፡
ጊብዓ ፡ ተምና ፡ አሥር ፡ ከተሞችና ፡ መንደ
ሮቻቸው ።

ሐልሐል ፡ ቤትጹር ፡ ጌዶር ፡ ማዕራት ፡ ፡ ፵፡፵፱ ፡
ቤትዓናት ፡ ኤልትቆን ፡ ስድስት ፡ ከተሞችና ፡
መንደሮቻቸው ።

ቂርያትዩዓሪም ፡ የምትባለው ፡ ቂርያትበአል ፡ ፡ ፵ ፡
ረባት ፡ ሁለት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

በምድረ ፡ በዓ ፡ ቤትዓረባ ፡ ሚዳን ፡ ስከከ ፡ ፡ ፵፡፵፩ ፡
ኒብሻን ፡ የጨው ፡ ከተማ ፡ ዓይንጋዲ ፡ ስድ ፡ ፵፡፵፪ ፡
ስት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ።

በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡትን ፡ ኢያቡሳ ፡ ፵፫ ፡
ውያንን ፡ ግን ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ሊያሳድዱ ፡
አቸው ፡ አልተቻላቸውም ፡ ኢያቡሳውያንም ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በኢ
የሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

የዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ዕጣ ፡ በኢያሪኮ ፡ አጠ ፡ ፩ ፡
ገብ ፡ በምሥራቁ ፡ በኩል ፡ ካለው ፡ ከዮርዳኖስ ፡
እንሥቶ ፡ በምድረ ፡ በዳውና ፡ በተራራማው ፡
በኩል ፡ ከኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወጣ ፡ ከቤ ፡ ፪ ፡
ቴል ፡ ወደ ፡ ሉዛ ፡ ወጣ ፡ በአርኪውያንም ፡
ዳርቻ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አጣሮት ፡ አለፈ ፡ ወደ ፡ ፫ ፡
ምዕራብም ፡ እስከ ፡ የፍሌጣውያን ፡ ዳርቻ ፡
እስከ ፡ ታችኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡

ጌዝር ፡ ድረስ ፡ ወረደ ፡ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፡
፬ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። የዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ምናሴና ፡
ኤፍሬም ፡ ርስታቸውን ፡ ወረሱ ።

፭ ፡ የኤፍሬምም ፡ ልጆች ፡ ድንበር ፡ በየወገኖቻ ፡ ፱ ፡
ቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡
የርስታቸው ፡ ድንበር ፡ አጣሮተአዳር ፡ እስከ ፡
፮ ፡ ላይኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፡ ድንበ ፡ ፱ ፡
ሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ሚክምታት ፡
በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወጣ ፡ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምሥ
ራቅ ፡ ወደ ፡ ተአናትሴሎ ፡ ዞረ ፡ ወደ ፡ ኢያኖክ ፡
፯ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ አለፈ ፡ ከኢያኖክም ፡
ወደ ፡ አጣሮትና ፡ ወደ ፡ ነዓራት ፡ ወረደ ፡ ወደ ፡
ኢያሪኮም ፡ ደረሰ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ ወጣ ። ፡ ፱ ፡
ድንበሩም ፡ ከታጵዋ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እስከ ፡
ቃና ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ አለፈ ፡ መውጫውም ፡
በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡
ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገናቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ፡ ፱ ፡
፱ ፡ ይኸውም ፡ በምናሴ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡
ለኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ከተለዩ ፡ ከተሞች ፡ ጋር ፡
ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ከመንደሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ነው ።
በጌዝርም ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ አላ
ሳደዱአቸውም ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ከነዓና
ውያን ፡ በኤፍሬም ፡ መካከል ፡ ተቀምጠዋል ።
የጦልበት ፡ ግብርም ፡ ያስገብሩአቸው ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ ዕጣ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የዮሴፍ ፡
በኩር ፡ እርሱ ፡ ነውና ። የምናሴም ፡ በኩር ፡
የገለዓድ ፡ አባት ፡ ማኪር ፡ ብርቱ ፡ ሰልፈኛ ፡
ስለ ፡ ነበረ ፡ ገለዓድንና ፡ ባሳንን ፡ ወረሰ ። ፡ ዕጣ
ውም ፡ ለቀሩት ፡ ለምናሴ ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻ
ቸው ፡ ለአቢዔዝር ፡ ልጆች ፡ ለከሌማ ፡ ልጆች ፡
ለአሥሪኤል ፡ ልጆች ፡ ለሰሌም ፡ ልጆች ፡ ለአ
ፈር ፡ ልጆች ፡ ለሸሚዳ ፡ ልጆች ፡ ሆነ ፡ የዮ
ሴፍ ፡ ልጅ ፡ የምናሴ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ በየወ
ገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ለምናሴ ፡ ልጅ ፡
ለማኪር ፡ ልጅ ፡ ለገለዓድ ፡ ልጅ ፡ ለአፈር ፡
ልጅ ፡ ለሰለጰጓድ ፡ ግን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንጂ ፡
ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፡ የሴቶች ፡ ልጆ
ቹም ፡ ስም ፡ ማህለህ ፡ ኑዓ ፡ ዔግላ ፡ ሚልካ ፡
ቲርጻ ፡ ነበረ ። ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡
አልዓዛርና ፡ ወደ ፡ ነዌ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡
ወደ ፡ አለቆችም ፡ ቀርበው ፡ — እግዚአብሔር ፡
በወንድሞቻችን ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ እንዲሰጠን ፡
ሙሴን ፡ አዘዘ ፡ አሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳ
ዘዘ ፡ በአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡
ሰጣቸው ። ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ካለው ፡ ከገለ
ዓድና ፡ ከባሳን ፡ አገር ፡ ሴላ ፡ ለምናሴ ፡ አሥር ፡
ዕጣ ፡ ሆነ ፤ የምናሴ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በወን
ዶች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ ተቀብለዋልና ፡
የገለዓድም ፡ ምድር ፡ ለቀሩት ፡ ለምናሴ ፡ ልጆች ፡
ሆኖአልና ።

የምናሴም ፡ ድንበር ፡ ከአሴር ፡ ጀምሮ ፡ በሴ
ኬም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እስከአለው ፡ እስከ ፡ ሚክም
ታት ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፡ ድንበሩም ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡
ወደ ፡ ዓይንታጵዋ ፡ ሰዎች ፡ አለፈ ። የታጵዋ ፡ ፯ ፡
ምድር ፡ ለምናሴ ፡ ነበረ ፤ በምናሴ ፡ ዳርቻ ፡ ያለው ፡
ታጵዋ ፡ ግን ፡ ለኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ሆነ ። ፡ ድን ፡ ፰ ፡
በሩም ፡ ወደ ፡ ቃና ፡ ወንዝ ፡ ከወንዙ ፡ በደቡብ ፡
ወገን ፡ ወረደ ፤ በምናሴም ፡ ከተሞች ፡ መካከል ፡
የነበሩት ፡ እነዚህ ፡ ከተሞች ፡ ለኤፍሬም ፡ ሆኑ ፡
የምናሴም ፡ ድንበር ፡ በወንዙ ፡ በኩል ፡ በሰ
ሜን ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፡
አጠገብ ፡ ነበረ ። ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ፱ ፡
ለኤፍሬም ፡ ነበረ ፡ በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡
ለምናሴ ፡ ነበረ ፡ ድንበሩም ፡ ባሕሩ ፡ ነበረ ፡
በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አሴር ፤ በምሥራቅም ፡
በኩል ፡ ወደ ፡ ይሳኮር ፡ ደረሰ ። ፡ በይሳኮርና ፡ ፲ ፡
በአሴር ፡ ካከከል ፡ ቤትሳንና ፡ መንደሮችዋ ፡
ይብልዓምና ፡ መንደሮችዋ ፡ ዶርና ፡ የመንደሮ
ችዋ ፡ ሰዎች ፡ ዓይንዶርና ፡ የመንደሮችዋ ፡
ሰዎች ፡ ታዕናክና ፡ የመንደሮችዋ ፡ ሰዎች ፡
መጊዶና ፡ የመንደሮችዋ ፡ ሰዎች ፡ ሦስቱ ፡ ክረ
ብቶች ፡ ለምናሴ ፡ ነበሩ ። ፡ የምናሴ ፡ ልጆች ፡ ፡ ፲፩ ፡
ግን ፡ የእነዚህን ፡ ከተሞች ፡ ሰዎች ፡ ሊያሳድዱአ
ቸው ፡ አልቻሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከነዓናውያን ፡
በዚያ ፡ አገር ፡ በመቀመጥ ፡ ጸኑ ። የእስራ ፡ ፲፪ ፡
ልም ፡ ልጆች ፡ በጸኑ ፡ ጊዜ ፡ ከነዓናውያንን ፡
የጦልበት ፡ ግብር ፡ አስገበሩአቸው ፡ ፈጽመ
ውም ፡ አሳሳደዱአቸውም ።

የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ኢያሱን ፡ — እኔ ፡ ብዙ ፡ ፲፫ ፡
ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ሆንሁ ፡ እስከ ፡ አሁንም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ስለ ፡ ባረከኝ ፡ ለምን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡
አንድም ፡ ዕጣ ፡ ብቻ ፡ ርስት ፡ አድርገህ ፡ ሰጠ
ኸኝ ? አሉት ። ኢያሱም ፡ — ብዙ ፡ ሕዝብስ ፡ ፲፬ ፡
ከሆንህ ፡ ተራራማውም ፡ የኤፍሬም ፡ አገር ፡
ጠብበህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ወጥተህ ፡
በፈርዛውያንና ፡ በራፋይም ፡ ምድር ፡ ለአ
ንተ ፡ ስፍራ ፡ መንጥር ፡ አላቸው ። የዮሴፍም ፡ ፲፭ ፡
ልጆች ፡ — ተራራማው ፡ አገር ፡ አይበቃንም ፡
በሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩት ፡ በቤትሳ
ንና ፡ በመንደሮችዋ ፡ በኢይዝራኤልም ፡ ሸለቆ ፡
ለሚኖሩት ፡ ከነዓናውያን ፡ የብረት ፡ ሰረገሎች ፡
አላቸው ፡ አሉት ። ኢያሱም ፡ የዮሴፍ ፡ ወገን ፡ ፲፮ ፡
ለሚሆኑ ፡ ለኤፍሬምና ፡ ለምናሴ ፡ — አንተ ፡
ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነህ ፡ ጽኑም ፡ ኃይል ፡ አለህ ፡
አንድ ፡ ዕጣ ፡ ብቻ ፡ አይሆንልህም ፤ ነገር ፡ ፲፯ ፡
ግን ፡ ተራራማው ፡ አገር ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ፡
ዱር ፡ እንኳ ፡ ቢሆንም ፡ ትመነጥረዋለህ ፡ ለአን
ተም ፡ ይሆናል ፤ ለከነዓናውያንም ፡ የብረት ፡
ሰረገሎች ፡ ቢሆኑላቸው ፡ የበረቱም ፡ ቢሆኑ ፡
ታሳድዳቸዋለህ ፡ አላቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በሴሎ ፡ ፩ ፡
ተሰበሰቡ ፡ በዚያም ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡
ተከሉ ፤ ምድሩም ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተገዛላቸው ። ፡
ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ያልተከፈሉ ፡ ፪ ፡

ሰባት ፡ ነገድ ፡ ቀርተው ፡ ነበር ። ኢያሱም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እላቸው ፡— የአበቶቻችሁ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጣችሁን ፡ ምድር ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ለመግባት ፡ ቸል ፡ ትላላችሁ ? ከየነገዳ ፡ ሁለ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ምረጡ ፡ እኔም ፡ እልካቸዋለሁ ፡ ተነሥተውም ፡ አገሩን ፡ ይዘዟሉ ፡ እንደ ፡ ርስታቸውም ፡ መጠን ፡ ይጽፉታል ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ይመለሳሉ ። በሰባትም ፡ ክፍል ፡ ይከፍሉታል ፡ ይሁዳ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በዳርቻው ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ፤ የዮሴፍ ፡ ወገኖች ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ በዳርቻው ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ። እናንተም ፡ ምድሩን ፡ በሰባት ፡ ክፍል ፡ ጻፉት ፡ የጻፋችሁትንም ፡ ወዲህ ፡ አምጡልኝ ፡ በእምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ ዕጣ ፡ አጣጥላችኋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ ርስታቸው ፡ ነውና ፡ ለሌዋውያን ፡ በመከከላችሁ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ የላቸውም ፡ ጋድም ፡ ሮቤልም ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ የሰጣቸውን ፡ ርስታቸውን ፡ ተቀብለዋል ።

ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ፤ ኢያሱም ፡ ምድሩን ፡ ሊጽፉ ፡ የሄዱትን ፡— ሂዱ ፡ ምድሩንም ፡ ዘራችሁ ፡ ጻፉት ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ተመለሱ ፤ በዚህም ፡ በሴሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዕጣ ፡ አጣጥላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ሰዎቹም ፡ ሄደው ፡ ምድሩን ፡ ዘሩ ፡ እንደ ፡ ከተሞችም ፡ በሰባት ፡ ክፍል ፡ ከፈሉት ፡ በመጽሐፍም ፡ ጻፉት ፡ ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ተመለሱ ። ኢያሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሴሎ ፡ ዕጣ ፡ አጣጣላቸው ፤ በዚያም ፡ ኢያሱ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ክፍሎቻቸው ፡ ምድሩን ፡ ከፈለ ።

የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ዕጣ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ የዕጣቸውም ፡ ዳርቻ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆችና ፡ በዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወጣ ። በሰሜን ፡ በኩል ፡ ድንበራቸው ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ጀመረ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ ወጣ ፥ ከዚያም ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወጣ ፥ መውጫውም ፡ በቤትአዌን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነበረ ። ድንበሩም ፡ ከዚያ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ቤቴል ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ ሉዛ ፡ አለፈ ፤ ድንበሩም ፡ በታችኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ አጣሮትአዳር ፡ ወረደ ። ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሄደ ፥ በቤትሖሮንም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ካለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዘረ ፤ መውጫውም ፡ ቂርያትይዓሪም ፡ በምትባል ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ በቂርያትበአል ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ የምዕራቡ ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ። የደቡብም ፡ ዳርቻ ፡ ከቂርያትይዓሪም ፡ መጨረሻ ፡ ነበረ ፤ ድንበሩም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ነፍቶ ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ወጣ ። ድንበሩም ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ መጨረሻ ፡ ወረደ ፥ እርሱም ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ሄኖም ፡ ሸለቆ ፡ ወደ ፡ ኢያቡስ ፡ ዳር ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወረደ ፥ ወደ ፡ ዓይንሮጌልም ፡ ወረደ ። ወደ ፡ ሰሜንም ፡ አለፈ ፤ በቤትሳሚስ ፡ ምንጭ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ በአዱሚም ፡ ዐቀበት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ጌሊሎት ፡ ደረሰ ፤ ወደ ፡ ሮቤልም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቦሀን ፡ ድንጋይ ፡ ወረደ ። በሰሜንም ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ዓረባ ፡ አጠገብ ፡ አለፈ ፥ ወደ ፡ ዓረባም ፡ ወረደ ። ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ቤትሖግላ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ አለፈ ፤ መውጫውም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዳርቻ ፡ መጨረሻ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በጨው ፡ ባሕር ፡ ልሳን ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ የደቡቡ ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ። በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ድንበሩ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ነበረ ። ይህ ፡ በዙሪያቸው ፡ ዳርቻ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ነበረ ።

የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከተሞች ፡ በየ ወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ። ኢያሪኮ ፥ ቤትሖግላ ፥ ዓመቀጺጽ ፥ ቤትዓረባ ፥ ዘማራይም ፥ ቤቴል ፥ ዓዊም ፥ ፋራ ፥ ኤፍራታ ፥ ከፊርዓ ፡ ሞናይ ፥ ዖፍኒ ፥ ጋባ ። አሥራ ፡ ሁለት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። ገባዖን ፥ ራማ ፥ ብኤሮት ፥ ምጽጳ ፥ ከፊራ ፥ አሞቂ ፥ ሬቄም ፥ የርጵኤል ፥ ተርአላ ፥ ጼላ ፥ ኤሌፍ ፥ ኢየሩሳሌም ፡ የምትባል ፡ የኢያቡስ ፡ ከተማ ፥ ቂርያትጊብዓት ፥ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። የብንያም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

ሁለተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ ርስታቸውም ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡ ርስታቸው ፡ ሆኑላቸው ፤ ቤርሳቤህ ፥ ሼባ ፥ ሞላዳ ፥ ሐጸርሹዓል ፥ ባላ ፥ ዔጼም ፥ ኤልቶላድ ፥ በቱል ፥ ሔርማ ፥ ጺቅላግ ፥ ቤትማርካቦት ፥ ሐጸርሱሳ ፥ ቤተ ፡ ለባአት ፥ ሻሩሔን ፤ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። ዓይን ፥ ሪሞን ፥ ዔቴር ፥ ዓሻን ፤ አራት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፤ እስከ ፡ ባዕላትብኤርና ፡ እስከ ፡ ደቡቡ ፡ ራማት ፡ ድረስ ፤ በእነዚህ ፡ ከተሞች ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ መንደሮች ፡ ሁሉ ። የስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፍል ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ሆነ ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ በዛባቸው ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በርስታቸው ፡ መካከል ፡ ወረሱ ።

ሦስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለዛብሎን ፡ ልጆች ፡ በየ ወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ የርስታቸውም ፡ ድንበር ፡ ወደ ፡ ሣሪድ ፡ ደረሰ ፤ ድንበራቸውም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ መርዓላ ፡ ወጣ ፥ እስከ ፡ ደበሼትም ፡ ደረሰ ፥ በዮቅንዓም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወንዝ ፡ ደረሰ ፤ ከሣሪድም ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ኪስሎትታቦር ፡ ዳርቻ ፡ ዘረ ፤ ወደ ፡ ዳብራትም ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ያፊዓም ፡ ደረሰ ፤ ከዚያም ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጋትሔፍርና ፡ ወደ ፡ ዒታቃጺን ፡ አለፈ ፤ ወደ ፡ ሪምንና ፡ ወደ ፡ ነዓቶን ፡ ዘረ ፥ መውጫውም ፡ በዒፍታሕኤል ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ። ቀጣት ፥ ነህላል ፥ ሺምሮን ፥ ይዳላ ፥ ቤተ ፡ ልሔም ፤ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። የዛብሎን ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

አራተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለይሳኮር ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ። ድንበራቸውም ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፥ ወደ ፡ ከስሎት ፥ ወደ ፡ ሱነም ፥ ወደ ፡ ሐፍራይም ፥ ወደ ፡ ሺአን ፥ ወደ ፡ አናሐራት ፥ ወደ ፡ ረቢት ፥ ወደ ፡ ቂሶን ፥ ወደ ፡ አቢጽ ፥ ወደ ፡ ሬሜት ፥ ወደ ፡ ዓይንጋኒም ፥ ወደ ፡ ዓይንሐዳ ፥ ወደ ፡ ቤትጳጼጽ ፡ ደረሰ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ታቦርና ፡ ወደ ፡ ሻሕጺማ ፥ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ደረሰ ፥ የድንበራቸውም ፡ መውጫ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ነበረ ፤ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

አምስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለአሴር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ። ድንበራቸውም ፡ ሔልቃት ፥ ሐሊ ፥ ቤጤን ፥ አዚፍ ፥ አላሜሌክ ፥ ዓምዓድ ፥ ሚሻአል ፤ ነበረ ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስና ፡ ወደ ፡ ሺሖርሊብናት ፡ ደረሰ ፤ ወደ ፡ ፀሐይም ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ቤትዳጎን ፡ ዘረ ፥ ወደ ፡ ዛብሎንም ፡ ወደ ፡ ይፍታሕኤል ፡ ሸለቆ ፥ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቤትዓሜቅና ፡ ወደ ፡ ንዒኤልም ፡ ደረሰ ፤ በስተ ፡ ግራ ፡ በኩልም ፡ ወደ ፡ ካቡል ፡ ወጣ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ዔብሮን ፥ ወደ ፡ ረአብ ፥ ወደ ፡ ሐሞን ፥ ወደ ፡ ቃና ፥ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ሲዶናም ፡ ደረሰ ። ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ራማ ፥ ወደ ፡ ተመሸገውም ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ዘረ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ሖሳ ፡ ዘረ ፤ መውጫውም ፡ በአክዚብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ነበረ ፤ ዑማ ፥ አፊቅ ፥ ረአብ ፡ ደግሞ ፡ ነበሩ ፥ ዘጠ ፡ ሁለት ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። የአሴር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ስድስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ። ድንበራቸውም ፡ ከሔሌፍ ፥ ከጸዕንኒም ፡ ዛፍ ፥ ከአዳሚኔቄብ ፥ ከየብኒኤል ፡ እስከ ፡ ለቁም ፡ ድረስ ፤ ነበረ ፤ መውጫውም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ነበረ ። ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ አዝኖትታቦር ፡ ዘረ ፥ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሖቆቅ ፡ ወጣ ፤ ከዚያም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ዛብሎን ፥ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አሴር ፥ በዮርዳኖስም ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ደረሰ ። የተመሸጉትም ፡ ከተሞች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፡ ጺዲም ፥ ሴር ፥ ሐማት ፥ ረቃት ፥ ኬኔሬት ፥ አዳማ ፥ ራማ ፥ አሰር ፥ ቃዴስ ፥ ኤድራይ ፥ ዓይንሐጾር ፥ ይርአን ፥ ሚግዳልኤል ፥ ሖሬም ፥ ቤትዓናት ፥ ቤትሳሚስ ፤ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ። የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ሰባተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለዳን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ። የርስታቸውም ፡ ዳርቻ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ጾርዓ ፥ ኤሽታኦል ፥ ዒርሼሜሽ ፥ ሻዕለቢን ፥ ኤሎን ፥ ይትላ ፥ ኤሎን ፥ ተምና ፥ ዕቅሮን ፥ ኢልተቄ ፥ ገባቶን ፥ ባዕላት ፥ ይሁድ ፥ ብኔብረቅ ፥ ጋትሪሞን ፥ ሜያርቆን ፥ ራቆን ። የዳንም ፡ ልጆች ፡ ከሌሼም ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ፥ ወጡ ፥ ያዙአትም ፥ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቱአት ፥ ወረሱአትም ፥ ተቀመጡባትም ፤ ስምዋንም ፡ በአባታቸው ፡ በዳን ፡ ስም ፡ ዳን ፡ ብለው ፡ ጠሩአት ። የዳን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተሞችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ምድሩንም ፡ ሁሉ ፡ በየድንበሩ ፡ ርስት ፡ እንዲሆን ፡ ከፈለው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለነዌ ፡ ልጅ ፡ ለኢያሱ ፡ በመካከላቸው ፡ ርስት ፡ ሰጡት ። በኤፍሬም ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ተምናሴራ ፡ የምትባለውን ፡ የፈለጋትን ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡት ፤ ከተማም ፡ ሠርቶ ፡ ተቀመጠበት ።

ካህኑ ፡ አልዓዛር ፥ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ የአባቶች ፡ አለቆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሴሎ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በዕጣ ፡ የተከፈሉት ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ። ምድሪቱንም ፡ መከፈል ፡ ጨረሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡— ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ተናገራቸው ፡— ሳይወድድ ፡ ሳያውቅም ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ገዳይ ፡ እንዲሸሽበቸው ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የነገርኋችሁን ፡ መማፀኛ ፡ ከተሞችን ፡ ለዩ ፤ ከደም ፡ ተበቃዩ ፡ መማፀኛ ፡ ይሆኑላቸኋል ። ከእነዚህም ፡ ከተሞች ፡ ወደ ፡ እንዲቱ ፡ ይሸሻል ፥ በከተማይቱም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ቆሞ ፡ በከተማይቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጆሮ ፡ ነገሩን ፡ ይናገራል ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ይቀበሉታል ፥ የሚቀመጥበትም ፡ ስፍራ ፡ ይሰጡታል ። ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ቢያሳድደው ፥ አስቀድሞ ፡ ሳይጠላው ፡ ባልንጀራውን ፡ በስሕተት ፡ ስለ ፡ ገደ

ለው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ በእጁ ፡ አሳልፈው ፡ አይ
፮ ስጡት ። በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ እስኪ
ቆም ፡ ድረስ ÷ በዚያም ፡ ወራት ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡
ካህን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በዚያች ፡ ከተማ ፡
ይቀመጥ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ይመ
ለሳል ÷ ወደ ፡ ከተማውም ፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ሸሽቶ ፡
ወደ ፡ ወጣባትም ፡ ከተማ ፡ ይገባል ።
፯ በንፍታሌም ፡ ባለው ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡
በገሊላ ፡ ቃዴስን ÷ በኤፍሬምም ፡ ባለው ፡ በተ
ራራማው ፡ አገር ፡ ሴኬምን ÷ በይሁዳም ፡ ባለው ፡
በተራራማው ፡ አገር ፡ ኬብሮን ፡ የምትባለውን ፡
፰ ቂርያትአርቦቅን ፡ ለዩ ። በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡
ከኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡
በምድረ ፡ በዳው ፡ በደልዳላው ፡ ስፍራ ፡ ቦሶ
ርን ÷ ከጋድም ፡ ነገድ ፡ በገለዓድ ፡ ራሞትን ÷
፱ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ በባሳን ፡ ጎላንን ፡ ለዩ ። በማ
ኅበሩ ፡ ፊት ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፡ በደም ፡ ተበ
ቃዩ ፡ እጅ ፡ እንዳይሞት ፡ ሳያውቅ ፡ ሰውን ፡ የገ
ደለ ፡ ወደዚያ ፡ እንዲሸሽ ÷ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ በመከከላቸውም ፡ ለሚቀመጥ ፡ መጸተኛ ፡
የተለዩ ፡ ከተሞች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩ የሌዋውያን ፡ አባቶች ፡ አለቆች ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡
ወደ ፡ አልዓዛር ÷ ወደ ፡ ነዌም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡
ኢያሱ ÷ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡
፪ አለቆች ፡ ቀረቡ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡
በሴሎ ፡ — እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የም
ንቀመጥባቸውን ፡ ከተሞች ÷ ለከብቶቻችንም ፡
መሰምርያዎች ፡ ትሰጡን ፡ ዘንድ ፡ አዝዞአል ፡
፫ ብለው ፡ ተናገሩአቸው ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ከርስታቸው ፡
እነዚህን ፡ ከተሞችና ፡ መሰምርያቸውን ፡ ለሌ
ዋውያን ፡ ሰጡ ።
፬ ለቀዓትም ፡ ወገኖች ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ፤ ሌዋውያ
ንም ፡ ለነበሩ ፡ ለካህኑ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ከይ
ሁዳ ፡ ነገድ ÷ ከስምዖንም ፡ ነገድ ÷ ከብንያምም ፡
ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተሞች ፡ በዕጣ ፡ ሆኑ
ላቸው ።
፭ ለቀሩትም ፡ ለቀዓት ፡ ልጆች ፡ ከኤፍሬም ፡
ነገድ ÷ ከዳንም ፡ ነገድ ÷ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩ
ሌታ ፡ አሥር ፡ ከተሞች ፡ በዕጣ ፡ ሆኑላቸው ።
፮ ለጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ ከይሳኮር ፡ ነገድ ÷ ከአ
ሴርም ፡ ነገድ ÷ ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ÷ በባሳ
ንም ፡ ካለው ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ አሥራ ፡
ሦስት ፡ ከተሞች ፡ በዕጣ ፡ ሆኑላቸው ።
፯ ለሜራሪም ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ከሮ
ቤል ፡ ነገድ ÷ ከጋድም ፡ ነገድ ፡ ከዛብሎንም ፡
ነገድ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ከተሞች ፡ ሆኑላቸው ።
፰ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህን ፡ ከተሞችና ፡
መሰምርያቸውን ፡ ለሌዋውያን ፡ በዕጣ ፡ ሰጡ ።
፱ ከይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከስምዖንም ፡ ልጆች ፡
ነገድ ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩትን ፡ እነዚህን ፡ ከተ
ሞች ፡ ሰጡ ። የፈተኛው ፡ ዕጣ ፡ ለእነርሱ ፡ ስለ ፡ ፲፡
ወጣ ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ የቀዓት ፡ ወገን ፡ ለሆኑ ፡
ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ሆኑ ። በይሁዳ ፡ ተራራማ ፡ ፲፩፡
አገር ፡ ያለችውን ፡ ቂርያትአርቦቅ ፡ የምትባለ
ውን ፡ ከተማ ፡ በዙሪያዋም ፡ ያለውን ፡ መሰም
ርያ ፡ ሰጡአቸው ፡ እርስዋም ፡ ኬብሮን ፡ ናት ÷
ይህም ፡ አርቦቅ ፡ የዔናቅ ፡ አባት ፡ ነበረ ። ፲፡ የከ ፲፪፡
ተማይቱን ፡ እርሻ ፡ ግን ፡ መንደሮችዋንም ፡ ለዮ
ፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ሰጡት ።
ለካህኑም ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ እነዚህን ፡ ሰጡ ፡ ፲፫፡
ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የሆነችውን ፡
ኬብሮንንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ልብናንና ፡ መሰ
ምርያዋን ÷ የተቲርንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ኤሽት ፡ ፲፬፡
ሞዓንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ሖሎንንና ፡ መሰምር ፡ ፲፭፡
ያዋን ÷ ዳቤርንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ዓይንንና ፡ ፲፮፡
መሰምርያዋን ÷ ዩጣንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ቤት ፡
ሳሚስንና ፡ መሰምርያዋን ፤ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡
ነገዶች ፡ ዘጠኝ ፡ ከተሞችን ፡ ሰጡ ። ከብንያ ፡ ፲፯፡
ምም ፡ ነገድ ፡ ገብዖንንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ናሲ ፡
ብንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ዓናቶትንና ፡ መሰምር ፡ ፲፰፡
ያዋን ÷ አልሞንንና ፡ መሰምርያዋን ፤ አራት ፡
ከተሞችን ፡ ሰጡ ። የአሮን ፡ ልጆች ፡ የካህናት ፡ ፲፱፡
ከተሞች ፡ ከመሰምርያቸው ፡ ጋር ፡ አሥራ ፡
ሦስት ፡ ናቸው ።
ለቀሩትም ፡ ለቀዓት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ሌዋው ፡ ፳፡
ያን ፡ የሰጣቸው ፡ ከተሞች ፡ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡
ደረሱአቸው ። በኤፍሬም ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ፳፩፡
ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የሆነችውን ፡
ሴኬምንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ጌዝርንና ፡ መሰም
ርያዋን ÷ ቂብጻይምንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ቤት ፡ ፳፪፡
ሖሮንንና ፡ መሰምርያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተሞች ፡
ሰጡአቸው ። ከዳንም ፡ ነገድ ፡ ኤልተቄንና ፡ ፳፫፡
መሰምርያዋን ÷ ገበቶንንና ፡ መሰምርያዋን ÷
ኤሎንንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ጋትሪሞንንና ፡ መሰ ፳፬፡
ምርያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡአቸው ።
ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ታዕናክንና ፡ መሰ ፳፭፡
ምርያዋን ÷ ጋትሪሞንንና ፡ መሰምርያዋን ፤ ሁለ
ቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡአቸው ። የቀሩት ፡ የቀ ፳፮፡
ዓት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ከመ
ሰምርያቸው ፡ ጋር ፡ አሥር ፡ ናቸው ።
ለሌዋውያንም ፡ ወገኖች ፡ ለጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ፳፯፡
ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡
መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ በባሳን ፡ ውስጥ ፡ የሆነች
ውን ፡ ጎላንንና ፡ መሰምርያዋን ÷ በኤሽትራ
ንና ፡ መሰምርያዋን ፤ ሁለቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡ
አቸው ። ከይሳኮርም ፡ ነገድ ፡ ቂሶንንና ፡ መሰም ፳፡
ርያዋን ÷ ዳብራትንና ፡ መሰምርያዋን ÷ የርሙ ፳፩፡
ትንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ዓይንጋኒምንና ፡ መሰ
ምርያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡአቸው ።
ከአሴርም ፡ ነገድ ፡ ሚሽአልንና ፡ መሰምርያዋን ፤ ፳፡
ዓብዶንንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ሔልቃትንና ፡ መሰ ፳፩፡
ምርያዋን ፤ ረአብንና ፡ መሰምርያዋን ፤ አራቱን ፡
ከተሞች ፡ ሰጡአቸው ። ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ፡ ፳፪፡
ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የሆነችውን ፡

በገሊላ ፡ ውስጥ ፡ ቃዴስንና ፡ መሰምርያዋን ÷
ሐሞትዶርንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ቀርታንንና ፡
መሰምርያዋን ፤ ሦስቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡአቸው ።
፳፫ የጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ በየወገኖ
ቻቸው ፡ አሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተሞች ፡ ከመሰምር
ያቸው ፡ ጋር ፡ ናቸው ።
፳፬ ከሌዋውያንም ፡ ለቀሩት ፡ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡
ወገን ፡ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ ዮቅንዓምንና ፡ መሰ
ምርያዋን ÷ ቀርታንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ዲሞ ፳፭፡
ናንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ነህላልንና ፡ መሰምርያ
ዋን ፡ አራቱን ፡ ከተሞች ፡ ሰጡ ። ከርቤልም ፡
ነገድ ፡ ቦሶርንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ያህጽንና ፡
መሰምርያዋን ÷ ቅዲሞትንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ፳፮፡
ሜፋዓትንና ፡ መሰምርያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተ
ሞች ፡ ሰጡ ። ከጋድም ፡ ነገድ ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡
መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የሆነችውን ፡ በገለዓድ ፡
ውስጥ ፡ ራሞትንና ፡ መሰምርያዋን ÷ መሃናይ ፳፯፡
ምንና ፡ መሰምርያዋን ÷ ሐሴቦንንና ፡ መሰምር
ያዋን ÷ ኢያዜርንና ፡ መሰምርያዋን ፤ አራቱን ፡
ከተሞች ፡ ሰጡ ። ከሌዋውያን ፡ ወገኖች ፡ የቀ ፳፡
ሩት ፡ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ በየ
ወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፡ ዕጣቸውም ፡
አሥራ ፡ ሁለት ፡ ከተማ ፡ ነበረ ።
፳፱ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡ የነቢ
ሩት ፡ የሌዋውያን ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ አርባ ፡ ስም
ንት ፡ ከተሞችና ፡ መሰምርያቸው ፡ ነበሩ ። ፴ እነ
ዚህም ፡ ከተሞች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከመሰምር
ያቸው ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፡ እነዚህም ፡ ከተሞች ፡
ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነበሩ ።
፴፩ እግዚአብሔርም ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአባ
ቶቻቸው ፡ የማለላቸውን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ሰጠ ፡ ወረሱአትም ፡ ተቀመጡባ
ትም ። ፴፪ እግዚአብሔርም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እንደ ፡
ማለላቸው ፡ በዙሪያቸው ፡ ካሉት ፡ አሳረፋቸው ፡
ከጠላቶቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ይቋቋማቸው ፡ ዘንድ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ አልቻለም ፤ እግዚአብሔርም ፡
ጠላቶቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡
ሰጣቸው ። ፴፫ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡
ከተናገረው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተፈጸመ ፡
እንጂ ፡ ምንም ፡ አልቀረም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ የሮቤልን ፡ ልጆችና ፡
የጋድን ፡ ልጆች ፡ የምናሴንም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡
፪ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — የእግዚአብሔር ፡
ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛችሁን ፡ ሁሉ ፡ ጠብቃችኋል ÷
እኔም ፡ ላዘዝኋችሁ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ታዝዛችኋል ፡
፫ ይህንም ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዘሬ ፡
ድረስ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ አልተዋችሁም ÷
የአምላካችሁንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡
፬ ጠብቃችኋል ። አሁንም ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ፡ ወንድሞቻች
ሁን ፡ አሳርፎአቸዋል ፤ አሁን ፡ እንግዲህ ፡
ተመለሱ ÷ ወደ ፡ ቤታችሁና ፡ የእግዚአብሔር ፡
ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ሰጣችሁ ፡
ወደ ፡ ርስታችሁ ፡ ምድር ፡ ሂዱ ። ፭ ብቻ ፡ የእግ ፡ ፭፡
ዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛችሁን ፡ ትእዛ
ዙንና ፡ ሕጉን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አምላካች
ሁን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወድዱ ፡ ዘንድ ፡ መንገ
ዱንም ፡ ሁሉ ፡ ትሄዱ ፡ ዘንድ ÷ ትእዛዙንም ፡
ትጠብቁ ፡ ዘንድ ÷ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ትጠጉ ፡
ዘንድ ÷ በፍጹምም ፡ ልባችሁ ፡ በፍጹምም ፡
ነፍሳችሁ ፡ ታመልኩ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ተጠን
ቀቁ ። ፮ ኢያሱም ፡ መረቃቸው ÷ ሰደዳቸውም ፤ ፮፡
ወደ ፡ ቤታቸውም ፡ ሄዱ ።
ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ሙሴ ፡ በባሳን ፡ ፯፡
ውስጥ ፡ ርስት ፡ ሰጥቶአቸው ፡ ነበር ፡ ለቀ
ረው ፡ ለእኩሌታው ፡ ግን ፡ ኢያሱ ፡ በዮር
ዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ በወንድ
ሞቻቸው ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ። ፰ ኢያ
ሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ በሰደዳቸው ፡ ጊዜ ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መረቃቸው ፡ — በብዙ ፡ ፰፡
ብልጥግና ፡ በእጅግም ፡ ብዙ ፡ ከብት ÷ በብ
ርም ÷ በወርቅም ÷ በናስም ÷ በብረትም ÷
በእጅግም ፡ ብዙ ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡
ተመለሱ ፤ የጠላቶቻችሁንም ፡ ምርኮ ፡ ከወን
ድሞቻችሁ ፡ ጋር ፡ ተካፈሉ ።
የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ የጋድም ፡ ልጆች ፡ የም ፡ ፱፡
ናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ሄዱ ፡ በሙሴም ፡ እጅ ፡
በተሰጠ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡
ተቀበሉአት ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡
ምድር ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ካለ
ችው ፡ ከሴሎ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡
ተመለሱ ። ፱ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ፲፡
ዮርዳኖስ ፡ አቅራቢያም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የሮ
ቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡
ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ በዚያ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡
ታላቅ ፡ መሠዊያ ፡ ሠሩ ። ለእስራኤልም ፡ ፲፩፡
ልጆች ፡ — እነሆ ÷ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡
በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ግዛት ÷ የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ በሉ ፡ በት ፡ ወገን ÷ የሮቤል ፡
ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡
እኩሌታ ፡ መሠዊያ ፡ ሠርተዋል ፡ የሚል ፡
ወሬ ፡ ደረሰላቸው ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፲፪፡
ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ወጥተው ፡ እነርሱን ፡ ሊዋጉ ፡
በሴሎ ፡ ተሰበሰቡ ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ፲፫፡
ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ወደ ፡
ጋድ ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩ
ሌታ ፡ የከህኑን ፡ የአልዓዛርን ፡ ልጅ ፡ ፊንሐ
ስን ፡ ላኩ ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አሥር ፡ አለ ፡ ፲፬፡
ቆች ፡ ነበሩ ፡ ከእስራኤል ፡ ከየነገዱ ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ አንድ ፡ የአባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡
እያንዳንዱም ፡ በእስራኤል ፡ አእላፋት ፡ መካ
ከል ፡ የአየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡
ነበረ ። ፲፭ በገለዓድም ፡ ምድር ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ፲፭፡
ሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ወደ ፡ ጋድ ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡

ምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ መጡ ፡ እንዲህም ፡
ብለው ፡ ተናገሩአቸው ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ማኅ
በር ፡ ሁሉ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ — ይህ ፡ በእ
ስራኤል ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ያደረጋችሁት ፡ ኃጢ
አት ፡ ምንድር ፡ ነው ? ዛሬ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ከመከተል ፡ ተመልሳችኋል ፤ ዛሬም ፡ መሠዊያ ፡
በመሥራታችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ሀም
ፃችኋል ። እኛ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከእርሱ ፡
ያልነጻንበት ፡ የፌጎር ፡ ኃጢአት ፡ ጥቂት ፡
ነውን ? በእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ መቅ
ሠፍት ፡ ወረደ ። እናንተ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ከመከተል ፡ ትመለሳላችሁን ? ዛሬ ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ብታምፁ ፡ ነገ ፡ በእስራኤል ፡
ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ። ነገር ፡ ግን ፡
የርስታችሁ ፡ ምድር ፡ የረከሰ ፡ ቢመስላችሁ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ወደሚቀመጥበት ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ምድር ፡ አልፋ
ችሁ ፡ በመካከላችን ፡ ውረሱ ፤ ከአምላካችንም ፡
ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሌላ ፡ ለእናንተ ፡
መሠዊያ ፡ በመሥራታችሁ ፡ በእግዚአብሔርና ፡
በእኛ ፡ ላይ ፡ አታምፁ ። የዘራ ፡ ልጅ ፡ አካን ፡
እርም ፡ ነገር ፡ በመውሰድ ፡ ኃጢአትን ፡ ስለ ፡
ሠራ ፡ በእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡
አልወረደምን ? እርሱም ፡ በኃጢአቱ ፡ ብቻ
ውን ፡ አልሞተም ።

የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምና
ሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ለእስራኤል ፡ አእላፋት ፡
አለቆች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ፡ —
የአግልክት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ የአግ
ልክት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ አው
ቆታል ፥ እስራኤልም ፡ ያውቀዋል ፤ በእግዚ
አብሔር ፡ ላይ ፡ ዐምፀንና ፡ ተላልፈን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ዛሬ ፡ አታድነን ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡
እንድንመለስ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡
የእህልን ፡ ቍርባን ፡ እንድናሳርግበት ፥ የደኅን
ነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ እንድናቀርብበት ፡ ብለን ፡
መሠዊያ ፡ ሠርተን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡
እርሱ ፡ ራሱ ፡ ይበቀለን ፤ ይልቁንም ፡ ከልብ
ችን ፡ ፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ — በሚመጣው ፡ ዘመን ፡
ልጆቻችሁ ፡ ልጆቻችንን ፡ — ከእስራኤል ፡ አም
ላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አላችሁ ?
እናንተ ፡ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በእኛና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ዮርዳኖ
ስን ፡ ድንበር ፡ አድርጎአልና ፡ በእግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ የላችሁም ፡ ይሉአቸ
ዋል ፡ ብለን ፡ ይህን ፡ አደረግን ። በዚህም ፡
ልጆቻችሁ ፡ ልጆቻችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡
ከመፍራት ፡ ያስተዋቸዋል ። ስለዚህም ፡ —
መሠዊያ ፡ እንሥራ ፡ አልን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለሚ
ቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ መሥዋ
ዕት ፡ አየደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእኛና ፡ በእና
ንተ ፡ መካከል ፡ ከእኛም ፡ በኋላ ፡ በትውልዳች
ንና ፡ በትውልዳችሁ ፡ መካከል ፡ በሚቃጠል ፡
መሥዋዕትና ፡ በቍርባን ፡ በደኅንነትም ፡ መሥ
ዋዕታችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልክ ፡ ዘንድ ፥
በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ ልጆቻችሁ ፡ ልጆቻች
ንን ፡ — በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡
የላችሁም ፡ እንዳይሉ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ። ስለ
ዚህም ፡ አልን ፡ — በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ለእኛ ፡
ወይም ፡ ለትውልዳችን ፡ ይህን ፡ ሲሉ ፥ እኛ ፡ —
እነሆ ፥ አባቶቻችን ፡ ያደረጉትን ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ መሠዊያ ፡ ምሳሌ ፡ እዩ ፤ በእኛና ፡ በእ
ናንተ ፡ መካከል ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ
ሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ መሥዋ
ዕት ፡ አይደለም ፡ እንላለን ። በማደሪያው ፡
ፊት ፡ ካለው ፡ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
መሠዊያ ፡ ሌላ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡
ለእህል ፡ ቍርባን ፡ ለሌላ ፡ መሥዋዕትም ፡ የሚ
ሆን ፡ መሠዊያን ፡ የሠራነው ፡ በእግዚአብሔር ፡
ላይ ፡ በማመፅ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ዛሬ ፡ መከ
ተልን ፡ ለመተው ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡
ከእኛ ፡ ይራቅ ።

ካህኑ ፡ ፊንሐስና ፡ የማኅበሩ ፡ አለቆች ፥ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ የእስራኤል ፡ አእላፋት ፡
አለቆች ፥ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡
የምናሴም ፡ ልጆች ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ። የካህኑም ፡
የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ ለሮቤል ፡ ልጆችና ፡
ለጋድ ፡ ልጆች ፡ ለምናሴም ፡ ልጆች ፡ — ይህን ፡
መተላለፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አላደረጋ
ችሁምና ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ እን
ዳለ ፡ ዛሬ ፡ እናውቃለን ፤ አሁን ፡ የእስራኤልን ፡
ልጆች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ አድናችኋል ፡
አላቸው ። የካህኑም ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊን
ሐስና ፡ አለቆቹ ፡ ከሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ከጋድ ፡
ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ከገለዓድ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡
አገር ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፥
ወሬም ፡ አመጡላቸው ። ነገሩም ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ ደስ ፡ አሰኘ ፡ የእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፥ ከዚያም ፡
ወዲያ ፡ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የተ
ቀመጡባትን ፡ ምድር ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወዋ
ተው ፡ አንዲወጉአቸው ፡ አልተናገሩም ። የሮ
ቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆችም ፡ — እግዚአብ
ሔር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በመካከላችን ፡
ምስክር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መሠዊያውን ፡ ምስክር ፡
ብለው ፡ ጠሩት ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡
እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ በዙሪያቸው ፡
ከሉት ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ካሳረፈ ፡ በኋላ ፥
ኢያሱም ፡ በሸመገለ ፡ በዕድሜውም ፡ ባረጀ ፡
ጊዜ ፥ ኢያሱ ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡ ሽማግሌዎ
ቻቸውንም ፡ አለቆቻቸውንም ፡ ፈራጆቻቸው
ንም ፡ ሹማምቶቻቸውንም ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡
አላቸው ፡ — እኔ ፡ ሽምግያለሁ ፥ በዕድሜም ፡
አርጅቻለሁ ፤ እናንተም ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እና
ንተ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ አይታችኋል ፤ ስለ ፡
እናንተ ፡ የተዋጋ ፡ እርሱ ፡ አምላካችሁ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ነው ። እነሆ ፥ እኔ ፡ ካጠፋኋቸው ፡
አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ጀምሮ ፡ በፀ
ሐይ ፡ መግቢያ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ለነገዶቻችሁ ፡ ርስት ፡ እንዲ
ሆኑ ፡ የቀሩትን ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ በዕጣ ፡
ከፈልሁላችሁ ። አምላካችሁም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እርሱ ፡ ከፊታችሁ ፡ በብርቱ ፡ ይበትናቸ
ዋል ፥ ከፊታችሁም ፡ ያሳድዳቸዋል ፡ አምላካ
ችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራችሁም ፡
ምድራቸውን ፡ ትወርሳላችሁ ። ስለዚህም ፡
በሙሴ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡
ለመጠበቅና ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ በርቱ ፥ ከእ
ርሱም ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡
አትበሉ ። በእናንተ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ቀሩት ፡
ወደ ፡ እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ አትግቡ ፤ የአግልክ
ቶቻቸውንም ፡ ስም ፡ አትጥሩ ፥ አትማሉባ
ቸውም ፥ አታምልኩአቸውም ፥ አትስገዱላቸ
ውም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዳደረጋችሁት ፡
ወደ ፡ አምላካችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ተጠጉ ፡ እንጂ ። እግዚአብሔር ፡ ታላላቆች
ንና ፡ ኃይለኞችን ፡ አሕዛብ ፡ ከፊታችሁ ፡ አስወ
ጥቶአል ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ ሊቋ
ቋማችሁ ፡ አልቻለም ። አምላካችሁ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡
የሚዋጋ ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡
ሰው ፡ ሺህ ፡ ሰውን ፡ ያሳድዳል ። አምላካችሁን ፡
እግዚአብሔርን ፡ ትወድዱት ፡ ዘንድ ፡ ለራሳ
ችሁ ፡ እጅግ ፡ ተጠንቀቁ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ተመ
ልሳችሁ ፡ በመካከላችሁ ፡ ወደ ፡ ቀሩት ፡ ወደ ፡
እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ብትጠጉ ፥ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡
ብትጋቡ ፥ እናንተም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ እነር
ሱም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ብትደራረሱ ፥ አምላ
ካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጣችሁ ፡ ከዚህች ፡
ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እስከትጠፋ ፡ ድረስ ፡
ጠውደቂያና ፡ ወጥመድ ፥ በጎናችሁም ፡ መገ
ፈፊያ ፥ በዓይናችሁም ፡ እሾህ ፡ ይሆኑባችኋል ፡
እንጂ ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንግ
ዲህ ፡ ወዲያ ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ ከፊታችሁ ፡
እንዳያሳድዳቸው ፡ ፈጽማችሁ ፡ እወቁ ።

እነሆም ፥ ዛሬ ፡ የምድርን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡
እሄዳለሁ ፡ እናንተም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡
እናንተ ፡ ከተናገረው ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳልቀረ ፡ በልባችሁ ፡ ሁሉ ፡
ነፍሳችሁም ፡ ሁሉ ፡ እወቁ ፡ ሁሉ ፡ ደርሰላች
ኋል ፤ ከእርሱም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አልቀረም ።
አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ መል
ካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ደረሰላችሁ ፥ አምላ
ካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጣችሁ ፡ ከዚህች ፡
ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እናንተን ፡ እስኪያጠፋ ፡
ችሁ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ ክፉን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያመጣባችኋል ። አምላካችሁ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያዘዛችሁን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስታ
ፈርሱ ፥ ሄዳችሁም ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ስታ
መልኩ ፥ ስትሰግዱላቸውም ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ይነድድባችኋል ፥ ከሰጣች
ሁም ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ ፈጥናችሁ ፡ ትጠ
ፋላችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

ኢያሱም ፡ የእስራኤልን ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡
ሴኬም ፡ በሰበሰበ ፥ የእስራኤልንም ፡ ሽማግሌ
ዎች ፡ አለቆቻቸውንም ፡ ፈራጆቻቸውንም ፡
ሹማምቶቻቸውንም ፡ ጠራ ። እነርሱም ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆሙ ። ኢያሱም ፡ ለሕ
ዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — የእስራኤል ፡ አም
ላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ — አበቶ
ቻችሁ ፥ የአብርሃምና ፡ የናኮር ፡ አባት ፡ ታራ ፥
አስቀድመው ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ተቀመጡ ፤ ሌሎ
ችንም ፡ አማልክት ፡ አመለኩ ። አባታችሁንም ፡
አብርሃምን ፡ ከወንዝ ፡ ማዶ ፡ ወስጄ ፡ በከነዓን ፡
ምድር ፡ ሁሉ ፡ መራሁት ፤ ዘሩንም ፡ አበዛሁ ፥
ይስሐቅንም ፡ ሰጠሁት ። ለይስሐቅም ፡ ያዕቆ
ብንና ፡ ዔሳውን ፡ ሰጠሁት ፤ ለዔሳውም ፡ የሴ
ይርን ፡ ተራራ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጠሁት ፤ ያዕ
ቆብም ፡ ልጆቹም ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረዱ ። ሙሴ
ንና ፡ አሮንንም ፡ ላክሁ ፥ በመካከላቸውም ፡
እንዳደረግሁ ፡ ግብፅን ፡ ቀሠፍሁ ፤ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ አወጣኋቸው ። አባቶቻችሁንም ፡ ከግ
ብፅ ፡ አወጣኋቸው ፥ ወደ ፡ ባሕሩም ፡ ደረሳችሁ ፡
ግብፃውያንም ፡ አባቶቻችሁን ፡ በሰረገሎችና ፡
በፈረሰኞች ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ አበ
ረሩአቸው ። ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሮጡ ፡
ጊዜ ፡ በእናንተና ፡ በግብፃውያን ፡ መካከል ፡
ጨለማ ፡ አደረገ ፥ ባሕሩንም ፡ መለሰባቸው ፥
አሰጠማቸውም ፡ ዓይኖቻችሁም ፡ በግብፅ ፡ ያደ
ረግሁትን ፡ አዩ ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
ተቀመጣችሁ ። እኔም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡
ተቀመጡበት ፡ ወደ ፡ አሞራውያን ፡ ምድር ፡
አመጣኋችሁ ፤ ከእናንተም ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ፥
አሳልፌም ፡ በእጃችሁ ፡ ሰጠኋችሁ ፥ ምድራቸ
ውንም ፡ ወረሳችሁ ፤ ከፊታችሁም ፡ አጠፋኋ
ቸው ። የሞዓብም ፡ ንጉሥ ፡ የሴፎር ፡ ልጅ ፡
በላቅ ፡ ተነሥቶ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፤
እንዲረግማችሁም ፡ የቢዖርን ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡
ልኮ ፡ አስጠራው ። እኔ ፡ ግን ፡ በለዓምን ፡ መስ
ማት ፡ አልወደድሁም ፤ እርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ በረ
ካችሁ ፥ እኔም ፡ ከእጁ ፡ አዳንኋችሁ ። ዮርዳ
ኖስንም ፡ ተሻገራችሁ ፥ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጣ
ችሁ ፤ የኢያሪኮም ፡ ሰዎች ፥ አሞራዊው ፥ ፌሬ
ዛዊው ፥ ከነዓናዊው ፥ ኬጢያዊው ፥ ጌርጌሳ
ዊው ፥ ኤዊያዊው ፥ ኢያቡሳዊው ፡ ተዋጉአ
ችሁ ፤ አሳልፌም ፡ በእጃችሁ ፡ ሰጠኋቸው ።
በፊታችሁም ፡ ተርብ ፡ ሰደድሁ ፥ በሰይፍህም ፡
በቀሥትህም ፡ ሳይሆን ፡ ሁለቱን ፡ የአሞራውያ
ንን ፡ ነገሥታት ፡ ከፊታችሁ ፡ አሳደዳቸው ።

ያልደከማችሁበትንም ፡ ምድር ÷ ያልሠራችኋ
ቸውንም ፡ ከተሞች ፡ ሰጠኋችሁ ÷ ተቀመጣች
ሁባቸውም ፡ ካልተከላችኋቸውም ፡ ከወይንና ፡
ከወይራ ፡ በላችሁ ።
፲፭ ፡ አሁንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ÷ በፍጹምም ፡
በእውነተኛም ፡ ልብ ፡ አምልኩት ፡ አባቶቻች
ሁም ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ በግብፅም ፡ ውስጥ ፡ ያመ
ለኩአቸውን ፡ አማልክት ፡ ከእናንተ ፡ አርቁ ÷
፲፮ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አምልኩ ። እግዚአብሔ
ርንም ፡ ማምለክ ፡ ክፉ ፡ መስሎ ፡ ቢታያችሁ ÷
አባቶቻችሁ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ሳሉ ፡ ያመለኩ
አቸውን ፡ አማልክት ፡ ወይም ፡ በምድራቸው ፡
ያላችሁባቸውን ፡ የአሞራውያንን ፡ አማልክት ፡
ታመልኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ የምታመልኩትን ፡ ዛሬ ፡
ምረጡ ። እኔና ፡ ቤቴ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡
እናመልካለን ።
፲፯ ፡ ሕዝቡም ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እግ
ዚአብሔርን ፡ ትተን ፡ ሌሎች ፡ አማልክትን ፡
፲፰ ፡ ማምለክ ፡ ከእኛ ፡ ይራቅ ፡ እኛንና ፡ አባቶቻች
ንን ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ÷
በንይናችንም ፡ ፊት ፡ እነዚያን ፡ ታላላቅ ፡ ተአ
ምራት ፡ ያደረገ ÷ በሄድንበትም ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡
ባለፍንባቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መከከል ፡
የጠበቀን ÷ እርሱ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡
፲፱ ፡ ነውና ። እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ በም
ድሪቱም ፡ የተቀመጡትን ፡ አሞራውያን ፡ ከፊ
ታችን ፡ አሳደደ ! ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ አምላካችን ፡
ነውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ።
፲፱ ፡ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ እርሱ ፡ ቅዱስ ፡ አም
ላክ ፡ ነውና ÷ እርሱም ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡
ነውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማምለክ ፡ አትችሉም ፡
መተላለፋችሁንና ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ይቅር ፡
፳ ፡ አይልም ። እግዚአብሔርን ፡ ትታችሁ ፡ እንግ
ዶችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ÷ መልካም ፡
ካደረገላችሁ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ያደርግባችኋል ÷ ያጠፋችሁማል ፡ አላቸው ።
፳፩ ፡ ሕዝቡም ፡ ኢያሱን ፦ እንዲህ ፡ አይሁን ፡ ነገር ፡
ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ፡ አሉት ።
፳፪ ፡ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ እንድታመልኩት ፡ እና
ንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ መረጣችሁ ፡ በራ
ሳችሁ ፡ ላይ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ፡ አላቸው ፡
እነርሱም ፦ ምስክሮች ፡ ነን ፡ አሉ ። እርሱም ፦ ፳፫
አሁን ፡ እንግዲህ ፡ በመካከላችሁ ፡ ያሉትን ፡ እን
ግዶች ፡ አማልክት ፡ አርቁ ÷ ልባችሁንም ፡ ወደ ፡
እስራኤል ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘ
ንብሉ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኢያሱን ፦ አም ፳፬
ላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ÷
ድምፁንም ፡ እንሰማለን ፡ አሉት ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አደረገ ÷ በሴኬምም ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡
አደረገላቸው ። ኢያሱም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፳፭
በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈ ፡ ታላ
ቁንም ፡ ድንጋይ ፡ ወስዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅ
ደስ ፡ አጠገብ ፡ ከነበረችው ፡ ከአድባሩ ፡ ዛፍ ፡
በታች ፡ አቆመው ። ኢያሱም ፡ ለሕዝቡ ፦ ፳፮
እነሆ ÷ የተናገረንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ሁሉ ፡ ሰምቶአልና ፡ ይህ ፡ ድንጋይ ፡ ይመሰክር
ብናል ፡ እንግዲህ ፡ አምላካችሁን ፡ እንዳትክዱ ፡
ይህ ፡ ምስክር ፡ ይሆንባችኋል ፡ አላቸው ። ኢያ
ሱም ፡ ሕዝቡን ፡ በእያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡
ሰደደ ።
እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ የእ ፳፱
ግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዕድ
ሜው ፡ መቶ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ሞተ ።
በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ በገዓስ ፡ ፴
ተራራ ፡ በሰሜን ፡ ባለችው ፡ በርስቱ ፡ ዳርቻ ፡
በተምናሴራ ፡ ቀበሩት ። ኢያሱ ፡ ባለበት ፡ ፴፩
ዘመን ፡ ሁሉ ÷ ከኢያሱም ፡ በኋላ ፡ በነበሩት ፡
ለእስራኤልም ፡ ያደረገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በወቁት ፡ በሽማግሌዎች ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ÷ እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመለኩ ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከግብፅ ፡ ያወጡትን ፡ ፴፪
የዮሴፍን ፡ አጥንት ፡ ያዕቆብ ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡
ከአሞር ፡ ልጆች ፡ በመቶ ፡ በግ ፡ በገዛው ፡ እርሻ ፡
በሴኬም ፡ ቀበሩት ፡ እርሻውም ፡ ለዮሴፍ ፡ ልጆች ፡
ርስት ፡ ሆነ ። የአሮንም ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ሞተ ፡ ፴፫
በተራራውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ለልጁ ፡ ለፊ
ንሐስ ፡ በተሰጠችው ፡ በጊብዓ ፡ መሬት ፡ ቀበሩት ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ኢያሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፦ ከነዓናውያንን ፡ ለመ
ውጋት ፡ ማን ፡ በፊት ፡ ይወጣልናል ? ብለው ፡
፪ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቁ ። እግዚአብሔርም ፦
ይሁዳ ፡ ይውጣ ፡ እነሆ ፡ ምድሪቱን ፡ በእጁ ፡
፫ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለሁ ፡ አለ ። ይሁዳም ፡ ወንድ
ሙን ፡ ስምዖንን ፦ ከነዓናውያንን ፡ እንወጋ ፡
ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዕጣዬ ፡ ውጣ ÷ እኔም ፡
ደግሞ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዕጣህ ፡ እሄዳለሁ ፡
አለው ። ስምዖንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሄደ ።
፬ ፡ ይሁዳም ፡ ወጣ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከነዓናው
ያንንና ፡ ፈሪዛውያንን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡
ሰጣቸው ÷ ከእነርሱም ፡ በቤዜቅ ፡ ውስጥ ፡
አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ። አዶኒቤዜቅንም ፡ ፭
በቤዜቅ ፡ አገኙትና ፡ ተዋጉት ፡ ከነዓናውያን
ንና ፡ ፈሪዛውያንንም ፡ መቱአቸው ። አዶኒቤ ፮
ዜቅም ፡ ሸሸ ፡ አሳድደውም ፡ ያዙት ÷ የእጁ
ንና ፡ የእግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ቈረጡ ።

፯ ፡ አዶኒቤዜቅም ፦ የእጃቸውና ፡ የእግራቸው ፡
አውራ ፡ ጣት ፡ የተቈረጡ ፡ ሰብ ፡ ነገሥታት ፡
ከገበታዬ ፡ በታች ፡ ፍርፋሪ ፡ ይለቅሙ ፡ ነበር ፡
እኔ ፡ እንዳደረግሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡
መለሰልኝ ፡ አለ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ አመ
ጡት ÷ በዚያም ፡ ሞተ ።
፰ ፡ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ተዋግ
ተው ፡ ያዙአት ÷ በሰይፍ ፡ ስለትም ፡ መቱአት ÷
ከተማይቱንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉአት ። ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በተራራማው ፡
አገርና ፡ በደቡቡ ፡ በኩል ፡ በቈላውም ፡ ውስጥ ፡
የሚኖሩትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ ሊወጉ ፡ ወረዱ ።
፱ ፡ ይሁዳም ፡ በኬብሮን ፡ የሚኖሩትን ፡ ከነዓናውያ
ንን ፡ ሊወጋ ፡ ሄደ ። የኬብሮንም ፡ ስም ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ቂርያትአርበቅ ፡ ነበረ ። ሴሲንና ፡ አኪ
መንን ፡ ተላሚንም ፡ ገደሉ ።
፲ ፡ ከዚያም ፡ የዳቤርን ፡ ሰዎች ፡ ሊወጋ ፡ ሄደ ! ፲፩
አስቀድሞም ፡ የዳቤር ፡ ስም ፡ ቅርያትሤፍር ፡
ነበረ ። ካሌብም ፦ ቅርያትሤፍርን ፡ ለሚመ
ታና ፡ ለሚይዝ ፡ ልጄን ፡ ዓክሳን ፡ አጋባዋለሁ ፡
አለ ። የካሌብም ፡ ትንሽ ፡ ወንድም ፡ የቄኔዝ ፡ ፲፪
ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ያዛት ፡ ልጁንም ፡ ዓክሳን ፡
አጋባው ። እርስዋም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ በመጣች ፡ ፲፫
ጊዜ ፡ ከአባትዋ ፡ እርሻ ፡ እንዲለምን ፡ መከረ
ችው ። እርስዋም ፡ ከአህያዋ ፡ ወረደች ፡ ካሌ
ብም ፦ ምን ፡ ፈለግሽ ? አላት ። እርስዋም ፦ ፲፬
በረከትን ፡ ስጠኝ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡
ምድር ፡ ሰጥተኸኛልና ፡ የውኃ ፡ ምንጭ ፡ ደግሞ ፡
ስጠኝ ፡ አለችው ። ካሌብም ፡ ላይኛውንና ፡ ታች
ኛውን ፡ ምንጭ ፡ ሰጣት ።
፲፭ ፡ የቄናዊው ፡ የሙሴ ፡ አማት ፡ ልጆችም ፡ ከይ
ሁዳ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ዘንባባ ፡ ካለባት ፡ ከተማ ፡
ተነሥተው ፡ ከዓራድ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወዳ
ለው ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጡ ፡ ሄደ
፲፮ ፡ ውም ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተቀመጡ ። ይሁዳም ፡
ከወንድሙ ፡ ከስምዖን ፡ ጋር ፡ ሄደ ÷ በጽፋት ፡
የተቀመጡትንም ፡ ከነዓናውያንን ፡ መቱ ÷ ፈጽ
መውም ፡ አጠፉአት ። የከተማይቱንም ፡ ስም ፡
፲፯ ፡ ሖርማ ፡ ብለው ፡ ጠሩአት ። ይሁዳም ፡ ጋዛንና ፡
ዳርቻዋን ÷ አስቀሎናንና ፡ ዳርቻዋን ÷ አቃሮ
፲፰ ፡ ንንና ፡ ዳርቻዋን ፡ ያዘ ። እግዚአብሔርም ፡ ከይ
ሁዳ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ ይሁዳም ፡ ተራራማውን ፡
አገር ፡ ወረሰ ፡ በሸለቆው ፡ የሚኖሩት ፡ ግን ፡
የብረት ፡ ሰረገሎች ፡ ነበሩአቸውና ፡ ሊያወጣ
፲፱ ፡ ቸው ፡ አልቻለም ። ሙሴም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡
ለካሌብ ፡ ኬብሮንን ፡ ሰጡት ፡ ከዚያም ፡ ሦስ
ቱን ፡ የዔናቅ ፡ ልጆች ፡ አወጣ ። ነገር ፡ ግን ፡
በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ኢያቡሳውያንን ፡
የብንያም ፡ ልጆች ፡ አላወጡአቸውም ፡ ኢያ
ቡሳውያንም ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጠዋል ።
፳፩ ፡ የዮሴፍም ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በቤቴል ፡ ላይ ፡
ወጡ ÷ እግዚአብሔርም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ።
፳፪ ፡ የዮሴፍም ፡ ወገን ፡ ቤቴልን ፡ የሚሰልሉ ፡ ላኩ ።
አስቀድሞም ፡ የከተማይቱ ፡ ስም ፡ ሉዛ ፡ ይባል ፡
ነበር ። ጠባቂዎቹም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ፳፫
ሲወጣ ፡ አይተው ፦ የከተማይቱን ፡ መግቢያ ፡
አሳየን ÷ እኛም ፡ ቸርነት ፡ እናደርግልሃለን ፡
አሉት ። የከተማይቱንም ፡ መግቢያ ፡ አሳያ ፡ ፳፬
ቸው ÷ ከተማይቱንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፡
ያንን ፡ ሰውና ፡ ወገኖቹን ፡ ግን ፡ ለቀቁአቸው ።
ሰውዮውም ፡ ወደ ፡ ኬጢያውያን ፡ ምድር ፡ ሄደ ÷ ፳፭
በዚያም ፡ ከተማን ፡ ሠራ ÷ ስምዋንም ፡ ሉዛ ፡
ብሎ ፡ ጠራት ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ስምዋ ፡
ይህ ፡ ነው ።
ምናሴም ፡ የቤትሳንንና ፡ የመንደሮቹን ÷ ፳፮
የታዕናክንና ፡ የመንደሮቹን ÷ የዶርንና ፡ የመ
ንደሮችዋን ÷ የይብለዓምንና ፡ የመንደሮቹን ÷
የመጊዶንና ፡ የመንደሮችዋን ፡ ሰዎች ፡ አላወጣ
ቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከነዓናውያን ፡ በዚያ ፡
አገር ፡ በመቀመጥ ፡ ጸኑ ። እስራኤልም ፡ በበ ፳፯
ረቱ ፡ ጊዜ ፡ ከነዓናውያንን ፡ አስገበሩአቸው ÷
ፈጽመውም ፡ አላወጡአቸውም ።
ኤፍሬምም ፡ በጌዝር ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓ ፳፱
ናውያንን ፡ አላወጣቸውም ! ነገር ፡ ግን ፡ ከነዓ
ናውያን ፡ በመካከላቸው ፡ በጌዝር ፡ ተቀመጡ ።
ዛብሎንም ፡ የቂድሮንንና ፡ የነህሎልን ፡ ሰዎች ፡ ፴
አላወጣቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከነዓናውያን ፡ በመ
ካከላቸው ፡ ተቀመጡ ÷ ግብርም ፡ የሚገብሩለት ፡
ሆኑ ።
አሴርም ፡ የዓኮንና ፡ የሲዶንን ፡ የአሕላብንም ፡ ፴፩
የአክዚብንም ፡ የሐሌባንም ፡ የአፌቅንም ፡ የረ
አብንም ፡ ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ። በዚያችም ፡ ፴፪
ምድር ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓናውያን ፡ አላወ
ጡአቸውምና ፡ በመካከላቸው ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡
ተቀመጡ ።
ንፍታሌምም ፡ የቤትሳሚስንና ፡ የቤትዓናትን ፡ ፴፫
ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ÷ በምድሩም ፡ በተቀ
መጡት ፡ በከነዓናውያን ፡ መካከል ፡ ተቀመጡ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የቤትሳሚስና ፡ የቤትዓናት ፡ ሰዎች ፡
ግብር ፡ የሚገብሩለት ፡ ሆኑ ።
አሞራውያንም ፡ የዳንን ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ተራ ፡ ፴፬
ራማው ፡ አገር ፡ እንዲያፈገፍጉ ፡ አስገደዱአ
ቸው ÷ ወደ ፡ ሸለቆውም ፡ እንዳይወርዱ ፡ ከለ
ከሉአቸው ። አሞራውያን ፡ በሔሬስ ፡ ተራ ፡ ፴፭
ራና ፡ በኤሎን ፡ በሸዓልቢምም ፡ በመቀመጥ ፡
ጸኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዮሴፍ ፡ ቤት ፡ እጅ ፡ ከበ
ደች ÷ አስገበረቻቸውም ። የአሞራውያንም ፡ ፴፮
ድንበር ፡ ከአቅረቢም ፡ ዐቀበት ፡ ከጭንጫው ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ ድረስ ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከጌልገላ ፡ ወደ ፡ ፩
ቦኪም ፡ ወጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እኔ ፡ ከግብፅ ፡
አውጥቻችኋለሁ ÷ ለአባቶቻችሁም ፡ ወደ ፡ ማል
ሁላቸው ፡ ምድር ፡ አግብቻችኋለሁ ፡ እኔም ፡ ፦
ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ያደረግሁትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ለዘላለም ፡ አላፈርስም ፤ እናንተም ፡ መሠዊያ ፡ ፪

ቸውን ፡ አፍርሱ ፡ እንጂ ፡ በዚህች ፡ ምድር ፡ ከሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አታድርጉ ፡
አልሁ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ቃሌን ፡ አልሰማች
፫ ፡ ሁም ፤ ይህንስ ፡ ለምን ፡ አደረጋችሁ ? ስለዚ
ህም ፡— ከፊታችሁ ፡ አላወጣቸውም ÷ ነገር ፡
ግን ፡ ያስጨንቋችኋል ÷ አማልክቶቻቸውም ፡
፬ ፡ ወጥመድ ፡ ይሆኑባችኋል ፡ አልሁ ። የእግዚአ
ብሔርም ፡ መልእክ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ድም
፭ ፡ ፃቸውን ፡ አንሥተው ፡ አለቀሱ ። የዚያንም ፡
ስፍራ ፡ ስም ፡ ቦኪም ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፡ በዚ
ያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠዉ ።
፮ ፡ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፡ በሰናበተ ፡ ጊዜ ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ምድሪቱን ፡ ሊወርሱ ፡ ወደ ፡
፯ ፡ እየርስታቸው ፡ ሄዱ ። ኢያሱም ፡ በነበረበት ፡
ዘመን ፡ ሁሉ ÷ ለእስራኤልም ፡ ያደረገውን ፡ ታላ
ቁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ባዩት ÷
ከኢያሱ ፡ በኋላ ፡ በነበሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ÷ ሕዝቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመለኩ ።
፰ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡
ዕድሜው ፡ መቶ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡
፱ ፡ ሞተ ። በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡
በገዓስ ፡ ተራራ ፡ በሰሜን ፡ በለችው ፡ በርስቱ ፡
፲ ፡ ዳርቻ ፡ በተምናሔራስ ፡ ቀበሩት ። ትውልድ ፡
ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ተከማቹ ፤
ከእነዚያም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለእስራኤ
ልም ፡ ያደረገውን ፡ ሥራ ፡ ያላወቀ ፡ ሌላ ፡ ትው
ልድ ፡ ተነሣ ።
፲፩ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ክፉ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ÷ በአሊ
፲፪ ፡ ምንም ፡ አመለኩ ። ከግብፅ ፡ ምድርም ፡ ያወ
ጣቸውን ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ ተዉ ÷ በዙሪያቸውም ፡ ካሉት ፡
ከአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡
ተከተሉ ÷ ሰገዱላቸውም ፡ እግዚአብሔርንም ፡
፲፫ ፡ አስቈጡ ። እግዚአብሔርንም ፡ ትተው ፡ በአ
፲፬ ፡ ልንና ፡ አስታሮትን ፡ አመለኩ ። የእግዚአብ
ሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ ወደ ፡
ማረኩአቸውም ፡ ማራኪዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጣቸው ፤ በዙሪያቸውም ፡ ባሉት ፡ በጠላቶች
ቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ÷ ጠላቶቻቸ
ውንም ፡ ከዚያ ፡ ወዳያ ፡ ሊቋቋሙ ፡ አልቻ
፲፭ ፡ ሉም ። እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ÷
እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ማለ ÷
ወደ ፡ ወጡበት ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡
ትክፋባቸው ፡ ነበረች ፤ እጅግም ፡ ተጨነቁ ።
፲፮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ መሳፍንትን ፡ አስነሣ
ቸው ÷ ከሚማርኩአቸውም ፡ እጅ ፡ አዳኑአ
፲፯ ፡ ቸው ። ሌሎች ፡ አማልክትን ፡ ተከተለው ፡ አመነ
ዘሩ ፡ ሰገዱላቸውም ፡ እንጂ ፡ መሳፍንቶቻቸ
ውን ፡ አልሰሙም ፤ አባቶቻቸውም ፡ ይሄዱበት ፡
ከነበረ ፡ መንገድ ፡ ፈጥነው ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፡ አባ
ቶቻቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡
፲፰ ፡ ታዘዙ ፡ እንዲሁ ፡ አላደረጉም ። እግዚአብሔ
ርም ፡ መሳፍንትን ፡ በስነሣላቸው ፡ ጊዜ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ከመስፍኑ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፤ እግዚአ
ብሔርም ፡ ስለሚጎሳአቸውና ፡ ስለሚያስጨን
ቋቸው ፡ በጩኸታቸው ፡ ያዝን ፡ ነበርና ፡ በመ
ስፍኑ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡
አዳናቸው ። መስፍኑ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፲፱ ፡
ይመለሱ ፡ ነበር ÷ ሌሎችንም ፡ አማልክት ፡
በመከተላቸው ፡ እነርሱንም ፡ በማምለካቸውና ፡
ለእነርሱ ፡ በመስገዳቸው ፡ አባቶቻቸው ፡ አድ
ርገውት ፡ ከነበረው ፡ የከፋ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፤
የእልከኝነታቸውን ፡ መንገድና ፡ ሥራቸውን ፡
አልተዉም ፡ ነበር ። የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ፳ ፡
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡—
ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ያዘዝሁትን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ስለ ፡ ተላለፉ ÷ ድምፄንም ፡ ስላልሰሙ ፡
አባቶቻቸውም ፡ እንደ ፡ ጠበቁ ÷ ይሄዱበት ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡
ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ይጠብቁ ፡
ወይም ፡ አይጠብቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስራኤልን ፡
እፈትንባቸው ፡ ዘንድ ÷ ኢያሱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡
ከተዋቸው ፡ አሕዛብ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከፊታቸው ፡ አላወጣም ።
እግዚአብሔርም ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ አስቀረ ÷ ፳፫ ፡
ፈጥኖም ፡ አላወጣቸውም ÷ በኢያሱም ፡ እጅ ፡
አሳልፎ ፡ አልሰጣቸውም ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ከከነዓናውያንም ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ ያላወቁ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡
ትን ፡ እስራኤልን ፡ በእነርሱ ፡ ይፈትናቸው ፡
ዘንድ ÷ በፊትም ፡ ሰልፍን ፡ ያልለመዱ ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ትውልድ ፡ መዋጋትን ፡ ያው
ቁና ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስቀራ
ቸው ፡ አሕዛብ ፡ እነዚህ ፡ናቸው ፡ አምስቱ ፡ የፍ ፫
ልስጥኤማውያን ፡ መኳንንት ÷ ከነዓናውያንም ፡
ሁሉ ÷ ሲዶናውያንም ÷ ከበአልሐርሞንዔም ፡
ተራራ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐማት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡
በሊባኖስ ፡ ተራራ ፡ የሚኖሩትም ፡ ኤዊያውያን ። ፬
እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ፭
ያዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስማታቸው ፡ እንዲታ
ወቅ ፡ እስራኤል ፡ ይፈተኑባቸው ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡
ቀሩ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በከነዓናውያን ፡ ፮
በኬጢያውያንም ፡ በአሞራውያንም ፡ በፈሪዛ
ውያንም ፡ በኤዊያውያንም ፡ በኢያቡሳውያንም ፡
መካከል ፡ ተቀመጡ ። ሴት ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ፯
አገቡአቸው ÷ እነርሱም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸ
ውን ፡ ለወንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ሰጡ ÷ አማል
ክቶቻቸውንም ፡ አመለኩ ።
፰ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ክፉ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ አደረጉ ÷ አምላካ
ቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ረስተው ፡ በኣሊም
ንና ፡ አስታሮትን ፡ አመለኩ ። ስለዚህ ፡ የእግዚአ ፱
ብሔር ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷ በመ
ስጴጦምያ ፡ ንጉሥ ፡ በሩሰርሰቴም ፡ እጅ ፡ አሳ
ልጎ ፡ ሰጣቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለሩሰ
ርሰቴም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ተገዙለት ። የእስራ ፱
ኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፤
እግዚአብሔርም ፡ የሚያድናቸውን ፡ አዳኝ ፡
የካሌብን ፡ የታናሽ ፡ ወንድሙን ፡ የቄኔዝን ፡
ልጅ ፡ ጎቶንያልን ፡ አስነሣላቸው ። የእግዚአ
ብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ መጣ ÷
በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፤ ለሰልፍ ፡
ወጣ ÷ እግዚአብሔርም ፡ የመስጴጦምያን ፡
ንጉሥ ፡ ኩሰርሰቴምን ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጠው ፤ እጁም ፡ በኩሰርሰቴም ፡ ላይ ፡ አሸነ
ፈች ። ምድሪቱም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ዐረፈች ፤
የቄኔዝም ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ሞተ ።
፲፩ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ፤ በእግዚ
አብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የሞዓብን ፡ ንጉሥ ፡ ዔግሎምን ፡ በእስራ
ኤል ፡ ላይ ፡ አበረታባቸው ። የአሞንን ፡ ልጆ
ች ፡ ና ፡ አማሌቅን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሰበሰበ ፤ ሄዶም ፡
እስራኤልን ፡ መታ ÷ ዘንባባም ፡ ያለባትን ፡ ከተማ ፡
ያዙአት ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለሞዓብ ፡
ንጉሥ ፡ ለዔግሎም ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡
ተገዙለት ።
፲፭ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጮኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብንያማዊውን ፡ የጌ
ራን ፡ ልጅ ፡ ናያድን ፡ ግራኙን ፡ ሰው ፡ አዳኝ ፡
አስነሣላቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእ
ርሱ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዔግ
፲፮ ፡ ሎም ፡ ግብር ፡ ላኩ ። ናያድም ፡ ሁለት ፡ አፍ ፡
ያለው ፡ ርዝመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ የሆነ ፡ ሰይፍ ፡
አበጀ ÷ ከልብሱም ፡ በታች ፡ በቀኝ ፡ ጭኑ ፡
፲፯ ፡ በኩል ፡ አደረገው ። ለሞዓብም ፡ ንጉሥ ፡ ለዔ
ግሎም ፡ ግብሩን ፡ አቀረበ ፤ ዔግሎምም ፡ እጅግ ፡
ወፍራም ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ግብሩንም ፡ ማቅረብ ፡
በጨረሰ ፡ ጊዜ ÷ ግብር ፡ የተሸከሙትን ፡ ሰዎች ፡
፲፰ ፡ ሰደደ ። ናያድ ፡ ግን ፡ በጌልገላ ፡ ከነበሩት ፡
ትክል ፡ ድንጋዮች ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡— ንጉሥ ፡
ሆይ ÷ የምሥጢር ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ አለ ፡ ንጉ
ሡም ፡— ዝም ፡ በል ፡ አለ ፤ በዙሪያውም ፡ የቆሙት ፡
ሁሉ ፡ ወጡ ። ናያድም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበ ፤
እርሱም ፡ በሰገነት ፡ ቤት ፡ ለብቻው ፡ ተቀምጦ ፡
ነበር ። ናያድም ፡— የእግዚአብሔር ፡ መልእክት ፡
ለአንተ ፡ አለኝ ፡ አለ ። ከዙፋኑም ፡ ተነሣ ።
፲፱ ፡ ናያድም ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ከቀኝ ፡ ጭኑ ፡
ሰይፉን ፡ ወሰደ ÷ ሆዱንም ፡ ወጋው ፤ የሰይፉም ፡
እጀታው ፡ ደግሞ ፡ ከስለቱ ፡ በኋላ ፡ ገባ ፤ ስቡም ፡
ስለቱን ፡ ከደነው ÷ ሰይፉንም ፡ ከሆዱ ፡ መልሶ ፡
፲፰ ፡ አላወጣውም ፤ በኋላውም ፡ ወጣ ። ናያድም ፡
ወደ ፡ ደርቡ ፡ ወጣ ÷ የሰገነቱንም ፡ ደጅ ፡ ዘግቶ ፡
ቈለፈው ።
፲፱ ፡ ናያድም ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ በረያዎቹ ፡ መጡ ፤
የሰገነቱም ፡ ደጅ ፡ ተቈልፎ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡—
ምናልባት ፡ በሰገነቱ ፡ ውስጥ ፡ ወገቡን ፡ ይሞ
፲፱ ፡ ክር ፡ ይሆናል ፡ አሉ ። እስኪያፍሩም ፡ ድረስ ፡
እጅግ ፡ ዘገዩ ፤ የሰገነቱንም ፡ ደጅ ፡ እንዳልከ
ፈተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መክፈቻውን ፡ ወስደው ፡

ከፈቱ ÷ እነሆም ÷ ጌታቸው ፡ በምድር ፡ ወድቆ ፡
ሞቶም ፡ አገኙት ።
በዘገዩበትም ፡ ጊዜያት ፡ ናያድ ፡ ሸሸ ÷ ትክል ፡ ፳፮ ፡
ድንጋዮቹንም ፡ አለፈ ÷ ወደ ፡ ሴይሮታም ፡ አመ
ለጠ ። በመጣም ፡ ጊዜ ፡ በተራራማው ፡ በኤፍ ፳፯ ፡
ሬም ፡ አገር ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ፤ የእስራኤ
ልም ፡ ልጆች ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ከተራራማው ፡
አገር ፡ ወረዱ ÷ እርሱም ፡ በፊታቸው ፡ ሄደ ።
እርሱም ፡— እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ፳፰ ፡
ሞዓብያንን ፡ በእጃችሁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአ
ልና ፡ ተከተሉኝ ፡ አላቸው ። ተከትለውትም ፡
ወረዱ ÷ ወደ ፡ ሞዓብም ፡ የሚያሻግረውን ፡ የዮ
ርዳኖስን ፡ መሻገሪያ ፡ ያዙ ÷ ማንንም ፡ አላሳለ
ፉም ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከሞዓብ ፡ አሥር ፡ ፳፱ ፡
ሺህ ፡ የሚያህሉትን ፡ ኮልግሶችና ፡ ጽኑዓን ፡
ሁሉ ፡ መቱ ፤ እንጂ ፡ እንኳ ፡ አላመለጠም ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ሞዓብ ፡ ከእስራኤል ፡ እጅ ፡ ፴ ፡
በታች ፡ ተዋረደ ፤ ምድሪቱም ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡
ዐረፈች ።
ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ የዓናት ፡ ልጅ ፡ ሰሜጋር ፡ ፴፩ ፡
ተነሣ ÷ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡
ሰው ፡ በበሬ ፡ መውጊያ ፡ ገደለ ፤ እርሱም ፡
ደግሞ ፡ እስራኤልን ፡ አዳነ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ናያድም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፩ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ሠሩ ። እግዚአብሔርም ፡ በአሶር ፡ በነገሠው ፡ ፪ ፡
በከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ በኢያቢስ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጣቸው ፤ የሠራዊቱም ፡ አለቃ ፡ በአሕዛብ ፡
አሪሶት ፡ የተቀመጠው ፡ ሲሣራ ፡ ነበረ ። የእስ ፫
ራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፤
ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብረት ፡ ሰረገሎች ፡ ነበሩትና ÷
የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡
እጅግ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ ነበር ።
በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ነቢይቱ ፡ የለፊዶት ፡ ሚስት ፡ ፬ ፡
ዲቦራ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ትፈርድ ፡ ነበረች ።
እርስዋም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ፭ ፡
በራማና ፡ በቤቴል ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ የዲቦራ ፡
ዛፍ ፡ ከሚባለው ፡ ከዘንባባው ፡ በታች ፡ ተቀ
ምጣ ፡ ነበር ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እር
ስዋ ፡ ለፍርድ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ። ልክም ፡ ከታ ፮ ፡
ዴስ ፡ ንፍታሌም ፡ የአቢኢኤምን ፡ ልጅ ፡ ባር
ቅን ፡ ጠርታ ፡— የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡— ሄደህ ፡ ወደ ፡ ታቦር ፡ ተራራ ፡ ውጣ ÷
ከአንተም ፡ ጋር ፡ ከንፍታሌምና ፡ ከዛብሎን ፡
ልጆች ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ውሰድ ፤ እኔም ፡ ፯ ፡
የኢያቢስን ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ሲሣራን ፡ ሰረገ
ሎቹንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ወደ ፡
ቂሶን ፡ ወንዝ ፡ እስባለሁ ÷ በእጅህም ፡ አሳልፌ ፡
እሰጠዋለሁ ፡ ብሎ ፡ አላዘዘህምን ? አለችው ።
ባርቅም ፡— አንቺ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ብትሄጂ ፡ እኔ ፡ ፰ ፡
እሄዳለሁ ፡ አንቺ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ባትሄጂ ፡
እኔ ፡ አልሄድም ፡ አላት ። እርስዋም ፡— በእው ፡ ፱ ፡

ነት ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ እሄዳለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሲሣራን ፡ በሴት ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡
ይሰጣልና ፡ በዚህ ፡ በምትሄድበት ፡ መንገድ ፡
ለእንተ ፡ ክብር ፡ አይሆንም ፡ አለችው ። ዲቦ
ራም ፡ ተነሥታ ፡ ከባርቅ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቃዴስ ፡
ሄደች ። ባርቅም ፡ ዛብሎንንና ፡ ንፍታሌምን ፡
ወደ ፡ ቃዴስ ፡ ጠራቸው ፡ አሥር ፡ ሺህም ፡
ሰዎች ፡ ተከትለውት ፡ ወጡ ፤ ዲቦራም ፡ ከአ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ወጣች ።

ቄናዊውም ፡ ሔቤር ፡ ከሙሴ ፡ አማት ፡ ከአ
ባብ ፡ ልጆች ፡ ከቄናውያን ፡ ተለይቶ ፡ ድንኳ
ኑን ፡ በቃዴስ ፡ አጠገብ ፡ በጻዕናይም ፡ እስከ ፡
ነበረው ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ዛፍ ፡ ድረስ ፡ ተከለ ።

የአቢኒኤምም ፡ ልጅ ፡ ባርቅ ፡ ወደ ፡ ታቦር ፡
ተራራ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ለሲሣራ ፡ ነገሩት ። ሲሣ
ራም ፡ ሰረገሎቹን ፡ ሁሉ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብ
ረት ፡ ሰረገሎች ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡
ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ከሐሮሼት ፡ ወደ ፡ ቂሶን ፡ ወንዝ ፡
ሰበሰባቸው ። ዲቦራም ፡ ባርቅን ፡ — እግዚአ
ብሔር ፡ ሲሣራን ፡ በእጅህ ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ
በት ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ ነውና ፡ ተነሣ ! እነሆ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በፊትህ ፡ ወጥቶአል ፡ አለችው ። ባር
ቅም ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ተከትለውት ፡ ከታ
ቦር ፡ ተራራ ፡ ወረደ ። እግዚአብሔርም ፡ ሲሣ
ራን ፡ ሰረገሎቹንም ፡ ሁሉ ፡ ሠራዊቱንም ፡ ሁሉ ፡
ከባርቅ ፡ ፊት ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ አስደነገጣቸው ፤
ሲሣራም ፡ ከሰረገላው ፡ ወርዶ ፡ በእግሩ ፡ ሸሸ ።
ባርቅም ፡ ሰረገሎችንና ፡ ሠራዊቱን ፡ እስከ ፡ አሪ
ሶት ፡ ድረስ ፡ አባረረ ፤ የሲሣራም ፡ ሠራዊት ፡
ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ወደቀ ፤ አንድ ፡ እንኳ ፡
አልቀረም ።

በአሶር ፡ ንጉሥም ፡ በኢያቢስና ፡ በቄናዊው ፡
በሔቤር ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ነበረና ፡ ሲሣራ ፡
በእግሩ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ቄናዊው ፡ ወደ ፡ ሔቤር ፡
ሚስት ፡ ወደ ፡ ኢያዔል ፡ ድንኳን ፡ ደረሰ ።

ኢያዔልም ፡ ሲሣራን ፡ ለመገናኘት ፡ ወጥታ ፡ —
ግባ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ግባ ፤ አትፍራ ፡
አለችው ። ወደ ፡ እርስዋም ፡ ወደ ፡ ድንኳንዋ ፡
ገባ ፡ በመጐናጸፊያዋም ፡ ሸፈነችው ። እር
ሱም ፡ — ጠምቶኛልና ፡ እባክሽ ፡ የምጠጣው ፡
ጥቂት ፡ ውኃ ፡ ስጭኝ ፡ አላት ፤ እርስዋም ፡ የወ
ተቱን ፡ አቁማዳ ፡ ፈትታ ፡ አጠጣችው ፡ ሸፈ
ነችውም ። እርሱም ፡ — ከድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡
ቁሚ ፡ ሰውም ፡ መጥቶ ፡ — በዚህ ፡ ሰው ፡ አለን ?
ብሎ ፡ ቢጠይቅሽ ፡ እንቺ ፡ — የለም ፡ ትዩዋለሽ ፡
አላት ። የሔቤርም ፡ ሚስት ፡ ኢያዔል ፡ የድን
ኳን ፡ ካስማ ፡ ወሰደች ፡ በእጅዋም ፡ መዶሻ ፡
ያዘች ፡ ቀስ ፡ ብላም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበች ፡
በጆሮግንዱ ፡ ካስማውን ፡ ቸነከረች ፤ እርሱም ፡
ደክሞ ፡ አንቀላፍቶ ፡ ነበርና ፡ ካስማው ፡ ወደ ፡
መሬት ፡ ጠለቀ ፡ እርሱም ፡ ሞተ ። እነሆም ፡
ባርቅ ፡ ሲሣራን ፡ ሲያስር ፡ ኢያዔል ፡ ልትገ
ናኘው ፡ ወጥታ ፡ — ና ፡ የምትሻውንም ፡ ሰው ፡
አሳይሃለሁ ፡ አለችው ። ወደ ፡ እርስዋም ፡ ገባ ፡
እነሆም ፡ ሲሣራን ፡ ወድቆ ፡ ሞቶም ፡ አገኘው ፡
ካስማውም ፡ ከጆሮግንዱ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ የከነዓንን ፡ ፹፫
ንጉሥ ፡ ኢያቢስን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡
አዋረደ ። የከነዓንን ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስንም ፡ ፹፬
እስከ ፡ ያጠፉ ፡ ድረስ ፡ በከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ በኢያ
ቢስ ፡ ላይ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ እየበረ
ታች ፡ ሄደች ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

በዚያም ፡ ቀን ፡ ዲቦራና ፡ የአቢኒኤም ፡ ልጅ ፡ ፩
ባርቅ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተቀኙ ፡ —

በእስራኤል ፡ ውስጥ ፡ መሪዎች ፡ ስለ ፡ ፪
መሩ ፡ ፡
ሕዝቡም ፡ ነፍሳቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡
ስለ ፡ ሰጡ ፡ ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።
ነገሥታት ፡ ሆይ ፡ ስሙ ፤ ፫
መኳንንት ፡ ሆይ ፡ እድምጡ ፤
እኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እቀኛለሁ ፡ ፡
ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እዘምራለሁ ።
አቤቱ ፡ ከሴይር ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ ፡ ፬
ከኤዶምያስም ፡ ሜዳ ፡ በተራመድህ ፡ ጊዜ ፡
ምድሪቱ ፡ ተናወጠች ፡ ሰማያቱም ፡ እን
ጠበጠቡ ፤
ደመናትም ፡ ደግሞ ፡ ውኃን ፡ አንጠበጠቡ ።
ተራሮች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ፫
ቀለጡ ፡ ፡
ያም ፡ ሲና ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተነሣ ።
በዓናት ፡ ልጅ ፡ በሰሜጋር ፡ ዘመን ፡ ፡ ፮
በኢያዔል ፡ ዘመን ፡ መንገዶች ፡ ተቋረጡ ፡
መንገደኞች ፡ በስርጥ ፡ መንገድ ፡ ይሄዱ ፡
ነበር ።
አንቺ ፡ ዲቦራ ፡ እስከ ፡ ተነሽ ፡ ድረስ ፡ ፡ ፯
ለእስራኤልም ፡ እናት ፡ ሆነሽ ፡ እስከ ፡ ተነሽ ፡
ድረስ ፡
ኃያላን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አነሱ ፡ ፡
አለቁም ።
አዲሶች ፡ አማልክትን ፡ መረጡ ፤
በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሰልፍ ፡ በበሮች ፡ ሆነ ፤ ፡ ፡ ፰
በአርባ ፡ ሺህ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ጦርና ፡
ጋሻ ፡ አልታየም ።
ልቤ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ አለቆች ፡ ነው ፡ ፡ ፱
በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ነፍሳቸውን ፡ በፈቃ
ዳቸው ፡ ወደ ፡ ሰጡት ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።
በነጫጭ ፡ አህዮች ፡ ላይ ፡ የምትጫኑ ፡ ፡ ፡ ፲
በወላንሳ ፡ ላይ ፡ የምትቀመጡ ፡
በመንገድም ፡ የምትሄዱ ፡ ተናገሩ ።
በማጠጫው ፡ መካከል ፡ ካሉት ፡ ከቀስተ ፡ ፡ ፡ ፲፩
ኞች ፡ ጩኸት ፡ ርቀው ፡
በዚያ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡

በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የግዛቱን ፡ ጽድቅ ፡
ይጫወታሉ ፡
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡
ወደ ፡ በሮች ፡ ወረዱ ።
ንቂ ፡ ንቂ ፡ ዲቦራ ፡ ሆይ ፡ ፡ ፡

ተዉም ፡ ነበር ፡ በግ ፡ ወይም ፡ በሬ ፡ ወይም ፡
፭ አህያ ፡ ቢሆን ፡ አይተዉም ። እንስሶቻቸውንና ፡
ድንኳኖቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በብዛት ፡ እንደ ፡ አን
በጣ ፡ ሆነው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፡ ለእነርሱና ፡ ለግ
መሎቻቸውም ፡ ቍጥር ፡ አልነበራቸውም ፡
ምድሪቱንም ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።
፮ ከምድያምም ፡ የተነሣ ፡ እስራኤል ፡ እጅግ ፡
ተጠቁ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ጮኹ ።

፯ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በምድ
ያም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጮኹ ፡
፰ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡
ነቢይ ፡ ላከ ፥ እርሱም ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ አም
ላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ከግ
ብፅ ፡ ምድር ፡ አወጣኋችሁ ፥ ከባርነትም ፡ ቤት ፡
፱ አስለቀቅኋችሁ ፤ ከግብፃውያንም ፡ እጅ ፥ ከሚ
ጨቁኑአችሁም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ አዳንኋችሁ ፥ ከፊ
ታችሁም ፡ አሳደድኋቸው ፥ አገራቸውንም ፡
፲ ሰጠኋችሁ ፤ እናንተንም ፦ እኔ ፡ አምላካችሁ ፡
እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ በምድራቸው ፡ የተቀመ
ጣችሁባቸውን ፡ የአሞራውያንን ፡ አማልክት ፡
አትፍሩ ፡ እልኋችሁ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ድምፄን ፡ አልሰማችሁም ።

፲፩ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ በዖ
ፍራ ፡ በላችው ፡ ለአቢዔዝራዊው ፡ ለኢዮአስ ፡
በነበረችው ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀ
መጠ ፤ ልጁም ፡ ጌዴዎን ፡ ከምድያማውያን ፡
ለመሸሽግ ፡ በወይን ፡ መጥመቂያው ፡ ውስጥ ፡
፲፪ ስንዴ ፡ ይወቃ ፡ ነበር ። የእግዚአብሔርም ፡
መልአክ ፡ ለእርሱ ፡ ተገለጠ ፦ አንተ ፡ ጽኑዕ ፡
ኃያል ፡ ሰው ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡
፲፫ ነው ፡ አለው ። ጌዴዎንም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥
እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ለምን ፡ ደረሰብን ? አበቶቻችንስ ፦ እግ
ዚአብሔር ፡ ከግብፅ ፡ አውጥቶናል ፡ ብለው ፡
ይነግሩን ፡ የነበረ ፡ ተአምራቱ ፡ ወዴት ፡ አለ ?
አሁን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ትቶናል ፥ በምድ
ያማውያንም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶናል ፡ አለው ።
፲፬ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፦
በዚህ ፡ በጕልበትህ ፡ ሂድ ፥ እስራኤልንም ፡ ከም
ድያም ፡ እጅ ፡ አድን ፤ እነሆ ፥ ልኬሃለሁ ፥ አለው ።
፲፭ እርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስራኤልን ፡ በምን ፡
አድናለሁ ? መኔ ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ ከሁሉ ፡
ይልቅ ፡ የተጠቃ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡
፲፮ የሁሉ ፡ ታናሽ ፡ ነኝ ፡ አለው ። እግዚአብሔ
ርም ፦ በእርግጥ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ እሆናለሁ ፥
ምድያምንም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አድርገህ ፡
፲፯ ትመታለህ ፡ አለው ። እርሱም ፦ በእንተ ፡
ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ ካገኘሁ ፡ የምትናገረኝም ፡ እንተ ፡
፲፰ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ምልክት ፡ አሳየኝ ፤ ወደ ፡ እን
ተም ፡ እስከመለስ ፡ ድረስ ፥ ቍርባኔንም ፡ አም
ጥቼ ፡ እስከቀርብልህ ፡ ድረስ ፥ እባክህ ፡ ከዚህ ፡
አትላወስ ፡ አለው ። እርሱም ፦ እስከትመ
፲፱ ለስ ፡ ድረስ ፡ እቆያለሁ ፡ አለ ። ጌዴዎን ፡ ገባ ፡
የፍየሉንም ፡ ጠበት ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያም ፡
ዱቄት ፡ የቂጣ ፡ እንጎቻ ፡ አዘጋጀ ፤ ሥጋውን ፡
በሴማት ፡ አኖረ ፥ መረቁንም ፡ በምንቸት ፡ ውስጥ ፡
አደረገ ፥ ሁሉንም ፡ ይዞ ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡
አቀረበለት ። ፳ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፦
ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡ እንጎቻ ፡ ወስደህ ፡
በዚህ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አኑር ፥ መረቁንም ፡ አፍ
ስስ ፡ አለው ። እንዲሁም ፡ አደረገ ። ፳፩ የእግዚ
አብሔርም ፡ መልአክ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ የበት
ሩን ፡ ጫፍ ፡ ዘርግቶ ፡ ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡
እንጎቻ ፡ አስነካ ፤ እሳትም ፡ ከድንጋዩ ፡ ውስጥ ፡
ወጥቶ ፡ ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡ እንጎቻ ፡ በላ ።
የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከዓይኑ ፡ ተሰወረ ።
ጌዴዎንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡
፳፪ ሆነ ፡ አየ ፤ ጌዴዎንም ፦ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡
ሆይ ፥ ወዮልኝ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ አይቻለሁና ፡ አለ ። ፳፫ እግዚአብሔ
ርም ፦ ሰላም ፡ ለእንተ ፡ ይሁን ፤ አትፍራ ፡
አትሞትም ፡ አለው ። ፳፬ ጌዴዎንም ፡ በዚያ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ ስሙንም ፦
እግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። እር
ሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለአቢዔዝራውያን ፡
በምትሆነው ፡ በዖፍራ ፡ አለ ።

፳፭ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፦ የአባት
ህን ፡ በሬ ፥ ሰባት ፡ ዓመት ፡ የሆነውን ፡ ሁለተ
ኛውን ፡ በሬ ፥ ውሰድ ፥ የአባትህ ፡ የሆነው
ንም ፡ የበአል ፡ መሠዊያ ፡ አፍርስ ፥ በእርሱም ፡
ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐፀድ ፡ ቍረጥ ፡
፳፮ በዚያም ፡ ኮረብታ ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ለአምላክህ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ አሳምረህ ፡ ሥራ ፡
ሁለተኛውንም ፡ በሬ ፡ ውሰድ ፥ በዚያም ፡ በቁ
ረጥኸው ፡ በማምለኪያ ፡ ዐፀዱ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡
የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርብ ፡ አለው ።
፳፯ ጌዴዎንም ፡ ከባሪያዎቹ ፡ አሥር ፡ ሰዎችን ፡ ወስዶ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፤ የአባቱን ፡
ቤተ ፡ ሰብቶ ፡ የከተማውንም ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡
ይህን ፡ በቀን ፡ ለማድረግ ፡ አልቻለም ፥ ነገር ፡
ግን ፡ በሌሊት ፡ አደረገው ።

፳፰ የከተማውም ፡ ሰዎች ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥
እነሆም ፥ የበአል ፡ መሠዊያ ፡ ፈርሶ ፥ በዙሪ
ያው ፡ ያለውም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐፀድ ፡ ተቈ
ርጦ ፥ በተሠራውም ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሁለተ
ኛው ፡ በሬ ፡ ተሠውቶ ፡ አገኙት ። ፳፱ እርስ ፡ በር
ሰዎውም ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ?
ተብባሉ ። በጠየቁና ፡ በመረመሩም ፡ ጊዜ ፡ ፦
ይህን ፡ ነገር ፡ ያደረገ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ ጌዴ
ዎን ፡ ነው ፡ አሉ ። ፴ የከተማውም ፡ ሰዎች ፡
ኢዮአስን ፦ የበአልን ፡ መሠዊያ ፡ አፍርሶአ
ልና ፥ በዙሪያውም ፡ ያለውን ፡ የማምለኪያ ፡
ዐፀድ ፡ ቈርጦአልና ፡ እንዲሞት ፡ ልጅህን ፡
አውጣ ፡ አሉት ። ፴፩ ኢዮአስም ፡ እርሱን ፡ የተ
ቃወሙትን ፡ ሁሉ ፦ ለበአል ፡ ትምዋገቱለታ
ላችሁን ? ወይስ ፡ እርሱን ፡ ታድናላችሁን ?
የሚምዋገትለት ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ይሙት ፤

እርሱ ፡ አምላክ ፡ ከሆነ ፡ መሠዊያውን ፡ ካፈረ
ሰው ፡ ጋር ፡ ለራሱ ፡ ይምዋገት ፡ አላቸው ።
፴፪ ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፦ መሠዊያውን ፡ አፍ
ርሶአልና ፡ በአል ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይምዋገት ፡
ብሎ ፡ ጌዴዎንን ፦ ይሩብአል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።
፴፫ ምድያማውያንም ፡ አማሌቃውያንም ፡ ሁሉ ፡
የምሥራቅም ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ተሰበ
ሰቡ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገሩ ፥ በኢይዝራኤ
፴፬ ልም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፈሩ ። የእግዚአብሔርም ፡ መን
ፈስ ፡ በጌዴዎን ፡ ገባበት ፥ እርሱም ፡ ቀንደ ፡
መለከቱን ፡ ነፋ ፤ የአቢዔዝርም ፡ ሰዎች ፡ ተጠ
፴፭ ርተው ፡ በኋላው ፡ ተከተሉት ። ወደ ፡ ምና
ሴም ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ መልክተኞችን ፡ ሰደደ ፡
እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ተጠርተው ፡ በኋላው ፡ ተከ
ተሉት ፡ መልክተኞችንም ፡ ወደ ፡ አሴርና ፡ ወደ ፡
ዛብሎን ፡ ወደ ፡ ንፍታሌምም ፡ ሰደደ ፥ እነር
ሱም ፡ ሊገናኙአቸው ፡ ወጡ ።

፴፮ ጌዴዎንም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እንደ ፡ ተና
ገርህ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡
ታድን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፥ እነሆ ፥ በእውድማው ፡
ላይ ፡ የተብዘተ ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ እናሳለሁ ፤ በጠ
ጕሩ ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ጠል ፡ ቢሆን ፥ በምድሩም ፡
ሁሉ ፡ ደረቅ ፡ ቢሆን ፥ እንደ ፡ ተናገርህ ፡ የእስ
ራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ እንድታድና
ቸው ፡ አውቃለሁ ፡ አለ ። ፴፯ እንዲሁም ፡ ሆነ ፤ ብነ
ጋውም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ጠጕሩንም ፡ ጨመ
ቀው ፥ ከጠጕሩም ፡ የተጨመቀው ፡ ጠል ፡ ቆሬ ፡
ሙሉ ፡ ውኃ ፡ ሆነ ። ፴፰ ጌዴዎንም ፡ እግዚአብሔ
ርን ፦ እኔ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስናገር ፡ አት
ቈጣኝ ፤ እኔ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጠጕሩ ፡
እባክህ ፡ ልፈትን ፡ አሁንም ፡ በጠጕሩ ፡ ብቻ ፡
፴፱ ላይ ፡ ደረቅ ፡ ይሁን ፥ በምድሩም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ጠል ፡ ይሁን ፡ አለው ። ፵ እግዚአብሔርም ፡
በዚያ ፡ ሌሊት ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ በጠጕሩ ፡
ብቻ ፡ ላይ ፡ ደረቅ ፡ ነበረ ፥ በምድሩም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ጠል ፡ ነበረ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ ጌዴዎን ፡ የተባለውም ፡ ይሩብአል ፡ ከእር
ሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ማልደው ፡
ተነሡ ፥ በሐሮድ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብም ፡ ሰፈሩ ፤
የምድያምም ፡ ሰፈር ፡ ከእነርሱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡
በኩል ፡ በሞሬ ፡ ኮረብታ ፡ አጠገብ ፡ በሸለቆው ፡
ውስጥ ፡ ነበረ ።
፪ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ከእንተ ፡
ጋር ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በዝቶአል ፤ ስለዚህ ፡
እስራኤል ፦ እጄ ፡ አዳነኝ ፡ ብሎ ፡ እንዳይታበ
ይብኝ ፤ እኔ ፡ ምድያምን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፌ ፡
፫ አልሰጣቸውም ። አሁንም ፡ እንግዲህ ፦ የፈራ ፡
የደነገጠም ፡ ከገለዓድ ፡ ተራራ ፡ ተነሥቶ ፡ ይመ
ለስ ፡ ብለህ ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ አውጅ ፡ አለው ።
ከሕዝቡም ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ተመለሱ ፤
አሥርም ፡ ሺህ ፡ ቀሩ ።
፬ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ሕዝቡ ፡ ገና ፡
ብዙ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ አውርዳቸው ፥ በዚ
ያም ፡ እፈትናቸዋለሁ ፤ እኔም ፦ ይህ ፡ ከአ
ንተ ፡ ጋር ፡ ይሄዳል ፡ እኔም ፦ ይህ ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡
አይሂድ ፡ የምለው ፡ እርሱ ፡ አይሄድም ፡ አለው ።
፭ ሕዝቡንም ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ አወረደ ። እግዚአብ
ሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ውሻ ፡ እንደሚጠጣ ፡
ውኃ ፡ በምላሱ ፡ የሚጠጣውን ፡ ሁሉ ፥ እርሱን ፡
ለብቻው ፡ አድርገው ፤ እንዲሁም ፡ ሊጠጣ ፡
በጕልበቱ ፡ የሚንበረከከውን ፡ ሁሉ ፡ ለብቻው ፡
አድርገው ፡ አለው ። ፮ በእጃቸውም ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡
አፋቸው ፡ አድርገው ፡ የጠጡት ፡ ቍጥር ፡
ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ፤ የቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡
ውኃ ፡ ሊጠጡ ፡ በጕልበታቸው ፡ ተንበረከኩ ።
፯ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ በእጃቸው ፡
ውኃ ፡ በጠጡት ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ አድ
ናችኋለሁ ፥ ምድያማውያንንም ፡ በእጅህ ፡ አሳ
ልፌ ፡ እሰጥሃለሁ ፤ የቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
ግን ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይመለሱ ፡ አለው ።
፰ የሕዝቡንም ፡ ስንቅና ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ በእ
ጃቸው ፡ ወሰዱ ፤ የቀሩትንም ፡ የእስራኤል ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ሰደዳቸው ፥
ሦስቱን ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡
ጠበቃቸው ፤ የምድያምም ፡ ሰፈር ፡ ከእርሱ ፡
በታች ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።
፱ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፦ በእ
ጅህ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻቸዋለሁና ፡ ተነሥተህ ፡
ወደ ፡ ሰፈር ፡ ውረድ ። ፲ አንተም ፡ ለመውረድ ፡
ብትፈራ ፡ አንተ ፡ ከሰሌህ ፡ ከፉራ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡
ሰፈሩ ፡ ውረድ ፤ የሚናገሩትንም ፡ ትሰማለህ ፡ ፲፩
ከዚያም ፡ ብኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ትወርድ ፡ ዘንድ ፡
እጅህ ፡ ትበረታለች ፡ አለው ። እርሱና ፡ ሰሌው ፡
ፉራ ፡ በሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ሰልፈ
ኞች ፡ ወረዱ ። ፲፪ ብዛታቸውም ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡
የሆነ ፡ ምድያማውያንና ፡ አማሌቃውያን ፡ የም
ሥራቅም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡
ሰፍረው ፡ ነበር ፤ የግመሎቻቸውም ፡ ብዛት ፡
ቍጥር ፡ እንደሌለው ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡
አሸዋ ፡ ነበረ ። ፲፫ ጌዴዎንም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ሕልምን ፡ ለባልንጀራው ፡ ሲያ
ጫውት ፦ እነሆ ፥ ሕልም ፡ አለምሁ ፤ እነሆም ፥
እንዲት ፡ የገብስ ፡ እንጉቻ ፡ ወደ ፡ ምድያም ፡
ሰፈር ፡ ተንከባልላ ፡ ወረደች ፥ ወደ ፡ ድንኳኑም ፡
ደርሳ ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ መታችው ፥ ገለበ
ጠችውም ፥ ድንኳኑም ፡ ተጋደመ ፡ ይል ፡ ነበር ።
፲፬ ባልንጀራውም ፡ መልሶ ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእስ
ራኤል ፡ ሰው ፡ ከኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ ከጌዴዎን ፡
ሰይፍ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ እግዚአብ
ሔር ፡ ምድያምንና ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡
አሳልፎ ፡ ሰጥቶአል ፡ አለው ።
፲፭ ጌዴዎንም ፡ ሕልሙንና ፡ ትርጓሜውን ፡ በሰማ ፡ ፲፮
ጊዜ ፡ ሰገደ ፤ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ ሰፈር ፡ ተመ
ልሶ ፦ እግዚአብሔር ፡ የምድያምን ፡ ሠራዊት ፡
በእጃችሁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአልና ፡ ተነሡ ፡ አለ ።

ሥስቱንም ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ከፈ
ላቸው ፥ በሁሉም ፡ እጅ ፡ ቀንደ ፡ መለከትና ፡
በዥ ፡ ማሰሮ ፥ በማሰሮውም ፡ ውስጥ ፡ ችቦ ፡ ሰጠ ። ፲፮
እርሱም ፡ — እኔን ፡ ተመልከቱ ፥ እንዲሁም ፡
አድርጉ ፤ እነሆም ፥ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ በደረ
ስሁ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እንደ ማደርግ ፡ እንዲሁ ፡ እና
ንተ ፡ አድርጉ ። ፲፯ እኔ ፡ ከእኔም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡
ሁሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ስንነፋ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡
በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከታችሁን ፡
ንፉ ፡ — ለእግዚአብሔርና ፡ ለጌዴዎን ፡ በሉ ፡
አላቸው ።

ጌዴዎንም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ መቶ ፡
ሰዎች ፡ በመከከለኛው ፡ ትጋት ፡ ትጋቱም ፡ በተ
ጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ መጡ ፤
ቀንደ ፡ መለከቶችንም ፡ ነፉ ፥ በእጃቸውም ፡
ያ፡ የነበሩትን ፡ ማሰሮች ፡ ሰባበሩ ። ፳ ሦስቱም ፡ ወገ
ኖች ፡ ቀንደ ፡ መለከቶችን ፡ ነፉ ፥ ማሰሮችንም ፡
ሰበሩ ፥ በግራ ፡ እጃቸውም ፡ ችቦችን ፥ በቀኝ ፡
እጃቸውም ፡ ቀንደ ፡ መለከቶችን ፡ ይዘው ፡ እየ
ነፉ ፡ — የእግዚአብሔርና ፡ የጌዴዎን ፡ ሰይፍ ፡
ብለው ፡ ጮኹ ። ሁሉም ፡ በየቦታው ፡ በሰ
ፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ቆመ ፤ ሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ ሮጠ ፥
ጮኸ ፥ ሸሸም ። ፳፪ ሦስቱንም ፡ መቶ ፡ ቀንደ ፡
መለከቶች ፡ ነፉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የሰውን ፡
ሁሉ ፡ ሰይፍ ፡ በባልንጀራውና ፡ በሠራዊቱ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ ሠራዊቱም ፡ በጽሬራ ፡
በኩል ፡ እስከ ፡ ቤትሺጣ ፡ ድረስ ፡ በጠባት ፡
አጠገብ ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ አቤልምሖላ ፡
ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ሸሸ ። ፳፫ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡
ከንፍታሌምና ፡ ከአሴር ፡ ከምናሴም ፡ ሁሉ ፡
ተሰብስበው ፡ ምድያምን ፡ አሳደዱ ።

ጌዴዎንም ፡ — ምድያምን ፡ ለመገናኘት ፡
ውረዱ ፥ እስከ ፡ ቤትባራ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡
ውኃ ፥ ዮርዳኖስን ፥ ያዙባቸው ፡ ብሎ ፡ መልክ
ተኞችን ፡ በኤፍሬም ፡ ወዳለው ፡ ተራራማ ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰደደ ። የኤፍሬም ፡ ሰዎችም ፡
ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እስከ ፡ ቤትባራ ፡ ድረስ ፡
ውኃውን ፥ ዮርዳኖስን ፥ ያዙ ። ፳፭ የምድያምን ፡
ሁለቱን ፡ መኳንንት ፡ ሔሬብንና ፡ ዜብን ፡ ያዙ ፤
ሔሬብንም ፡ በሔሬብ ፡ ዓለት ፡ አጠገብ ፡ ገደ
ሉት ፥ ዜብንም ፡ በዜብ ፡ መጥመቂያ ፡ ላይ ፡ ገደ
ሉት ፤ ምድያምንም ፡ አሳደዱ ፥ የሔሬብንና ፡
የዜብንም ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡
ማዶ ፡ ወደ ፡ ጌዴዎን ፡ መጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ የኤፍሬም ፡ ሰዎች ፡ — ይህ ፡ ያደረግህብን ፡
ምንድር ፡ ነው ? ምድያምን ፡ ለመዋጋት ፡ በወ
ጣህ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ አልጠራኸንም ? አሉት ።
ጽኑ ፡ ጥልም ፡ ተጣሉት ። እርሱም ፡ — እኔ ፡
ከደረግሁት ፡ እናንተ ፡ ያደረጋችሁት ፡ አይበል
ጥምን ? የኤፍሬም ፡ ወይን ፡ ቃርሚያ ፡ ከአቢ
ዔዝር ፡ ወይን ፡ መከር ፡ አይሻልምን ? ፫ እግዚአ
ብሔር ፡ የምድያምን ፡ መኳንንት ፡ ሔሬብንና ፡
ዜብን ፡ በእጃችሁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶአቸዋል ፤
እናንተ ፡ ያደረጋችሁትን ፡ የሚመስል ፡ እኔ ፡
ምን ፡ ማድረግ ፡ እችል ፡ ኖሮአል ? አላቸው ።
ይህን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ቁጣቸው ፡ በረደ ።

ጌዴዎንም ፡ ከሦስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ፬
ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ደርሶ ፡ ተሻገረ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡
ቢደክሙ ፡ ያሳድዱ ፡ ነበር ። ፭ የሱኮትንም ፡
ሰዎች ፡ — የምድያምን ፡ ነገሥታት ፡ ዛብዔል
ንና ፡ ስልማናን ፡ ሳሳድድ ፥ ደክመዋልና ፡ እኔን ፡
ለተከተሉ ፡ ሕዝብ ፡ እንጀራ ፥ እባካችሁ ፥ ስጡ ፡
አላቸው ። ፮ የሱኮትም ፡ አለቆች ፡ — እኛ ፡ ለሠ
ራዊትህ ፡ እንጀራ ፡ እንድንሰጥ ፡ የዛብዔልና ፡
የስልማና ፡ እጅ ፡ አሁን ፡ በእጅህ ፡ ነውን ? አሉ ።
፯ ጌዴዎንም ፡ — እግዚአብሔር ፡ ዛብዔልንና ፡ ስል
ማናን ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሲሰጣ ፡ እኔ ፡ በም
ድረ ፡ በዓ ፡ አሾህና ፡ በሱርንችት ፡ ሥጋችሁን ፡
እገርፋለሁ ፡ አለ ። ፰ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጵኒኤል ፡
ወጣ ፥ ለጵኒኤልም ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁ ፡ አላቸው ፤
የጵኒኤልም ፡ ሰዎች ፡ የሱኮት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡
መለሱ ፡ መለሱለት ። እርሱም ፡ የጵኒኤልን ፡
ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ — በደኅና ፡ በተመለስኩ ፡ ጊዜ ፡
ይህን ፡ ግንብ ፡ አፈርሰዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገ
ራቸው ።

፱ ዛብዔልና ፡ ስልማናም ፡ ከሠራዊቶቻቸው ፡
ጋር ፡ በቀርቀር ፡ ነበሩ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዝዙ ፡
መቶ ፡ ሀያ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ወድቀው ፡ ነበርና ፡
ከምሥራቅ ፡ ሰዎች ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ የቀሩ ፡
አምራ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ፱
ጌዴዎንም ፡ የድንኳን ፡ ተቀማጮች ፡ ባሉበት ፡
መንገድ ፡ በናባሀና ፡ በዮግብሃ ፡ በምሥራቅ ፡
በኩል ፡ ወጣ ፡ ሠራዊቱም ፡ ተዘልሎ ፡ ነበርና ፡
ሠራዊቱን ፡ መታ ። ፲ ዛብዔልና ፡ ስልማናም ፡
ሸሹ ፤ እርሱም ፡ አሳደዳቸው ፥ ሁለቱንም ፡ የም
ድያም ፡ ነገሥታት ፡ ዛብዔልንና ፡ ስልማናን ፡
ያዘ ፥ ሠራዊቱንም ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጠ ።

፲፩ የኢዮአስ ፡ ልጅም ፡ ጌዴዎን ፡ ከሔሬስ ፡ ዳገት ፡
ከሰልፍ ፡ ተመለሰ ። ፲፪ ከሱኮትም ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡
ብላቴና ፡ ይዘ ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም ፡ የሱኮትን ፡
አለቆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰባ ፡ ሳባት ፡ ሰዎች ፡
ጻፈለት ። ፲፫ ወደ ፡ ሱኮትም ፡ ሰዎች ፡ መጥቶ ፡ —
ለደከሙት ፡ ሰዎችህ ፡ እንጀራ ፡ እንሰጥ ፡ ዘንድ ፡
የዛብዔልና ፡ የስልማና ፡ እጅ ፡ አሁን ፡ በእጅህ ፡
ነውን ? ብላችሁ ፡ የተላገዳችሁብኝ ፥ ዛብዔልና ፡
ስልማና ፡ እነሆ ፥ አለ ። ፲፭ የከተማይቱንም ፡ ሽማ
ግሌዎች ፡ ያዘ ፥ የምድረ ፡ በዳንም ፡ እሾህና ፡
ሱርንችት ፡ ወስዶ ፡ የሱኮትን ፡ ሰዎች ፡ ገረፋ
ቸው ። ፲፮ የጵኒኤልንም ፡ ግንብ ፡ አፈረሰ ፥ የከተ
ማይቱንም ፡ ሰዎች ፡ ገደላቸው ።

፲፯ ዛብዔልንና ፡ ስልማናን ፡ — በታቦር ፡ የገደላ
ችኋቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ? አላ
ቸው ። እነርሱም ፡ — እንደ ፡ አንተ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ፥
አንተንም ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ፡ መልካቸውም ፡
እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ መልክ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡
መለሱለት ። ፲፰ እርሱም ፡ — የእናቴ ፡ ልጆች ፡
ወንድሞቼ ፡ ነበሩ ፡ አድናችኋቸው ፡ ቢሆን ፡
ኖሮ ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! እኔ ፡ አልገድላ
ችሁም ፡ ነበር ፡ አለ ። ፲፱ በዙፋንም ፡ ዩቴርን ፡ —
ተነሥተህ ፡ ግደላቸው ፡ አለው ፤ ብላቴናው ፡
ግን ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ነበረና ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ ሰይ
ፉን ፡ አልመዘዘም ። ፳ ዛብዔልና ፡ ስልማናም ፡ —
የሰው ፡ ኃይሉ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ነውና ፡ አንተ ፡
ተነሥተህ ፡ ውደቅብን ፡ አሉት ። ጌዴዎንም ፡
ተነሥቶ ፡ ዛብዔልንና ፡ ስልማናን ፡ ገደለ ፥ በግ
መሎቻቸውም ፡ አንገት ፡ የነበሩትን ፡ ሥሉሌ
ዎች ፡ ማረከ ።

፳፩ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ጌዴዎንን ፡ — ከምድ
ያም ፡ እጅ ፡ አድነኸናልና ፡ አንተ ፡ ልጅህም ፡
የልጅ ፡ ልጅህም ፡ ደግሞ ፡ ግዙን ፡ አሉት ። ጌዴ
ዎንም ፡ — እኔ ፡ አልገዛችሁም ፥ ልጄም ፡ አይገ
ዛችሁም ፤ እግዚአብሔር ፡ ይገዛችኋል ፡ አላ
ቸው ። ፳፪ እስማኤላውያንም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የወ
ርቅ ፡ ጉትቻ ፡ ነበራቸውና ፡ ጌዴዎን ፡ — ሁላ
ችሁ ፡ ከምርኮአችሁ ፡ ጉትቻችሁን ፡ እንድትሰ
ጡኝ ፡ አለምና ፡ ችኋለሁ ፡ አላቸው ። ፳፫ እነርሱም ፡ —
ፈቅደን ፡ እንሰጥሃለን ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።
መጐናጸፊያም ፡ አነጠፉ ፥ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ የም
ርኮውን ፡ ጉትቻ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ጣለ ። ፳፬ የለመነ
ውም ፡ የወርቅ ፡ ጉትቻ ፡ ሚዛኑ ፥ ከአምባሩ ፥
ከድሪውም ፥ የምድያምም ፡ ነገሥታት ፡ ከለበ
ሱት ፡ ከቀዩ ፡ ቀሚስ ፥ በግመሎቻቸውም ፡ አን
ገት ፡ ከነበሩት ፡ ሥሉሌዎች ፡ ሌላ ፥ ሺህ ፡ ሰባት ፡
መቶ ፡ ሰቅል ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ። ፳፭ ጌዴዎንም ፡ ኤፋድ ፡
አድርጎ ፡ አሠራው ፥ በከተማውም ፡ በዖፍራ ፡
አኖረው ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ተከትሎ ፡ አመ
ነዘረበት ፡ ለጌዴዎንና ፡ ለቤቱም ፡ ወጥመድ ፡
ሆነ ። ፳፮ ምድያምም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተቀ
ረደ ፥ ራሳቸውንም ፡ ዳግመኛ ፡ አላነሡም ። በጌ
ዴዎንም ፡ ዕድሜ ፡ ምድሪቱ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡
ዐረፈች ።

፳፯ የኢዮአስም ፡ ልጅ ፡ ይሩብአል ፡ ሄዶ ፡ በቤቱ ፡
ተቀመጠ ። ፳፰ ለጌዴዎንም ፡ ብዙ ፡ ሚስቶች ፡ ነበ
ሩትና ፡ ከወገቡ ፡ የወጡ ፡ ሰባ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።
፳፱ በሴኬምም ፡ የነበረችው ፡ ቁባቱ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡
ወለደችለት ፥ ስሙንም ፡ አቢሜሌክ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ። ፴ የኢዮአስም ፡ ልጅ ፡ ጌዴዎን ፡ በመ
ልካም ፡ ሽምግልና ፡ ሞተ ፥ በአቢዔዝራውያ
ንም ፡ ከተማ ፡ በዖፍራ ፡ በነበረችው ፡ በአባቱ ፡
በኢዮአስ ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ።

፴፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ጌዴዎን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፥ በአሊሎንም ፡
ተከተሉ ፡ አመነዘሩ ፡ በአልብረትንም ፡ አም
ላካቸው ፡ አደረጉ ። ፴፪ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
በዙሪያቸው ፡ ከነበሩት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡
እጅ ፡ ያዳናቸውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ አላሰቡትም ። እርሱም ፡ ለእስራኤል ፡
በጎ ፡ ነገርን ፡ ሁሉ ፡ እንዳደረገ ፡ መጠን ፥ እነርሱ ፡
ለጌዴዎን ፡ ለይሩብአል ፡ ቤት ፡ ወረታ ፡ አላደረ
ጉም ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ የይሩብአል ፡ ልጅ ፡ አቢሜሌክም ፡ ወደ ፡
ሴኬም ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ወንድሞች ፡ ሄደ ፥ ለእ
ነርሱም ፡ ለእናቱ ፡ አባት ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡
ሁሉ ፡ — በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ — ፪
ሰባ ፡ የሆኑት ፡ የይሩብአል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ቢገ
ዙአችሁ ፡ ወይስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢገዛችሁ ፡
ምን ፡ ይሻላችኋል ? ብላችሁ ፡ ንገሩአቸው ፡
ብዬ ፡ እለምናችኋለሁ ፤ ደግሞ ፡ እኔ ፡ የአጥን
ታችሁ ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችሁ ፡ ቍራጭ ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ አስቡ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ፫ የእና
ቱም ፡ ወንድሞች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡
እርሱ ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ ተናገሩ ፤
እነርሱም ፡ — እርሱ ፡ ወንድማችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡
አቢሜሌክን ፡ ለመከተል ፡ ልባቸውን ፡ አዘነበ
ሉት ። ፬ ከበአልብሪትም ፡ ቤት ፡ ሰባ ፡ ብር ፡
ሰጡት ፤ በዚያም ፡ አቢሜሌክ ፡ ምናምንቴዎች
ንና ፡ ወሮበሎችን ፡ ቀጠረበት ፥ እነርሱም ፡ ተከ
ተሉት ። ፭ ወደ ፡ አበቱም ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ያፍራ ፡
ሄደ ፤ ሰባ ፡ የሆኑትን ፡ የይሩብአልን ፡ ልጆች ፡
ወንድሞቹን ፡ በአንድ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አረዳ
ቸው ፤ ትንሹ ፡ የይሩብአል ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡
ግን ፡ ተሸሽጎ ፡ ነበርና ፡ ተረፈ ። ፮ የሴኬምም ፡
ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቤትሚሎም ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፥
ሄደውም ፡ በሴኬም ፡ በዓምዱ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡
በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ አቢሜሌክን ፡ አነገሡ ።

፯ ይህንም ፡ ነገር ፡ ለኢዮአታም ፡ በነገሩት ፡
ጊዜ ፥ ሄዶ ፡ በገሪዛን ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆመ ፥
ድምፁንም ፡ አንሥቶ ፡ ጮኸ ፥ እንዲህም ፡ አላ
ቸው ፡ — የሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡
እንዲሰማችሁ ፡ ስሙኝ ። ፰ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዛፎች ፡
በላያቸው ፡ ንጉሥ ፡ ሊያነግሡ ፡ ሄዱ ፡ ወይራ ፡
ውንም ፡ — በእኛ ፡ ላይ ፡ ንገሥ ፡ አሉት ። ፱ ወይ
ራው ፡ ግን ፡ — እግዚአብሔርና ፡ ሰዎች ፡ በእኔ ፡
የሚከበሩበትን ፡ ቅባቴን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡
እንድሰፍፍ ፡ ልሂድ ? አላቸው ። ፲ ዛፎችም ፡ በለ
ሱን ፡ — መጥተህ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ።
፲፩ በለሱ ፡ ግን ፡ — ጣፋጭነቴንና ፡ መልካሙን ፡
ፍሬዬን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ እንድሰፍፍ ፡
ልሂድ ? አላቸው ። ፲፪ ዛፎችም ፡ ወይኑን ፡ — መጥ
ተህ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ። ፲፫ ወይኑም ፡ —
እግዚአብሔርንና ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡
የወይን ፡ ጠጄን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ እንድ
ሰፍፍ ፡ ልሂድ ? አላቸው ። ፲፬ ዛፎችም ፡ ሁሉ ፡ እሾ
ህን ፡ — መጥተህ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ።
፲፭ እሾሁም ፡ ዛፎችን ፡ — በእውነት ፡ እኔን ፡ በእና
ንተ ፡ ላይ ፡ ታነግሡኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኑ ፡ ከጥላዬ ፡
በታች ፡ ተጠጉ ። እንዲሁም ፡ በይሆን ፡ እሳት ፡
ከእሾህ ፡ ይውጣ ፥ የሊባኖስንም ፡ ዝግባ ፡ ያቃ
ጥል ፡ አላቸው ። ፲፮ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ አቢሜሌ
ክን ፡ በማንገሣችሁ ፡ እውነትንና ፡ ቅንነትን ፡
አድርጋችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፥ ለይሩብአልም ፡ ለቤ
ቱም ፡ በጎ ፡ አድርጋችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፥ እንዳደ

ረገውም ፡ መጠን ፡ ለእርሱ ፡ የተገበውን ፡ አድ
፲፯ ፡ ርጋችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ አባቴ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡
ተጋድሎ ፡ ነበርና ÷ ከምድያምም ፡ እጅ ፡ ሊያ
ድናችሁ ፡ ነፍሱን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶ ፡
፲፰ ፡ ነበርና ÷ እናንተም ፡ ዛሬ ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ተነሥ
ታችኋልና ÷ ሰባ ፡ የሆኑትን ፡ ልጆቹንም ፡ በአ
ንድ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አርዳችኋልና ÷ ወንድማ
ችሁም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የባሪያይቱን ፡ ልጅ ፡ አቤሜ
ሌክን ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እንግሣችኋ
፲፱ ፡ ልና ÷ እንግዲህ ፡ ለይሩብአልና ፡ ለቤቱ ፡ እው
ነትንና ፡ ቅንነትን ፡ ዛሬ ፡ አድርጋችሁ ፡ እንደ
ሆነ ÷ በአቤሜሌክ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ÷ እርሱ ፡
፳ ፡ ደግሞ ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡ ይበለው ፤ እንዲህ ፡
በይሆን ፡ ግን ፡ ከአቤሜሌክ ፡ እሳት ፡ ይውጣ ÷
የሴኬምንም ፡ ሰዎች ፡ ቤትሚሎንም ፡ ይብላ ፤
ከሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ ከቤትሚሎም ፡ እሳት ፡
፳፩ ፡ ይውጣ ÷ አቤሜሌክንም ፡ ይብላ ። ኢዮአታ
ምም ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ÷ ወንድሙንም ፡ አቤ
ሜሌክን ፡ ፈርቶ ፡ ወደ ፡ ብኤር ፡ ሄደ ፡ ÷ በዚ
ያም ፡ ተቀመጠ ።
፳፪ ፡ አቤሜሌክም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡
፳፫ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እግዚአብሔር ፡ በአቤሜሌክና
በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክፉን ፡ መንፈስ ፡
ሰደደ ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ በአቤሜሌክ ፡
፳፬ ፡ ላይ ፡ ተንኰል ፡ አደረጉ ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ÷
በሰባ ፡ የይሩብአል ፡ ልጆቹ ፡ ላይ ፡ የተደረ
ገው ፡ ዓመፅ ፡ እንዲመጣ ÷ ደማቸውም ፡ በገደ
ላቸው ፡ በወንድማቸው ፡ በአቤሜሌክ ፡ ላይ ÷
ወንድሞቹንም ፡ እንዲገድል ፡ እጆቹን ፡ ባጸኑ
አቸው ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡
፳፭ ፡ ነው ። የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ በተራሮች ፡ ራስ ፡
ላይ ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አደረጉ ÷ መንገድ ፡ ተላ
ላፊዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ይዘርፉ ፡ ነበር ፤ አቤሜሌ
ክም ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ ሰማ ።
፳፮ ፡ የአቤድም ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋር ፡
መጥቶ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ገባ ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡
፳፯ ፡ ታመኑበት ። ወደ ፡ እርሻውም ፡ ወጡ ፡ ወይና
ቸውንም ፡ ለቀሙ ÷ ጠመቁትም ÷ የደስታም ፡
በዓል ፡ አደረጉ ፤ ወደ ፡ አምላካቸውም ፡ ቤት ፡
ገቡ ÷ በሉም ፡ ጠጡም ÷ አቤሜሌክንም ፡
፳፰ ፡ ሰደቡ ። የአቤድም ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፡ — የምንገ
ዛለት ፡ አቤሜሌክ ፡ ማን ፡ ነው ? ሴኬምስ ፡ ምን
ድር ፡ ነው ? እርሱ ፡ የይሩብአል ፡ ልጅ ፣ አይደለ
ምን ? ዜቡልም ፡ የእርሱ ፡ ሹም ፡ አይደለምን ?
ለሴኬም ፡ አባት ፡ ለኤሞር ፡ ሰዎች ፡ ተገዙ ፡
፳፱ ፡ ስለ ፡ ምንስ ፡ ለዚህ ፡ እንገዛለን ? ይህ ፡ ሕዝብ ፡
ከእጄ ፡ በታች ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አቤሜሌክን ፡
አሳድደው ፡ ነበር ፡ አለ ። አቤሜሌክንም ፡ — ሠራዊትህን ፡ አብዝተህ ፡ ና ÷ ውጣ ፡ አለው ።
፴ ፡ የከተማይቱ ፡ ገዥ ፡ ዜቡልም ፡ የአቤድን ፡
ልጅ ፡ የገዓልን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡
፴፩ ፡ ተቈጣ ። እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አቤሜሌክ ፡
በተንኰል ፡ መልክተኞች ፡ ላከ ፡ — እነሆ ÷ የአ
ቤድ ፡ ልጅ ፡ ገዓልና ፡ ወንድሞቹ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡
መጥተዋል ÷ በእንተም ፡ ላይ ፡ ከተማይቱን ፡ አሽ
ፍተዋል ። ፴፪ ፡ አሁንም ፡ እንተና ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡
ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ በሌሊት ፡ ተነሡ ÷ በሜዳም ፡
ሽምቅ ፤ ነገም ፡ ፀሐይ ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ማል
፴፫ ፡ ደህ ፡ ተነሣ ÷ በከተማይቱም ፡ ላይ ፡ ውደቅ
በት ፣ እነሆም ÷ እርሱና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡
ሕዝብ ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ እጅህ ፡
እንዳገኘች ፡ አድርግበት ።
፴፬ ፡ አቤሜሌክና ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ በሌሊት ፡ ተነሡ ÷ በሴኬምም ፡ አቅራ
ቢያ ፡ በአራት ፡ ወገን ፡ ሽመቁበት ። የአቤድም ፡
፴፭ ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፡ ወጥቶ ፡ በከተማይቱ ፡ በር ፡ አደባ
ባይ ፡ ቆመ ፤ አቤሜሌክና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡
ሕዝብ ፡ ከሽመቁበት ፡ ስፍራ ፡ ተነሡ ። ገዓልም ፡
ሕዝቡን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዜቡልን ፡ — እነሆ ፡ ከተ
ራሮች ፡ ራስ ፡ ሕዝብ ፡ ይወርዳል ፡ አለው ።
፴፮ ፡ ዜቡልም ፡ — ሰዎች ፡ የሚመስለውን ፡ የተራሮ
ችን ፡ ጥላ ፡ ታያለህ ፡ አለው ። ገዓልም ፡ ደግሞ ፡ —
፴፯ ፡ እነሆ ÷ ሕዝብ ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ይወርዳል ፡
አንድም ፡ ወገን ፡ በምዶንጊም ፡ በአድበሩ ፡
ዛፍ ፡ መንገድ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
፴፰ ፡ ዜቡልም ፡ — እንገዛለት ፡ ዘንድ ፡ አቤሜሌክ ፡
ማን ፡ ነው ? ያልህበት ፡ አፍህ ፡ አሁን ፡ የት ፡
አለ ? ይህ ፡ የናቅኸው ፡ ሕዝብ ፡ አይደለምን ?
አሁንም ፡ ወጥተህ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፡
፴፱ ፡ አለው ። ገዓልም ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡
ወጣ ÷ ከአቤሜሌክም ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ። ፵ ፡ አቤሜ
ሌክም ፡ አሳደደው ፡ በፊቱም ፡ ሸሸ ÷ እስከ ፡
በሩም ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ ብዙዎች ፡ ተጐድ
ተው ፡ ወደቁ ።
፴፩ ፡ አቤሜሌክም ፡ በአሩማ ፡ ተቀመጠ ፤ ዜቡ
ልም ፡ ገዓልንና ፡ ወንድሞቹን ፡ በሴኬም ፡ እንዳ
ይኖሩ ፡ አሳደዳቸው ። ፵፪ ፡ በነጋውም ፡ ሕዝቡ ፡
ወደ ፡ እርሻ ፡ ወጡ ፤ አቤሜሌክም ፡ ሰማ ።
ሕዝቡንም ፡ ወስዶ ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ከፈላ
ቸው ÷ በሜዳም ፡ ሽመቅ ፡ ተመለከተም ÷
፵፫ ፡ እነሆም ÷ ሕዝቡ ፡ ከከተማ ፡ ወጡ ÷ ተነሣባቸ
ውም ፡ መታቸውም ። ፵፬ ፡ አቤሜሌክም ፡ ከእር
ሱም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ወገኖች ፡ ተጣደፉ ፡ በከተ
ማይቱም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ቆሙ ፤ ሁለቱም ፡
ወገኖች ፡ በእርሻው ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ሮጡባቸው ÷ መቱአቸውም ። ፵፭ ፡ አቤሜሌ
ክም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ ከከተማይቱ ፡ ጋር ፡
ተዋጋ ፤ ከተማይቱንም ፡ ይዞ ፡ በእርስዋ ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሕዝብ ፡ ገደለ ፤ ከተማይቱንም ፡ አፈረሰ ÷
ጨውም ፡ ዘራበት ።
፵፮ ፡ በሴኬምም ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤልብሪት ፡
ቤት ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። ፵፯ ፡ አቤሜሌ
ክም ፡ በሴኬም ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሰማ ።
አቤሜሌክና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉትም ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰልሞን ፡ ተራራ ፡ ወጡ ፤ አቤሜ
ሌክም ፡ በእጁ ፡ መጥረቢያ ፡ ወስዶ ፡ የዛፉን ፡ ቅር

ንጫፍ ፡ ቈረጠ ÷ አንሥቶም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡
አደረገው ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ —
እኔ ፡ ሰደርግ ፡ ያያችሁትን ÷ እናንተም ፡ ፈጥና
ችሁ ፡ እኔ ፡ እንዳደረግሁ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።
፵፱ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ እያንዳንዳቸው ፡
የዛፉን ፡ ቅርንጫፎች ፡ ቈረጡ ÷ አቤሜሌክንም ፡
ተከተሉለው ፡ በምሽጉ ፡ ዙሪያ ፡ አኖሩአቸው ÷
ምሽጉንም ፡ በላያቸው ፡ አቃጠሉት ፤ የሴኬ
ምም ፡ ግንብ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡
ሺህ ፡ የሚያህሉ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሞቱ ።
፶ ፡ አቤሜሌክም ፡ ወደ ፡ ቴቤስ ፡ መጣ ÷ ቴቤስ
፶፩ ፡ ንም ፡ ከብበ ፡ ያዛት ። በከተማይቱም ፡ ውስጥ ፡
ብርቱ ፡ ግንብ ፡ ነበረ ÷ የከተማይቱም ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ወንዱና ፡ ሴቱ ፡ ሁሉ ፡ ወደዚያ ፡ ሸሹ ፤
ደጁንም ፡ በኋላቸው ፡ ዘጉ ÷ ወደ ፡ ግንቡም ፡
፶፪ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጡ ። አቤሜሌክም ፡ ወደ ፡
ግንቡ ፡ ቀርቦ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ÷ በእሳትም ፡ ሊያ
፶፫ ፡ ቃጥለው ፡ ወደ ፡ ግንቡ ፡ ደጅ ፡ ደረሰ ። እንዲ
ትም ፡ ሴት ፡ በአቤሜሌክ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የወፍጮ ፡
መጅ ፡ ጣለችበት ÷ እናቱንም ፡ ሰበረችው ።
፶፬ ፡ እርሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ጋሻ ፡ ዝግሪውን ፡ ጠርቶ ፡ —
እኔን ፡ — ሴት ፡ ገደለችው ፡ እንዳይሉ ፡ ሰይፍህን ፡
መዝዘህ ፡ ግደለኝ ፡ አለው ፡ ጕልማሳውም ፡
፶፭ ፡ ወጋው ÷ ሞተም ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡
አቤሜሌክ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳ
፶፮ ፡ ንዱ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ። እንዲሁ ፡
ሰባ ፡ ወንድሞቹን ፡ በመግደል ፡ አቤሜሌክ ፡
በአባቱ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ክፋት ፡ እግዚአብ
፶፯ ፡ ሔር ፡ መለሰበት ። እግዚአብሔርም ፡ የሴኬ
ምን ፡ ሰዎች ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡
መለሰባቸው ፡ የይሩብአልም ፡ ልጅ ፡ የኢዮአ
ታም ፡ እርግማን ፡ ደረሰባቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ፡ ከአቤሜሌክም ፡ በኋላ ፡ ከይሳነር ፡ ነገድ ፡
የሆነ ፡ የዱዳ ፡ ልጅ ፡ የፎሖ ፡ ልጅ ፡ ቶላ ፡ እስራ
ኤል ፡ ለማዳን ፡ ተነሣ ፤ በተራራማውም ፡ በኤ
ፍሬም ፡ አገር ፡ በለችው ፡ በሳምር ፡ ተቀምጦ ፡
፪ ፡ ነበር ። በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ዐያ ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ ፈረደ ፤ ሞተም ÷ በሳምርም ፡ ተቀበረ ።
፫ ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ገለዓዳዊው ፡ ኢያዕር ፡
ተነሣ ÷ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ዐያ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡
፬ ፡ ፈረደ ። በሠላሳ ፡ የአህያ ፡ ግልገሎች ፡ ይቀመጡ ፡
የነበሩ ፡ ሠላሳ ፡ ልጆችም ፡ ነበሩት ፡ ለእነርሱም ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡
የተባሉ ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ያሉ ፡ ሠላሳ ፡ ከተ
፭ ፡ ሞች ፡ ነበሩአቸው ። ኢያዕርም ፡ ሞተ ÷ በቃ
ሞንም ፡ ተቀበረ ።
፮ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ፡ በአሊ
ምንና ፡ አስታሮትን ፡ የሶርያንም ፡ አማልክት ÷
የሲዶናንም ፡ አማልክት ÷ የሞዓብንም ፡ አማ
ልክት ÷ የአሞንንም ፡ ልጆች ፡ አማልክት ÷
የፍልስጥኤማውያንንም ፡ አማልክት ፡ አመለኩ ፡
እግዚአብሔርንም ፡ ተዉ ÷ አላመለኩትም ።
፯ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላ ፡
ነደደ ÷ በፍልስጥኤማውያንና ፡ በአሞን ፡ ልጆ ፡
፰ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ። በዚያም ፡ ዓመት ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሥቃይ ፡ አበዙባቸው ፤
በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በአሞራውያን ፡ አገር ፡ በገ
ለዓድ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ተጋፉአቸው ።
የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ከይሁዳ ፡ ከብንያምና ፡ ከአ
፱ ፡ ፍሬም ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡ ሊዋጋ ፡ ዮርዳኖ
ስን ፡ ተሻገሩ ፤ እስራኤልም ፡ እጅግ ፡ ተጨነቁ ።
፱ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ — አምላካችንን ፡
ትተን ፡ በኢሊ ፡ ምን ፡ አምልከናልና ፡ አንተን ፡ በ
ደለና ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ። ፡
እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አላ
ፍ ፡ ፡ ፡

ፍ፡ ምድር ፡ ለማምጣት ፡ ሄዱ ። ዮፍታሔንም ፡— ፍ ÷ ከአሞን ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንድንዋጋ ፡ አለ
፲ ፡ ቃችን ፡ ሁን ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡ የገለዓ ፡ ቃችን ፡ ሁን ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡ የገለዓ
ድን ፡ ሽማግሌዎች ፡— የጠላቶሁኝ ፡ ከአባቴም ፡ ድን ፡ ሽማግሌዎች ፡— የጠላቶሁኝ ፡ ከአባቴም ፡
ቤት ፡ ያሳደዳችሁኝ ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምን ? ቤት ፡ ያሳደዳችሁኝ ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምን ?
አሁን ፡ በተጨነቃችሁ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ አሁን ፡ በተጨነቃችሁ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ወደ ፡
ፍ ፡ እኔ ፡ መጣችሁ ? አላቸው ። የገለዓድም ፡ ሽማ ፍ ፡ እኔ ፡ መጣችሁ ? አላቸው ። የገለዓድም ፡ ሽማ
ግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፡— ከእኛ ፡ ጋር ፡ እንድት ፡ ግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፡— ከእኛ ፡ ጋር ፡ እንድት ፡
ወጣ ÷ ከአሞንም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንድትዋጋ ÷ ወጣ ÷ ከአሞንም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንድትዋጋ ÷
ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ተመልሰን ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ተመልሰን ፡
መጣን ፡ በገለዓድም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አለ መጣን ፡ በገለዓድም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አለ
ፍ ፡ ቃችን ፡ ተሆናለህ ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡ የገ ፍ ፡ ቃችን ፡ ተሆናለህ ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡ የገ
ለዓድን ፡ ሽማግሌዎች ፡— ከአሞን ፡ ልጆች ፡ ለዓድን ፡ ሽማግሌዎች ፡— ከአሞን ፡ ልጆች ፡
ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ብትመልሱኝ ÷ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ብትመልሱኝ ÷
እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣቸው ÷ እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣቸው ÷
፲ ፡ እኔ ፡ አለቃችሁ ፡ እሆናለሁን ? አላቸው ። የገ ፲ ፡ እኔ ፡ አለቃችሁ ፡ እሆናለሁን ? አላቸው ። የገ
ለዓድም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፡— እግዚ ለዓድም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፡— እግዚ
አብሔር ፡ በመካከላችን ፡ ምስክር ፡ ይሁን ፡ በእ አብሔር ፡ በመካከላችን ፡ ምስክር ፡ ይሁን ፡ በእ
ርግጥ ፡ እንደ ፡ ቃልህ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉት ። ርግጥ ፡ እንደ ፡ ቃልህ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉት ።
፲፩ ፡ ዮፍታሔም ፡ ከገለዓድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ፲፩ ፡ ዮፍታሔም ፡ ከገለዓድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡
ሄደ ÷ ሕዝቡም ፡ በላያቸው ፡ ራስና ፡ አለቃ ፡ አደ ሄደ ÷ ሕዝቡም ፡ በላያቸው ፡ ራስና ፡ አለቃ ፡ አደ
ረጉት ፡ ዮፍታሔም ፡ ቃሉን ፡ ሁሉ ፡ በእግዚ ረጉት ፡ ዮፍታሔም ፡ ቃሉን ፡ ሁሉ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ በምጽጳ ፡ ተናገረ ። አብሔር ፡ ፊት ፡ በምጽጳ ፡ ተናገረ ።
፲፪ ፡ ዮፍታሔም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡— ፲፪ ፡ ዮፍታሔም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡—
አገሬን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የምትመጣ ፡ አገሬን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የምትመጣ ፡
አንተ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለህ ? ብሎ ፡ መል አንተ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለህ ? ብሎ ፡ መል
፲፫ ፡ ከተኞችን ፡ ላከ ። የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫ ፡ ከተኞችን ፡ ላከ ። የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡
የዮፍታሔን ፡ መልከተኞች ፡— እስራኤል ፡ ከግ የዮፍታሔን ፡ መልከተኞች ፡— እስራኤል ፡ ከግ
ብፅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአርኖን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ብፅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአርኖን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ያቦቅና ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ ምድሬን ፡ ያቦቅና ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ ምድሬን ፡
ስለ ፡ ወሰደ ፡ ነው ! አሁንም ፡ በሰላም ፡ መል ስለ ፡ ወሰደ ፡ ነው ! አሁንም ፡ በሰላም ፡ መል
፲፬ ፡ ሱልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ዮፍታሔም ፡ ፲፬ ፡ ሱልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ዮፍታሔም ፡
ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ መልክተኞችን ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ መልክተኞችን ፡
፲፭ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ላከ ÷ እንዲህም ፡ አለው ፡— ዮፍ ፲፭ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ላከ ÷ እንዲህም ፡ አለው ፡— ዮፍ
ታሔ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እስራኤል ፡ የሞዓብን ፡ ታሔ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እስራኤል ፡ የሞዓብን ፡
ምድር ፡ የአሞንንም ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ አልወ ምድር ፡ የአሞንንም ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ አልወ
፲፮ ፡ ሰደም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከግብፅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ÷ ፲፮ ፡ ሰደም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከግብፅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ÷
እስራኤልም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ እስራኤልም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡
ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ÷ ወደ ፡ ቃዴስም ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ÷ ወደ ፡ ቃዴስም ፡
፲፯ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ÷ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ ፡ ፲፯ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ÷ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ ፡
ንጉሥ ፡— በምድርህ ፡ እንዳልፍ ÷ እባክህ ፡ ፍቀ ንጉሥ ፡— በምድርህ ፡ እንዳልፍ ÷ እባክህ ፡ ፍቀ
ድልኝ ፡ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፤ የኤዶም ድልኝ ፡ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፤ የኤዶም
ያስም ፡ ንጉሥ ፡ አልሰማም ። እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ያስም ፡ ንጉሥ ፡ አልሰማም ። እንዲሁም ፡ ወደ ፡
ሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ÷ እርሱም ፡ አልፈቀደም ። ሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ÷ እርሱም ፡ አልፈቀደም ።
፲፰ ፡ እስራኤልም ፡ በቃዴስ ፡ ተቀመጠ ። በምድረ ፲፰ ፡ እስራኤልም ፡ በቃዴስ ፡ ተቀመጠ ። በምድረ ፡
በዳም ፡ በኩል ፡ ሄዶ ÷ የኤዶምያስንና ፡ የሞዓ በዳም ፡ በኩል ፡ ሄዶ ÷ የኤዶምያስንና ፡ የሞዓ
ብንም ፡ ምድር ፤ ዙሩ ፤ ከሞዓብ ፡ ምድርም ፡ ብንም ፡ ምድር ፤ ዙሩ ፤ ከሞዓብ ፡ ምድርም ፡
በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ መጡ ፡ በአርኖንም ፡ ማዶ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ መጡ ፡ በአርኖንም ፡ ማዶ ፡
ሰፈሩ ፤ አርኖንም ፡ የሞዓብ ፡ ድንበር ፡ ነበረና ፡ ሰፈሩ ፤ አርኖንም ፡ የሞዓብ ፡ ድንበር ፡ ነበረና ፡
፲፱ ፡ የሞዓብን ፡ ድንበር ፡ አላለፉም ። እስራኤልም ፡ ፲፱ ፡ የሞዓብን ፡ ድንበር ፡ አላለፉም ። እስራኤልም ፡
ወደ ፡ አሞራዊው ፡ ወደ ፡ ሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሞራዊው ፡ ወደ ፡ ሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡
ወደ ፡ ሴዎን ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፡ እስራኤ ወደ ፡ ሴዎን ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፡ እስራኤ
ልም ፡ ፡ በምድርህ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ስፍራችን ÷ ልም ፡ ፡ ፡ በምድርህ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ስፍራችን ÷
፳ ፡ እባክህ ፡ ፡ ሳልፈን ፡ አለው ። ሴዎንም ፡ እስራ ፳ ፡ እባክህ ፡ ፡ ሳልፈን ፡ አለው ። ሴዎንም ፡ እስራ
ኤል ፡ በድንበሩ ፡ እንዲያልፍ ፡ አላመነውም ፡ ኤል ፡ በድንበሩ ፡ እንዲያልፍ ፡ አላመነውም ፡
ነበር ! ነገር ፡ ግን ፡ ሴዎን ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰበ ነበር ! ነገር ፡ ግን ፡ ሴዎን ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰበ
ሰበ ÷ በያሀጽም ፡ ሰፈረ ÷ ከእስራኤልም ፡ ጋር ፡ ሰበ ÷ በያሀጽም ፡ ሰፈረ ÷ ከእስራኤልም ፡ ጋር ፡
ተዋጋ ። የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብ ፳፩ ፡ ተዋጋ ። የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብ ፳፩ ፡
ሔር ፡ ሴዎንንና ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ሔር ፡ ሴዎንንና ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡
እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ÷ መቱአቸውም ፤ እስራኤ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ÷ መቱአቸውም ፤ እስራኤ
ልም ፡ በዚያ ፡ ምድር ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩ ልም ፡ በዚያ ፡ ምድር ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩ
ትን ፡ የአሞራውያንን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ወረሰ ። ትን ፡ የአሞራውያንን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ወረሰ ።
፳፪ ፡ ከአርኖንም ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ድረስ ፡ ከምድረ ፡ ከአርኖንም ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ድረስ ፡ ከምድረ ፡ ፳፪ ፡
በዳውም ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ የአሞራ በዳውም ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ የአሞራ
ውያንን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ወረሱ ። የእስራኤ ውያንን ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ወረሱ ። የእስራኤ
ልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ከእ ልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ከእ
ስራኤል ፡ ፊት ፡ አሞራውያንን ፡ አስወገደ ፤ አን ስራኤል ፡ ፊት ፡ አሞራውያንን ፡ አስወገደ ፤ አን
ተም ፡ ምድሩን ፡ ትወርሳለህን ? አምላክህ ፡ ተም ፡ ምድሩን ፡ ትወርሳለህን ? አምላክህ ፡
፳፫ ፡ ካሞሽ ፡ የሚሰጥህን ፡ አትወርስምን ? እኛም ፡ ፳፫ ፡ ካሞሽ ፡ የሚሰጥህን ፡ አትወርስምን ? እኛም ፡
አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊታችን ፡ ያስ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊታችን ፡ ያስ
ወጣቸውን ፡ የእነርሱን ፡ ምድር ፡ እንወርሳለን ። ወጣቸውን ፡ የእነርሱን ፡ ምድር ፡ እንወርሳለን ።
ወይስ ፡ ከሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ከሴፎር ፡ ልጅ ፡ ከባ ወይስ ፡ ከሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ከሴፎር ፡ ልጅ ፡ ከባ ፳፬ ፡
ላቅ ፡ አንተ ፡ ትሻላለህን ? በውኑ ፡ እርሱ ፡ ከእ ላቅ ፡ አንተ ፡ ትሻላለህን ? በውኑ ፡ እርሱ ፡ ከእ
ራኤልን ፡ ከቶ ፡ ተጣላውን ? ወይስ ፡ ተዋጋውን ? ራኤልን ፡ ከቶ ፡ ተጣላውን ? ወይስ ፡ ተዋጋውን ?
እስራኤልም ፡ በሐሴቦንና ፡ በመንደሮችዋ ÷ በአ እስራኤልም ፡ በሐሴቦንና ፡ በመንደሮችዋ ÷ በአ
ሮዔርና ፡ በመንደሮችዋ ÷ በአርኖንም ፡ አቅራ ፳፭ ፡ ሮዔርና ፡ በመንደሮችዋ ÷ በአርኖንም ፡ አቅራ ፳፭ ፡
ቢያ ፡ ባሉት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ቢያ ፡ ባሉት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡
ዓመት ፡ ተቀምጦ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ÷ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ዓመት ፡ ተቀምጦ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ÷ በዚያ ፡ ዘመን ፡
ስለ ፡ ምን ፡ አልወሰዳችኋቸውም ፡ ነበር ? እኔ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልወሰዳችኋቸውም ፡ ነበር ? እኔ ፡ ፳፮ ፡
አልበደልሁህም ÷ አንተ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ አልበደልሁህም ÷ አንተ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡
እየተዋጋህ ፡ በድለኸኛል ፤ ፈራጁ ፡ እግዚአብ እየተዋጋህ ፡ በድለኸኛል ፤ ፈራጁ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡ ሔር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡
መካከል ፡ ዛሬ ፡ ይፍረድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዮፍታሔ ፡ ፳፯ ፡ መካከል ፡ ዛሬ ፡ ይፍረድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዮፍታሔ ፡ ፳፯ ፡
የላከበትን ፡ ቃል ፡ የአሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ የላከበትን ፡ ቃል ፡ የአሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡
አልሰማም ። አልሰማም ።
የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በዮፍታሔ ፡ ፳፱ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በዮፍታሔ ፡ ፳፱ ፡
ላይ ፡ መጣ ፤ እርሱም ፡ ገለዓድንና ፡ ምናሴን ፡ ላይ ፡ መጣ ፤ እርሱም ፡ ገለዓድንና ፡ ምናሴን ፡
አለፈ ÷ በገለዓድም ፡ ያለውን ፡ ምጽጳን ፡ አለፈ ÷ አለፈ ÷ በገለዓድም ፡ ያለውን ፡ ምጽጳን ፡ አለፈ ÷
ከምጽጳም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ አለፈ ። ዮፍ ከምጽጳም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ አለፈ ። ዮፍ ፴ ፡
ታሔም ፡— ዘእውነት ፡ የአሞንን ፡ ልጆች ፡ ታሔም ፡— ዘእውነት ፡ የአሞንን ፡ ልጆች ፡
በእጄ ፡ አሳልፈህ ፡ ብትሰጠኝ ÷ ከአሞን ፡ ልጆች ፡ በእጄ ፡ አሳልፈህ ፡ ብትሰጠኝ ÷ ከአሞን ፡ ልጆች ፡ ፴፩ ፡
ዘንድ ፡ በደኅና ፡ በተመለስሁ ፡ ጊዜ ÷ ሊገናኘኝ ፡ ዘንድ ፡ በደኅና ፡ በተመለስሁ ፡ ጊዜ ÷ ሊገናኘኝ ፡
ከቤቴ ፡ ደጅ ፡ የሚወጣው ፡ ማንኛውም ፡ ለእግ ከቤቴ ፡ ደጅ ፡ የሚወጣው ፡ ማንኛውም ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ይሆናል ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥ ዚአብሔር ፡ ይሆናል ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥ
ዋዕት ፡ አቀርበዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዋዕት ፡ አቀርበዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ስእለት ፡ ተሳለ ። ዮፍታሔም ፡ ሊዋጋቸው ፡ ስእለት ፡ ተሳለ ። ዮፍታሔም ፡ ሊዋጋቸው ፡ ፴፪ ፡
ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ አለፈ ÷ እግዚአብሔ ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ አለፈ ÷ እግዚአብሔ
ርም ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ። ከአሮዔ ፡ ፴፫ ፡ ርም ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ። ከአሮዔ ፡
ርም ፡ እስከ ፡ ሚኒትና ፡ እስከ ፡ አቤልከራሚም ፡ ርም ፡ እስከ ፡ ሚኒትና ፡ እስከ ፡ አቤልከራሚም ፡
ድረስ ፡ ዘያ ፡ ከተሞችን ፡ በታላቅ ፡ አገዳደል ፡ ድረስ ፡ ዘያ ፡ ከተሞችን ፡ በታላቅ ፡ አገዳደል ፡
መታቸው ። የአሞንም ፡ ልጆች ፡ በእስራኤል ፡ መታቸው ። የአሞንም ፡ ልጆች ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ ፊት ፡ ተዋረዱ ። ልጆች ፡ ፊት ፡ ተዋረዱ ።
ዮፍታሔም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ፴፬ ፡ ዮፍታሔም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ፴፬ ፡
መጣ ÷ እነሆም ፡ ልጁ ፡ ከበሮ ፡ ይዛ ፡ እየዘፈነች ፡ መጣ ÷ እነሆም ፡ ልጁ ፡ ከበሮ ፡ ይዛ ፡ እየዘፈነች ፡
ልትገናኘው ፡ ወጣች ፤ ለእርሱም ፡ አንዲት ፡ ልትገናኘው ፡ ወጣች ፤ ለእርሱም ፡ አንዲት ፡
ብቻ ፡ ነበረች ፤ ከእርስዋም ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡ ብቻ ፡ ነበረች ፤ ከእርስዋም ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡
ወይም ፡ ሴት ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አልነበረውም ። እር ወይም ፡ ሴት ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አልነበረውም ። እር ፴፭ ፡
ስዋንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡— አወይ ፡ ስዋንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀድዶ ፡— አወይ ፡

ልጄ ፡ ሆይ ! ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አፌን ፡ ልጄ ፡ ሆይ ! ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አፌን ፡
ከፍቻለሁና ÷ ከዚያውም ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ አል ከፍቻለሁና ÷ ከዚያውም ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ አል
ችልምና ፡ በጣም ፡ አዋረድኸኝ ፡ አስጨነቅኸ ችልምና ፡ በጣም ፡ አዋረድኸኝ ፡ አስጨነቅኸ
፴፮ ፡ ኝም ፡ አላት ። እርስዋም ፡— አባቴ ፡ ሆይ ÷ አፍ ፴፮ ፡ ኝም ፡ አላት ። እርስዋም ፡— አባቴ ፡ ሆይ ÷ አፍ
ህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከከፈትህ ÷ እግዚአብ ህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከከፈትህ ÷ እግዚአብ
ሔር ፡ በጠላቶችህ ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ሔር ፡ በጠላቶችህ ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡
ተበቅሎልሃልና ፡ በአፍህ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፡ ተበቅሎልሃልና ፡ በአፍህ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፡
፴፯ ፡ አድርግብኝ ፡ አለችው ። አባትዋንም ፡— ይህ ፴፯ ፡ አድርግብኝ ፡ አለችው ። አባትዋንም ፡— ይህ ፡
ነገር ፡ ይደረግልኝ ፡ ከዚህ ፡ ሄጄ ፡ በተራሮች ፡ ነገር ፡ ይደረግልኝ ፡ ከዚህ ፡ ሄጄ ፡ በተራሮች ፡
ላይ ፡ እንደወጣና ፡ እንደወርድ ÷ ከባልንጀሮ ላይ ፡ እንደወጣና ፡ እንደወርድ ÷ ከባልንጀሮ
ቼም ፡ ጋር ፡ ለድንግልናዬ ፡ እንዳለቅስ ፡ ሁለት ፡ ቼም ፡ ጋር ፡ ለድንግልናዬ ፡ እንዳለቅስ ፡ ሁለት ፡
፴፰ ፡ ወር ፡ አሰናብተኝ ፡ አለችው ። እርሱም ፡— ፴፰ ፡ ወር ፡ አሰናብተኝ ፡ አለችው ። እርሱም ፡—
ሂጂ ፡ አለ ። ሁለት ፡ ወርም ፡ አሰናበታት ፤ ከባ ሂጂ ፡ አለ ። ሁለት ፡ ወርም ፡ አሰናበታት ፤ ከባ
ልንጀሮችዋም ፡ ጋር ፡ ሄዳች ፡ በተራሮችም ፡ ልንጀሮችዋም ፡ ጋር ፡ ሄዳች ፡ በተራሮችም ፡
ላይ ፡ ለድንግልናዋ ፡ አለቀሰች ። ሁለትም ፡ ላይ ፡ ለድንግልናዋ ፡ አለቀሰች ። ሁለትም ፡
ወር ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አባትዋ ፡ ተመ ወር ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አባትዋ ፡ ተመ
ለሰች ÷ እንደ ፡ ተሳለችውም ፡ ስእለት ፡ አደረገ ለሰች ÷ እንደ ፡ ተሳለችውም ፡ ስእለት ፡ አደረገ
በት ፡ እርስዋም ፡ ወንድ ፡ አላወቀችም ፡ ነበር ። ፴፱ ፡ በት ፡ እርስዋም ፡ ወንድ ፡ አላወቀችም ፡ ነበር ። ፴፱ ፡
የእስራኤልም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በዓመት ፡ በዓ የእስራኤልም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በዓመት ፡ በዓ
መት ፡ እየሄዱ ፡ የገለዓዳዊውን ፡ የዮፍታሔን ፡ መት ፡ እየሄዱ ፡ የገለዓዳዊውን ፡ የዮፍታሔን ፡
ልጅ ፡ በዓመት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሾ ፡ እንዲያ ልጅ ፡ በዓመት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሾ ፡ እንዲያ
ወጡ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ሆነ ። ወጡ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ሆነ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ፡ የኤፍሬም ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ÷ ወደ ፡ ጻፎ ፩ ፡ የኤፍሬም ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ÷ ወደ ፡ ጻፎ
ንም ፡ ተሻግረው ፡ ዮፍታሔን ፡— ከአሞን ፡ ንም ፡ ተሻግረው ፡ ዮፍታሔን ፡— ከአሞን ፡
ልጆች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ስታልፍ ፡ ከአንተ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ስታልፍ ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ እንድንሄድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠራኸንም ? ጋር ፡ እንድንሄድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠራኸንም ?
ቤትህን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ እናቃጥለዋ ቤትህን ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ እናቃጥለዋ
፪ ፡ ለን ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡— ከአሞን ፡ ልጆች ፡ ፪ ፡ ለን ፡ አሉት ። ዮፍታሔም ፡— ከአሞን ፡ ልጆች ፡
ጋር ፡ ለእኔና ፡ ለሕዝቤ ፡ ጽኑ ፡ ጠብ ፡ ነበረን ፡ ጋር ፡ ለእኔና ፡ ለሕዝቤ ፡ ጽኑ ፡ ጠብ ፡ ነበረን ፡
በጠራኋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ አላዳናች በጠራኋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ አላዳናች
፫ ፡ ሁኝም ። እንዳላዳናችሁኝም ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ ፫ ፡ ሁኝም ። እንዳላዳናችሁኝም ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡
ነፍሴን ፡ በእጄ ፡ አድርጌ ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡ ነፍሴን ፡ በእጄ ፡ አድርጌ ፡ በአሞን ፡ ልጆች ፡
ላይ ፡ አለፍሁ ÷ እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳ ላይ ፡ አለፍሁ ÷ እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳ
ልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ ለምንስ ፡ ዛሬ ፡ ልትወጉኝ ፡ ልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ ለምንስ ፡ ዛሬ ፡ ልትወጉኝ ፡
፬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣችሁ ? አላቸው ። ዮፍታሔም ፡ ፬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣችሁ ? አላቸው ። ዮፍታሔም ፡
የገለዓድን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ÷ ከኤፍሬ የገለዓድን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ÷ ከኤፍሬ
ምም ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፡ ኤፍሬምም ፡— ገለዓዳው ምም ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፡ ኤፍሬምም ፡— ገለዓዳው
ያን ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ ያን ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡
መካከል ፡ የተቀመጣችሁት ፡ ከኤፍሬም ፡ ሸሽ መካከል ፡ የተቀመጣችሁት ፡ ከኤፍሬም ፡ ሸሽ
ታችሁ ፡ ነው ፡ ስላሉ ፡ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ኤፍሬ ታችሁ ፡ ነው ፡ ስላሉ ፡ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ኤፍሬ
፭ ፡ ምን ፡ መቱ ። ገለዓዳውያንም ፡ ኤፍሬም ፡ የሚ ፭ ፡ ምን ፡ መቱ ። ገለዓዳውያንም ፡ ኤፍሬም ፡ የሚ
ያልፍበትን ፡ የዮርዳኖስን ፡ መሻገሪያ ፡ ያዙ ፡ ያልፍበትን ፡ የዮርዳኖስን ፡ መሻገሪያ ፡ ያዙ ፡
ቸው ፤ የሸሸ ፡ የኤፍሬም ፡ ሰው ፡— ልለፍ ፡ ቸው ፤ የሸሸ ፡ የኤፍሬም ፡ ሰው ፡— ልለፍ ፡
ባለ ፡ ጊዜ ÷ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡— አንተ ፡ ኤፍ ባለ ፡ ጊዜ ÷ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡— አንተ ፡ ኤፍ
ሬማዊ ፡ ነህን ? አሉት ፡ እርሱም ፡ - አይደለ ሬማዊ ፡ ነህን ? አሉት ፡ እርሱም ፡ - አይደለ
፮ ፡ ሁም ፡ ቢል ÷ እንርሱ ፡— አሁን ፡ ሺቦሌት ፡ በል ፡ ፮ ፡ ሁም ፡ ቢል ÷ እንርሱ ፡— አሁን ፡ ሺቦሌት ፡ በል ፡
አሉት ፡ እርሱም ፡ አጥርቶ ፡ መናገር ፡ አልቻ አሉት ፡ እርሱም ፡ አጥርቶ ፡ መናገር ፡ አልቻ
ለምና ፡— ሲቦሌት ፡ አለ ፤ ይዘውም ፡ ብዮርዳ ለምና ፡— ሲቦሌት ፡ አለ ፤ ይዘውም ፡ ብዮርዳ
ኖስ ፡ መሻገሪያ ፡ አረዱት ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ከኤ ኖስ ፡ መሻገሪያ ፡ አረዱት ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ከኤ
፯ ፡ ፍሬም ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ወደቁ ። ፯ ፡ ፍሬም ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ወደቁ ።
ዮፍታሔም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡ ዮፍታሔም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡
ዓመት ፡ ፈረደ ። ገለዓዳዊውም ፡ ዮፍታሔ ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ። ገለዓዳዊውም ፡ ዮፍታሔ ፡

ሞተ ÷ ከገለዓድም ፡ ከተሞች ፡ በአንዲቱ ፡ ተቀ ሞተ ÷ ከገለዓድም ፡ ከተሞች ፡ በአንዲቱ ፡ ተቀ
በረ ። በረ ።
ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ልሔሙ ፡ ኢብ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ልሔሙ ፡ ኢብ ፲
ጻን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ ሆነ ። ሠላ ፡ ጻን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ ሆነ ። ሠላ ፡ ፲፩ ፡
ሳም ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሠላሳ ፡ ሴቶች ፡ ሳም ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሠላሳ ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ሠላሳ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹንም

ይሆናልና ፡ አሁን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያሰክ
ርም ፡ ነገር ፡ አትጠጪ ፡ ርኩስም ፡ ነገር ፡ አት
ብዪ ፡ አለኝ ፡ ብላ ፡ ተናገረች ።
ፍ፡ ማኑዔም ፡ — ጌታ ፡ ሆይ ፥ የላክኸው ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ሰው ፥ እባክህ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡
እኛ ፡ ይምጣ ፣ ለሚወለደውም ፡ ልጅ ፡ ምን ፡
እንድናደርግ ፡ ያስገንዝበን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግ
፱፡ ዚአብሔር ፡ ለመነ ። እግዚአብሔርም ፡ የማኑ
ሄን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መል
አክ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለሴቲቱ ፡ በእርሻ ፡ ውስጥ ፡ ተቀ
ምጣ ፡ ሳለች ፡ ተገለጠላት ፡ ባልዋ ፡ ማኑሄ ፡ ግን ፡
፲፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ አልነበረም ። ሴቲቱም ፡ ፈጥና ፡
ሮጠች ፡ ለባልዋም ፡ — እነሆ ፤ በቀደም ፡ ዕለት ፡
ወደ ፡ እኔ ፡ የመጣው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ተገለጠልኝ ፡
፲፩፡ ብላ ፡ ነገረችው ። ማኑዔም ፡ ተነሥቶ ፡ ሚስቱን ፡
ተከተለ ÷ ወደ ፡ ሰውዮውም ፡ መጥቶ ፡ — ፡
ከዚህች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ የተነጋገርህ ፡ አንተ ፡
ነህን ? አለው ። እርሱም ፡ — እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
፲፪፡ ማኑዔም ፡ — ቃልህ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የልጁ ፡
ሥርዓት ፡ ምንድር ፡ ነው ? የምናደርግለትስ ፡
፲፫፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ። የእግዚአብሔርም ፡
መልአክ ፡ ማኑዔን ፡ — ሴቲቱ ፡ ከነገርኋት ፡ ሁሉ ፡
፲፬፡ ትጠንቀቅ ። ከወይንም ፡ ከሚወጣው ፡ ሁሉ ፡
አትብላ ÷ የወይን ፡ ጠጅንም ፡ የሚያሰክርንም ፡
ነገር ፡ አትጠጣ ÷ ርኩስም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አት
ብላ ፤ ያዘዝኋትን ፡ ሁሉ ፡ ትጠብቅ ፡ አለው ።
፲፭፡ ማኑዔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ —
የፍየል ፡ ጠቦት ፡ እስክናዘጋጅልህ ፡ ድረስ ÷ አባ
፲፮፡ ክህ ÷ ቆይ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ መል
አክ ፡ ማኑዔን ፡ — አንተ ፡ የግድ ፡ ብትለኝ ፡
መብልህን ፡ አልበላም ፤ የሚቃጠለውንም ፡
መሥዋዕት ፡ ግዘጋጀት ፡ ብትወድድ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ አቅርበው ፡ አለው ። ማኑዔም ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ መልአክ ፡ መሆኑን ፡ አላወቀም ፡ ነበር ።
፲፯፡ ማኑዔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ — ነገ
ርህ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንድናከብርህ ፡ ስምህ ፡
፲፰፡ ማን ፡ ነው ? አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ መል
አክ ፡ — ስሜ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ፡ ለምን ፡ ትጠይ
፲፱፡ ቃለህ ? አለው ። ማኑዔም ፡ የፍየሉን ፡ ጠቦትና ፡
የእህሉን ፡ ቀርብን ፡ ወስዶ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ አቀረበው ። መልአኩም ፡
ተአምራት ፡ አደረገ ÷ ማኑዔና ፡ ሚስቱም ፡
፳፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። ነበልባሉም ፡ ከመሠዊያው ፡
ላይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ መልአክ ፡ በመሠዊያው ፡ ነበልባል ፡
ውስጥ ፡ ወረገ ፡ ማኑዔና ፡ ሚስቱም ፡ ተመለከቱ ÷
በምድርም ፡ በግምባራቸው ፡ ተደፉ ።
፳፩፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ዳግመኛ ፡ ለማ
ኑዔና ፡ ለሚስቱ ፡ አልተገለጠም ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡
ማኑዔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መሆኑን ፡
፳፪፡ አወቀ ። ማኑዔም ፡ ሚስቱን ፡ — እግዚአብሔ
ርን ፡ እይተናልና ፡ ሞት ፡ እንሞታለን ፡ አላት ።
፳፫፡ ሚስቱም ፡ — እግዚአብሔርስ ፡ ሊገድለን ፡ ቢወ
ድድ ፡ ናር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡
የእህሉን ፡ ቀርብን ፡ ከእጃችን ፡ ባልተቀበለን ÷
ይህንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በላሳየን ÷ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ነገርም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በላስታወቀን ፡ ነበር ፡ አለ
ችው ።
ሴቲቱም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ÷ ስሙ ፡ ፳፬፡
ንም ፡ ሶምሶን ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ ልጁም ፡ አደገ ፡
እግዚአብሔርም ፡ ባረከው ። የእግዚአብሔ ፡ ፳፭፡
ርም ፡ መንፈስ ፡ በጸርዓና ፡ በኤሽታኦል ፡ መካ
ከል ፡ ባለው ፡ በዳን ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ሊያነቃ
ቃው ፡ ጀመረ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ሶምሶንም ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ወረደ ÷ በተም ፡ ፩፡
ናም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ልጆች ፡ አንዲት ፡
ሴት ፡ አየ ። ወጥቶም ፡ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ፡ —
በተምና ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ልጆች ፡ አን ፡ ፪፡
ዲት ፡ ሴት ፡ አይቻለሁ ፤ አሁንም ፡ እርስዋን ፡
አጋቡኝ ፡ አላቸው ። አባቱና ፡ እናቱም ፡ — ፡ ፫፡
ካልተገረዙት ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ሚስት ፡
ለማግባት ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ ከወንድሞችህ ፡
ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከሕዝቤም ፡ ሁሉ ፡ መከከል ፡
ሴት ፡ የለምን ? አሉት ። ሶምሶንን ፡ አባቱን ፡ —
ለዓይኔ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኝታኛለችና ፡ እርስ
ዋን ፡ አጋባኝ ፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡ በፍ ፡ ፬፡
ልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ይፈልግ ፡
ነበርና ፡ ነገሩ ፡ ከእርሱ ፡ ሆነ ፤ አባቱና ፡ እናቱ ፡
ግን ፡ አላወቁም ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፍልስጥኤ
ማውያን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ገዦች ፡ ነበሩ ።
ሶምሶንም ፡ አባቱና ፡ እናቱም ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ፭፡
ወረዱ ÷ በተምናም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ወይኑ ፡
ስፍራ ፡ መጡ ፤ እነሆም ÷ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡
እያገሣ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ደረሰ ። የእግዚአብሔ
ርም ፡ መንፈስ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በኃይል ፡ ወረደ ፤
ጠቦትን ፡ እንደሚቈራርጥ ፡ በእጁ ፡ ምንም ፡
ሳይኖር ፡ ቈራረጠው ፤ ያደረገውንም ፡ ለአባ
ቱና ፡ ለእናቱ ፡ አልነገረም ። ወርዶም ፡ ከሴ ፡ ፮፡
ቲቱ ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ፤ እጅግም ፡ ደስ ፡ አሰኘ
ችው ። ከጥቂትም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሊያገባት ፡ ፯፡
ተመለሰ ÷ የአንበሳውንም ፡ ሬሳ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡
ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፤ እነሆም ÷ በአንበ
ሳው ፡ ሬሳ ፡ ውስጥ ፡ ንብ ፡ ሰፍሮበት ፡ ነበር ÷
ማርም ፡ ነበረበት ። በእጁም ፡ ወስዶ ፡ መንገድ ፡ ፰፡
ለመንገድ ፡ እየበላ ፡ ሄደ ፤ ወደ ፡ አባቱና ፡ ወደ ፡
እናቱ ፡ መጣ ÷ ማሩንም ፡ ሰጣቸው ÷ እነርሱም ፡
በሉ ፤ ማሩንም ፡ ከአንበሳው ፡ ሬሳ ፡ ውስጥ ፡
እንደ ፡ ወሰደ ፡ አልነገራቸውም ።
አባቱም ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ ወረደ ፤ ጎበዙችም ፡ ፲፡
እንዲህ ፡ ያደርጉ ፡ ነበርና ፡ ሶምሶን ፡ በዚያ ፡
በዓል ፡ አደረገ ። በዩትም ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ፲፩፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሌሎች ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ሰጡት ።
ሶምሶንም ፡ — እንቈቅልሽ ፡ ልስጣችሁ ፡ በሰባ ፡ ፲፪፡
ቱም ፡ በበዓሉ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ፈትታችሁ ፡
ብትነግሩኝ ÷ ሠላሳ ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስና ፡ ሠላሳ ፡
ልውጥ ፡ ልብስ ፡ እሰጣችኋለሁ ፤ መፍታትም ፡ ፲፫፡

ባትችሉ ፡ ሠላሳ ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስና ፡ ሠላሳ ፡
ልውጥ ፡ ልብስ ፡ ትሰጡኛላችሁ ፡ አላቸው ።
እነርሱም ፡ — እንድንሰማው ፡ እንቈቅልሽህን ፡
ንገረን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ — ከበላተኛ ፡ ውስጥ ፡ ፲፬፡
መብል ፡ ወጣ ፤ ከብርቱም ፡ ውስጥ ፡ ጥፍጥ ፡
ወጣ ፡ አላቸው ። ሦስት ፡ ቀንም ፡ እንቈቅልሹን ፡
መተርጐም ፡ አልቻሉም ።
በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ የሶምሶንን ፡ ሚስት ፡ — ፡ ፲፭፡
እንቈቅልሹን ፡ እንዲነግረን ፡ ባልሽን ፡ ሽንገ
ዪው ፡ አለዚያም ፡ አንቺንና ፡ የአባትሽን ፡ ቤት ፡
በእሳት ፡ እናቃጥላለን ፡ ወደዚህ ፡ ጠራችሁን ፡
ልትገፋን ፡ ነውን ? አሉአት ። የሶምሶንም ፡ ፲፮፡
ሚስት ፡ በፊቱ ፡ እያለቀሰች ፡ — በእውነት ፡ ጠል
ተኸኛል ÷ ከቶም ፡ አትወደኝም ፡ ለሕዝቤ ፡
ልጆች ፡ እንቈቅልሽ ፡ ሰጥተሃቸዋልና ፡ ትርጓሜ
ውንም ፡ አልነገርኸኝም ፡ አለችው ። እርሱም ፡ —
እነሆ ÷ ለአባቴና ፡ ለእናቴ ፡ አልነገርኋቸውም ÷ ፲፯፡
ለአንቺ ፡ እነግርሻለሁን ? አላት ። ሰባቱንም ፡ የበ
ዓል ፡ ቀን ፡ በፊቱ ፡ አለቀሰች ፤ እርስዋም ፡ ነገ
ንዋለችና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ነገረት ። ትር
ጉሜውንም ፡ ለሕዝብዋ ፡ ልጆች ፡ ነገረች ። በሰ ፡ ፲፰፡
ባተኛውም ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ ሳትገባ ፡ የከተማይቱ ፡
ሰዎች ፡ — ከማር ፡ የሚጣፍጥ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
ከአንበሳስ ፡ የሚበረታ ፡ ማን ፡ ነው ? አሉት ።
እርሱም ፡ — በጥጃዬ ፡ ባላረሳችሁ ፡ የእንቈቅል
ሽን ፡ ተርጓሜ ፡ ባላወቃችሁ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።
የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በላዩ ፡ በኃይል ፡ ፲፱፡
ወረደ ፤ ወደ ፡ አስቀሎናም ፡ ወረደ ÷ ከዚያም ፡
ሠላሳ ፡ ሰዎችን ፡ ገደለ ÷ ልብሳቸውንም ፡ ወስዶ ፡
እንቈቅልሹን ፡ ለፈቱት ፡ ሰዎች ፡ ሰጠ ። ቍጣ
ውም ፡ ነደደ ፡ ወደ ፡ አባቱም ፡ ቤት ፡ ጠጣ ። ፳፡
የሶምሶን ፡ ሚስት ፡ ግን ፡ ከተባበሩት ፡ ከሚዜ
ዎቹ ፡ ለአንደኛው ፡ ሆነች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በስንዴ ፡ መከር ፡ ጊዜ ፡ ሶም
ሶን ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ይዞ ፡ ሚስቱን ፡ ሊጠ
ይቅ ፡ ሄደና ፡ — ወደ ፡ ጫጉላ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡
ሚስቴ ፡ ልግባ ፡ አለ ፤ አባትዋ ፡ ግን ፡ እንዳይ
ገባ ፡ ከለከለው ። አባትዋም ፡ — ፈጽመህ ፡ የጠ
ላሃት ፡ መስሎኝ ፡ ለሚዜህ ፡ አጋባኋት ፤ ታናሽ ፡
እኅትዋ ፡ ከርስዋ ፡ ይልቅ ፡ የተዋበች ፡ አይደለ
ችምን ? እባክህ ÷ በእርስዋ ፡ ፋንታ ፡ አግባት ፡
አለው ። ሶምሶንም ፡ — ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ በደርግ ፡ እኔ ፡
ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ። ሶምሶንም ፡ ሄዶ ፡ ሦስት ፡
መቶ ፡ ቀበሮች ፡ ያዘ ፤ ችቦም ፡ ወስዶ ፡ ሁለት ፡
ሁለቱንም ፡ ቀበሮች ፡ በጅራታቸው ፡ አሰረ ÷
በሁለቱም ፡ ጅራቶች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ችቦ ፡
አደረገ ። ችቦውንም ፡ አንድዶ ፡ በቆመው ፡
በፍልስጥኤማውያን ፡ እህል ፡ መካከል ፡ ሰደዳ
ቸው ፤ ነዶውንም ፡ የቆመውንም ፡ እህል ፡ ወይ
ኑንም ፡ ወይራውንም ፡ አቃጠለ ። ፍልስጥኤ
ማውያንም ፡ — ይህን ፡ ያደረገው ፡ ማን ፡ ነው ?
አሉ ። እነርሱም ፡ — ሚስቱን ፡ ወስዶ ፡ ለሚ
ዜው ፡ አጋብቶበታልና ፡ የተምናዊው ፡ አማች ፡
ሶምሶን ፡ ነው ፡ አሉ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡
ወጥተው ፡ ሴቲቱንና ፡ አባትዋን ፡ በእሳት ፡ አቃ
ጠሉ ። ሶምሶንም ፡ — እናንተ ፡ እንዲሁ ፡ ብታ ፡ ፯፡
ደርጉ ፡ እኔ ፡ እበቀላችኋለሁ ÷ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ወርቻለሁ ፡ አላቸው ። እርሱም ፡ ጭን ፡ ጭና ፡ ፰፡
ቸውን ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ አገዳደል ፡ መታቸው ፡
ወርዶም ፡ በኤጣም ፡ ዓለት ፡ ባለው ፡ ዋሻ ፡
ውስጥ ፡ ተቀመጠ ።
ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወጡ ÷ በይሁዳም ፡ ፱፡
ሰፈሩ ÷ በሌሒ ፡ ላይም ፡ ተበታትነው ፡ ተቀ
መጡ ። የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ — በእኛ ፡ ላይ ፡ ፲፡
የወጣችሁት ፡ ለምንድር ፡ ነው ? አሉ ። እነር
ሱም ፡ — ሶምሶንን ፡ ልናስር ÷ እንዳደረገብንም ፡
ልናደርግበት ፡ መጥተናል ፡ አሉ ። ከይሁዳም ፡ ፲፩፡
ሰዎች ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ የሚያህሉ ፡ በኤጣም ፡
ዓለት ፡ ወዳለው ፡ ዋሻ ፡ ወርደው ፡ ሶምሶንን ፡ —
ገዦቻችን ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡
አታውቅምን ? ያደረግህብን ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡
ነው ? አሉት ። እርሱም ፡ — እንዳደረጉብኝ ፡ እን
ዲሁ ፡ አደረግሁባቸው ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ — ፲፪፡
አስረን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፈን ፡
ልንሰጥህ ፡ መጥተናል ፡ አሉት ። ሶምሶንም ፡ —
እናንተ ፡ እንዳትገድሉኝ ፡ ማሉልኝ ፡ አላቸው ።
እነርሱም ፡ — አስረን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፈን ፡ ፲፫፡
እንሰጥሃለን ፡ እንጂ ፡ እንገድልህም ፡ ብለው ፡
ተናገሩት ። በሁለትም ፡ አዲስ ፡ ገመድ ፡ አስ
ረው ፡ ከዓለቱ ፡ ውስጥ ፡ አወጡት ።
ወደ ፡ ሌሒ ፡ በመጣ ፡ ጊዜም ፡ ፍልስጥኤማ ፡ ፲፬፡
ውያን ፡ አልል ፡ እያሉ ፡ ተገናኙት ። የእግዚአ
ብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በኃይል ፡ ወረደበት ፤ ክንዱ
ዱም ፡ የታሰረበት ፡ ገመድ ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡
ተበላ ፡ እንደ ፡ ተልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ ሆነ ÷
ማሰሪያዎቹም ፡ ከእጁ ፡ ወደቁ ። አዲስም ፡ የአ ፡ ፲፭፡
ህያ ፡ መንጋጋ ፡ አገኘ ÷ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ወሰ
ደው ÷ በእርሱም ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ገደለ ።
ሶምሶንም ፡ — በአህያ ፡ መንጋጋ ፡ ክምር ፡ በክ ፡ ፲፮፡
ምር ፡ ላይ ፡ አድርጌአቸዋለሁ ፤ በአህያ ፡ መንጋጋ ፡
አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ገድያለሁ ፡ አለ ። መናገሩ ፡ ፲፯፡
ንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ መንጋጋውን ፡ ከእጁ ፡
ጣለ ፤ የዚያንም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ራማትሌሒ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ። እርሱም ፡ እጅግ ፡ ተጠምቶ ፡ ነበ ፡ ፲፰፡
ርና ፡ — አንተ ፡ ይህችን ፡ ታላቅ ፡ ማዳን ፡ በባሪ
ያህ ፡ እጅ ፡ ሰጥተሃል ፡ አሁንም ፡ በጥም ፡ እሞ
ታለሁ ÷ በልተገረዙትም ፡ እጅ ፡ እወድቃለሁ ፡
ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ። እግዚአብ ፡ ፲፱፡
ሔርም ፡ በሌሒ ፡ ያለውን ፡ አዘቅት ፡ ሰነጠቀ ÷
ከእርሱም ፡ ውኃ ፡ ወጣ ፤ እርሱም ፡ ጠጣ ÷
ነፍሱም ፡ ተመለሰች ÷ ተጠናከረም ። ስለዚ
ህም ፡ የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ዓይንሀቆሬ ፡ ብሎ ፡
ጠራው ፤ ይህም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በሌሒ ፡
አለ ። በፍልስጥኤማውያንም ፡ ዘመን ፡ በእስ ፡ ፳፡
ራኤል ፡ ላይ ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ ፡ ሶምሶንም ፡ ወደ ፡ ጋዛ ፡ ሄደ ፡ በዚያም ፡ ጋለ
፪ ፡ ሞታ ፡ ሴት ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ገባ ። የጋዛ ፡
ሰዎችም ፡ ሶምሶን ፡ መጣ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡
እንደ ፡ ገባ ፡ ሰሙ ፡ ፡ ከበቡትም ፡ ፡ ሌሊቱንም ፡
ሁሉ ፡ በከተማይቱ ፡ በር ፡ ሸመቁበት ፡ ፡ ― ማለዳ ፡
እንገድለዋለን ፡ ብለውም ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ በዝ
፫ ፡ ምታ ፡ ተቀመጡ ። ሶምሶንም ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡
ሌሊት ፡ ተኛ ፡ ፡ እኩለ ፡ ሌሊትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
ተነሥቶ ፡ የከተማይቱን ፡ በር ፡ መዝጊያ ፡ ያዘ ፡
ከሁለቱ ፡ መቃኖችና ፡ ከመወርወሪያውም ፡ ጋር ፡
ነቀለው ፡ ፡ በትከሻውም ፡ ላይ ፡ አደረገ ፡ ፡ በኬብ
ሮንም ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡
ተሸከሞት ፡ ወጣ ፡ በዚያም ፡ ጣለው ።
፬ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሶሬቅ ፡ ሸለቆ ፡ የነበረች ፡
ደሊላ ፡ የተባለች ፡ አንዲት ፡ ሴትን ፡ ወደደ ።
፭ ፡ የፍልስጥኤማውያንም ፡ መኳንንት ፡ ወደ ፡ እር
ስዋ ፡ ወጥተው ፡ ― እርሱን ፡ ሽንግለሽ ፡ በእርሱ ፡
ያለ ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፡
እኛስ ፡ እርሱን ፡ ለማዋረድ ፡ እናስረው ፡ ዘንድ ፡
የምናሸንፈው ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቂ ፡
እኛም ፡ እያንዳንዳችን ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡
ብር ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንሰጥሻለን ፡
፮ ፡ አሉአት ። ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፡ ― ታላቅ ፡ ኃይ
ልህ ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንድትዋረድስ ፡
የምትታሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እባክህ ፡
፯ ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ። ሶምሶንም ፡ ― በሰባት ፡
ባልደረቀ ፡ በእርጥብ ፡ ጠፍር ፡ ቢያስሩኝ ፡ እደ
ክማለሁ ፡ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እሆናለሁ ፡
፰ ፡ አላት ። የፍልስጥኤማውያንም ፡ መኳንንት ፡
ሰባት ፡ ያልደረቀ ፡ እርጥብ ፡ ጠፍር ፡ ፡ አመጡ
፱ ፡ ላት ፡ በእርሱም ፡ አሰረችው ። በጓዳዋም ፡
ውስጥ ፡ ሰዎች ፡ ተደብቀው ፡ ነበር ። እርስ
ዋም ፡ ― ሶምሶን ፡ ሆይ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡
መጡብህ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ የተልባ ፡
እግር ፡ ፈትል ፡ እሳት ፡ በሸተተው ፡ ጊዜ ፡ እን
ዲበጠስ ፡ ጠፍሩን ፡ በጣጠሰው ፡ ፡ ኃይሉም ፡
በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልታወቀም ።
፲ ፡ ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፡ ― እነሆ ፡ አታለልኸኝ ፡
የነገርኸኝም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ የምትታ
ሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እባክህ ፡ ንገረኝ ፡
፲፩ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ ― ሥራ ፡ ባልተሠራበት ፡
በአዲስ ፡ ገመድ ፡ ቢያስሩኝ ፡ እደክማለሁ ፡
፲፪ ፡ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እሆናለሁ ፡ አላት ። ደሊ
ላም ፡ አዲስ ፡ ገመድ ፡ ወስዳ ፡ በእርሱ ፡ አሰረ
ችው ፡ በጓዳዋም ፡ የተደበቁ ፡ ሰዎች ፡ ተቀም
ጠው ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ ― ሶምሶን ፡ ሆይ ፡
ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ። ገመ
ዱንም ፡ ከክንዱ ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ በጣጠሰው ።
፲፫ ፡ ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፡ ― እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡
አታለልኸኝ ፡ የነገርኸኝም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ የምት
ታሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ።
እርሱም ፡ ― የራሴን ፡ ጠጕር ፡ ሰባቱን ፡ ጉንጉን ፡
ከድር ፡ ጋር ፡ ብትጐነጉኘው ፡ በችካልም ፡ ብት
ቸክዪው ፡ እደክማለሁ ፡ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡
እሆናለሁ ፡ አላት ። ሶምሶንም ፡ በተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፲፬
ደሊላ ፡ የራሱን ፡ ጠጕር ፡ ሰባቱን ፡ ጉንጉን ፡
ከድሩ ፡ ጋር ፡ ጐነጐነችው ፡ በችካልም ፡ ቸከለ
ችውና ፡ ― ሶምሶን ፡ ሆይ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡
መጡብህ ፡ አለችው ። ከእንቅልፉም ፡ ነቃ ፡
ችካሉንም ፡ ከነቆንዳላው ፡ ድሩንም ፡ ነቀለ ።
፲፭ ፡ እርስዋም ፡ ― አንተ ፡ ― እወድድሻለሁ ፡ እን
ዴት ፡ ትሉኛለህ ፡ ፡ ልብህ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ አይደ
ለም ? ስንታታልለኝ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜህ ፡ ነው ፡
ታላቅ ፡ ኃይልህም ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልነ
ገርኸኝም ፡ አለችው ። ፡ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ፡ ፲፮
ልቀ ፡ ነዘነቸው ፡ አስቸገረችውም ፡ ፡ ነፍሱም ፡
እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ተጨነቀች ። እርሱም ፡ ፡ ፲፯
ከእናቴ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የተለየሁ ፡ ነኝና ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ ምላጭ ፡ አልደ
ረሰም ፡ የራሴንም ፡ ጠጕር ፡ ብላጭ ፡ ኃይሌ ፡
ከእኔ ፡ ይሄዳል ፡ ፡ እደክማለሁም ፡ ፡ እንደ ፡ ሌላም ፡
ሰው ፡ እሆናለሁ ፡ ብሎ ፡ የልቡን ፡ ሁሉ ፡ ገለጠ
ላት ። ደሊላም ፡ የልቡን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ገለጠ ፡ ፲፰
ላት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ― የልቡን ፡ ሁሉ ፡ ገልጦል
ኛልና ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ኑ ፡ ብላ ፡ ላከችና ፡
የፍልስጥኤማውያንን ፡ መኳንንት ፡ ጠራች ።
የፍልስጥኤማውያን ፡ መኳንንትም ፡ ብሩን ፡ በእ
ጃቸው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ መጡ ። እር ፲፱
ስዋም ፡ በጕልበትዋ ፡ ላይ ፡ አስተኛችው ፡ አንድ ፡
ሰውም ፡ ጠራች ፡ እርሱም ፡ ሰባቱን ፡ የራሱን ፡
ጉንጉን ፡ ላጨው ። ልታዋርደውም ፡ ጀመረች ፡ ፡
ኃይሉም ፡ ከእርሱ ፡ ሄደ ። እርስዋም ፡ ― ሶምሶን ፡ ፳
ሆይ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብህ ፡ አለችው ።
ከእንቅልፉም ፡ ነቅቶ ፡ ― እወጣለሁ ፡ እንደ ፡ ወት
ሮውም ፡ ጊዜ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡
እግዚአብሔር ፡ ከእርሱ ፡ እንደ ፡ ተለየው ፡ አላ
ወቀም ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ይዘው ፡ ዓይ ፳፩
ኖቹን ፡ አወጡት ፡ ወደ ፡ ጋዛም ፡ አምጥተው ፡
በናስ ፡ ሰንሰለት ፡ አሰሩት ፡ በግዘትም ፡ ሆኖ ፡
እህል ፡ ይፈጭ ፡ ነበር ። የራሱም ፡ ጠጕር ፡ ከላ ፳፪
ጨት ፡ በኋላ ፡ ያድግ ፡ ጀመር ።
የፍልስጥኤምም ፡ መኳንንት ፡ ― አምላካችን ፡ ፳፫
ጠላታችንን ፡ ሶምሶንን ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡
ሰጠን ፡ እያሉ ፡ ለአምላካቸው ፡ ለዳጎን ፡ ታላቅ ፡
መሥዋዕት ፡ ይሠው ፡ ዘንድ ፡ ደስም ፡ ይላቸው ፡
ዘንድ ፡ ተሰበሰቡ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ባዩት ፡ ፳፬
ጊዜ ፡ ― ምድራችንን ፡ ያጠፋውን ፡ ከእኛም ፡
ብዙ ፡ ሰው ፡ የገደለውን ፡ ጠላታችንን ፡ አምላ
ካችን ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠን ፡ እያሉ ፡
አምላካቸውን ፡ አመሰገኑ ። ልባቸውንም ፡ ፳፭
ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ― በፈታችን ፡ እንዲጫወት ፡
ሶምሶንን ፡ ጥሩት ፡ አሉ ። ሶምሶንንም ፡ ከግ
ዞት ፡ ቤት ፡ ጠሩት ፡ ፡ በፈታቸውም ፡ ተጫወተ ፡
ተዘባበቱበትም ፡ ፡ በምሰሶና ፡ በምሰሶም ፡ መካ
ከል ፡ አቆሙት ። ሶምሶንም ፡ እጁን ፡ የያዘውን ፡ ፳፮
ብላቴና ፡ ― ቤቱን ፡ የደገፉትን ፡ ምሰሶች ፡ እጠጋ

ባቸው ፡ ዘንድ ፡ እባክህ ፡ አስይዘኝ ፡ አለው ።
ዘፍጥ ፡ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ሞልተ
ውበት ፡ ነበር ፡ የፍልስጥኤምም ፡ መኳንንት ፡
ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ፡ ፡ በቤቱም ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡
ሶምሶን ፡ ሲጫወት ፡ የሚያይ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ የሚ
ያህሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።
ዘፍ ፡ ሶምሶንም ፡ ― ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ዓይኖቼ ፡ ፍል
ስጥኤማውያንን ፡ አሁን ፡ እንድበቀል ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ፡ እባክህ ፡ አስበኝ ፡
አምላክ ፡ ሆይ ፡ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እባ
ክህ ፡ አበርታኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራ ።
ዘፍ ፡ ሶምሶንም ፡ ቤቱ ፡ ተደግፎበቸው ፡ የነበሩትን ፡
ሁለቱን ፡ መካከለኞች ፡ ምሰሶች ፡ ያዘ ፡ አንዱን ፡
በቀኝ ፡ እጁ ፡ አንዱንም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡
ተጠጋባቸው ። ሶምሶንም ፡ ― ከፍልስጥኤማው ፡
ያን ፡ ጋር ፡ ልሙት ፡ አለ ፡ ፡ ተንጋብሶም ፡ ምሰሶ
ቹን ፡ በሙሉ ፡ ኃይሉ ፡ ገፋ ፡ ፡ ቤቱም ፡ በውስጡ ፡
በነበሩት ፡ በመኳንንቱም ፡ በሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ወደቀ ፡ በሞቱም ፡ የገደላቸው ፡ ሙታን ፡
ዘፍ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ከገደላቸው ፡ በዙ ። ወንድሞ
ቹም ፡ የአባቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ ሁሉ ፡ ወረዱ ፡ ፡
ይዘውም ፡ አመጡት ፡ በጾርዓና ፡ በኤሽታኦል ፡
መካከል ፡ ባለው ፡ በአባቱ ፡ በማኑሄ ፡ መቃብር ፡
ቀበሩት ። እርሱም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ሀያ ፡
ዓመት ፡ ፈረደ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ዘፍ ፡ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሚካ ፡
የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እናቱንም ፡ ―
ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ የተወሰደው ፡ የረገምሽበትም ፡
በጆሮዬም ፡ የተናገርሽበት ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡
መቶ ፡ ብር ፡ እነሆ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፡ እኔም ፡
ወስጄዋለሁ ፡ አላት ። እናቱም ፡ ― ልጄ ፡ ሆይ ፡ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ፡ አለችው ። አንዱን ፡
ሺህ ፡ አንዱን ፡ መቶ ፡ ብርም ፡ መለሰላት ፡ እና
ቱም ፡ ― ይህን ፡ ብር ፡ የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡
ቅልጠ ፡ የተሠራ ፡ ምስል ፡ አድርጌ ፡ ከእጄ ፡ ስለ ፡
ልጄ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እቀድሰዋለሁ ፡ ፡ አሁ
ንም ፡ ለአንተ ፡ እመልሰዋለሁ ፡ አለች ። ለእና
ቱም ፡ ገንዘቡን ፡ በመለሰላት ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡
ሁለቱን ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ወስዳ ፡ ለአንጥረኛ ፡ ሰጠ
ችው ፡ እርሱም ፡ የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡ ቅልጠ ፡
የተሠራ ፡ ምስል ፡ አደረገው ። ያም ፡ በሚካ ፡
ቤት ፡ ነበረ ። ሰውዮውም ፡ ሚካ ፡ የአምላክ ፡
ቤት ፡ ነበረው ፡ ኤፉድና ፡ ተራፊም ፡ አደረገ ፡ ፡
ከልጆቹም ፡ አንዱን ፡ ቀደሰው ፡ ፡ ካህንም ፡ ሆነ
ለት ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡
ንጉሥ ፡ አልነበረም ፡ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡
መልካም ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።
ዘፍ ፡ በቤተ ፡ ሌሔም ፡ ይሁዳም ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፡ ፡ እርሱም ፡ ሌዋዊ ፡
ነበረ ፡ ፡ በዚያም ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ። ይህም ፡
ሰው ፡ የሚቀመጥበትን ፡ ስፍራ ፡ ለመሻት ፡ ከከ
ተማው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ወጣ ፡ ሲሔ
ድም ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ አገር ፡
ወደ ፡ ሚካ ፡ ቤት ፡ መጣ ። ሚካም ፡ ― ከወዴት ፡ ፱
መጣህ ? አለው ። እርሱም ፡ ― ከቤተ ፡ ልሔም ፡
ይሁዳ ፡ የሆንሁ ፡ ሌዋዊ ፡ ነኝ ፡ ፡ የምቀመጥበት
ንም ፡ ስፍራ ፡ ለመሻት ፡ እሄዳለሁ ፡ አለው ።
ሚካም ፡ ― ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥ ፡ አባትና ፡ ፲
ካህንም ፡ ሁነኝ ፡ እኔም ፡ ልብሶችንና ፡ ምግብ
ህን ፡ በአየዓመቱም ፡ አሥር ፡ ብር ፡ እሰጥሃለሁ ፡
አለው ። ሌዋዊውም ፡ ገባ ። ሌዋዊውም ፡ ከሰ ፲፩
ውሮው ፡ ጋር ፡ መቀመጥን ፡ ፈቀደ ፡ ፡ ጕልማሳ
ውም ፡ ከልጆቹ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ሆነለት ።
ዘፍ ፡ ሚካም ፡ ሌዋዊውን ፡ ቀደሰ ፡ ፡ ጕልማሳውም ፡ ፲፪
ካህኑ ፡ ሆነለት ፡ በሚካም ፡ ቤት ፡ ነበረ ።
ዘፍ ፡ ሚካም ፡ ― ሌዋዊ ፡ ካህን ፡ ስለ ፡ ሆነልኝ ፡ እግ ፲፫
ዚአብሔር ፡ መልካም ፡ እንዲሠራልኝ ፡ አሁን ፡
አውቃለሁ ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

ዘፍ ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡
አልነበረም ። እስከዚያም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለዳን ፡
ነገድ ፡ በእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡
አልደረሰባቸውም ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሚ
ቀመጡባት ፡ ርስት ፡ ይሹ ፡ ነበር ። የዳንም ፡ ፪
ልጆች ፡ ከወገናቸው ፡ አምስት ፡ ጽኑዓን ፡ ሰዎች ፡
ምድሪቱን ፡ እንዲሰልሉና ፡ እንዲመረምሩ ፡ ―
ሂዱ ፡ ምድሪቱንም ፡ ሰልሉ ፡ ብለው ፡ ከጾርዓና ፡
ከኤሽታኦል ፡ ሰደዱ ። እነዚያም ፡ ወደ ፡ ተራራ
ማው ፡ ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሚካ ፡
ቤት ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ አደሩ ። በሚካ ፡ ቤት ፡ ፫
አጠገብም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ የሌዋዊውን ፡ የጮ
ልማሳውን ፡ ድምፅ ፡ አወቁ ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡
ቀርበው ፡ ― ወደዚህ ፡ ማን ፡ አመጣህ ? በዚ
ህስ ፡ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ? በዚህስ ፡
ምን ፡ አለህ ? አሉት ። እርሱም ፡ ― ሚካ ፡ እን ፬
ዲህ ፡ እንዲህ ፡ አደረገልኝ ፡ ቀጠረኝም ፡ እኔም ፡
ካህን ፡ ሆንሁለት ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ― የም ፭
ንሄድበት ፡ መንገድ ፡ የቀና ፡ መሆኑን ፡ እና
ውቅ ፡ ዘንድ ፡ እባክህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይ
ቅልን ፡ አሉት ። እርሱም ፡ ― የምትሄዱበት ፡ ፮
መንገድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ነውና ፡ በደ
ኅና ፡ ሂዱ ፡ አላቸው ።
አምስቱም ፡ ሰዎች ፡ ሄዱ ፡ ወደ ፡ ሌሳም ፡ ፯
መጡ ፡ በውስጡም ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ተዘ
ልለው ፡ አዩአቸው ፡ ፡ እንደ ፡ ሲዶናውያንም ፡
ልማድ ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠው ፡
ነበር ፡ የሚያስቸግራቸውም ፡ የሚገዛቸውም ፡
አልነበረም ፡ ፡ ከሲዶናውያንም ፡ ርቀው ፡ ከሰ
ውም ፡ ሁሉ ፡ ተለይተው ፡ ለብቻቸው ፡ ይኖሩ ፡
ነበር ። ወደ ፡ ወንድሞቻቸውም ፡ ወደ ፡ ጾር ፰
ዓና ፡ ወደ ፡ ኤሽታኦል ፡ ተመለሱ ፡ ወንድሞቻ
ቸውም ፡ ― ምን ፡ ወሬ ፡ ይዛችኋል ? አሉአ
ቸው ። እነርሱም ፡ ― ምድሪቱ ፡ እጅግ ፡ መል ፱
ካም ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አይተናልና ፡ ተነሡ ፡ ፡
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንውጣ ፡ እናንተ ፡ ዝም ፡ ትላ

ላችሁን ? ትሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ምድሪቱንም ፡ ለመ
፲ ፡ ውረስ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡ ቸል ፡ አትበሉ ። በሄዳ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ ተዘልለው ፡ ወደ ፡ ተቀመጡ ፡
ሕዝብ ፡ ትደርሳላችሁ ÷ ምድሪቱም ፡ ሰፊ ፡ ናት ፡
እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
እንዳች ፡ የማይጐድልበትን ፡ ስፍራ ፡ በእጃችሁ ፡
ሰጥቶአል ፡ አሉ ።
፲፩ ፡ ከዳን ፡ ወገንም ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ የታጠቁ ፡ ስድ
ስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ከዚያ ፡ ከጾርዓና ፡ ከኤሽ
፲፪ ፡ ታአል ፡ ተነሥተው ፡ ሄዱ ። ወጥተውም ፡ በይ
ሁዳ ፡ ባለችው ፡ በቂርያትይዓሪም ፡ ሰፈሩ ፡ ስለ
ዚህም ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
የዳን ፡ ሰፈር ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፤ እነሆም ÷ ከቂ
፲፫ ፡ ርያትይዓሪም ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡ ነው ። ከዚያም ፡
ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ አገር ፡
አለፉ ፡ ወደ ፡ ሚካም ፡ ቤት ፡ መጡ ።
፲፬ ፡ የሌሳን ፡ ምድር ፡ ሊሰልሉ ፡ ሄደው ፡ የነበሩት ፡
አምስቱ ፡ ሰዎችም ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ — በእነ
ዚህ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ኤፉድና ፡ ተራፊም ÷
የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስ
ልም ፡ እንዳሉ ፡ ታውቃላችሁን ? አሁንም ፡ የም
ታደርጉትን ፡ ምከሩ ፡ ብለው ፡ ተናገሩአቸው ።
፲፭ ፡ ከመንገዱም ፡ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ጕልማሳው ፡
ሌዋዊ ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡ ሚካ ፡ ቤት ፡
መጡ ÷ ደኅንነቱንም ፡ ጠየቁት ። የጦር ፡ ዕቃ ፡
የታጠቁት ÷ ከዳን ፡ ልጆችም ፡ የሆኑት ፡ ስድ
ስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ በደጃፉ ፡ አጠገብ ፡ ቆመው ፡
፲፮ ፡ ነበር ። ምድሪቱንም ፡ ሊሰልሉ ፡ ሄደው ፡ የነበ
ሩት ፡ አምስቱ ፡ ሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ወደዚያ ፡
ገቡ ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ኤፉዱንም ፡ ተራ
ፊሙንም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስልም ፡
ወሰዱ ፤ ካህኑም ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ከታጠቁት ፡ ከስ
ድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በደጃፉ ፡ አጠገብ ፡
፲፯ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ወደ ፡ ሚካ ፡ ቤት ፡
ገብተው ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ኤፉዱንም ፡
ተራፊሙንም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስ
ልም ፡ በወሰዱ ፡ ጊዜ ÷ ካህኑ ፡ — ምን ፡ ታደርጋ
፲፱ ፡ ላችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፡ — ዝም ፡ በል ÷
እጅህንም ፡ በአፍህ ፡ ላይ ፡ ጫን ÷ ከእኛም ፡
ጋር ፡ መጥተህ ፡ አባትና ፡ ካህን ፡ ሁንልን ፤ ለአ
ንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ካህን ፡ መሆን ፡ ወይስ ፡ በእ
ስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ለነገድና ፡ ለወገን ፡ ካህን ፡
፳ ፡ መሆን ፡ ማናቸው ፡ ይሻልሃል ? አሉት ። ካህ
ኑም ፡ በልቡ ፡ ደስ ፡ አለው ÷ ኤፉዱንም ፡ ተራ
ፊሙንም ፡ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ወሰደ ÷
በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ሄደ ።
፳፩ ፡ እነርሱም ፡ ዘረው ፡ ሄዱ ÷ ሕፃናቶችንና ፡ ከብ
ቶችን ፡ ዕቃዎችንም ፡ በፊታቸው ፡ አደረጉ ።
፳፪ ፡ ከሚካም ፡ ቤት ፡ በራቁ ፡ ጊዜ ፡ የሚካ ፡ ጐረቤ
ቶች ፡ ተሰበሰቡ ÷ የዳንንም ፡ ልጆች ፡ ተከት
፳፫ ፡ ለው ፡ ደረሱባቸው ። ወደ ፡ ዳንም ፡ ልጆች ፡
ጮኹ ÷ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ፊታቸውን ፡ መል
ሰው ፡ ሚካኤ ፡ — የምትጮኸው ፡ ምን ፡ ሆነህ ፡
፳፬ ፡ ነው ? አሉት ። እርሱም ፡ — የሠራኋቸውን ፡
አማልክቴን ፡ ካህኑንም ፡ ይዛችሁ ፡ ሄዳችኋል ፤
ሌላ ፡ ምን ፡ አለኝ ? እናንተስ ፡ — ምን ፡ ሆነ
ሃል ፡ እንዴት ፡ ትሉኛላችሁ ? አለ ። የዳንም ፡ ፳፭ ፡
ልጆች ፡ — የተቈጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይወድቁብህ ፡
ነፍስህም ፡ የቤተ ፡ ሰቦችህም ፡ ነፍስ ፡ እንዳይ
ጠፋብህ ÷ ድምፅህን ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ አታ
ሰማ ፡ አሉት ። የዳንም ፡ ልጆች ፡ መንገዳቸውን ፡ ፳፮ ፡
ሄዱ ፤ ሚካም ፡ ከእርሱ ፡ እንደ ፡ በረቱ ፡ በየ ፡
ጊዜ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።
እነርሱም ፡ ሚካ ፡ የሠራውን ፡ ጣዖትና ፡ ለእ ፳፯ ፡
ርሱ ፡ የነበረውን ፡ ካህን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሴሳ ÷
ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተዘልሎም ፡ ወደ ፡ ተቀመጠው ፡
ሕዝብ ÷ መጡ ፤ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቱአ
ቸው ፡ ከተማይቱንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ
አት ። ከተማይቱ ፡ ከሲዶና ፡ ራቅ ፡ ያለች ፡ ፳፰ ፡
ነበረችና ÷ እነርሱም ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ተለ
ይተው ፡ ብቻቸውን ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ የሚ
ታደግ ፡ አልነበራቸውም ። ሴሳም ፡ በቤትሮ
ዖብ ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ነበረች ።
ከተማይቱንም ፡ ሠርተው ፡ ተቀመጡባት ።
ከተማይቱንም ፡ ከእስራኤል ፡ በተወለደው ፡ ፳፱ ፡
በአባታቸው ፡ በዳን ፡ ስም ፡ ዳን ፡ ብለው ፡ ጠሩ
አት ፤ የከተማይቱም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ሴሳ ፡
ነበረ ። የዳንም ፡ ልጆች ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ፴ ፡
ለራሳቸው ፡ አቆሙ ፤ የሙሴም ፡ ልጅ ፡ የጌር
ሳም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ÷ እርሱና ፡ ልጆቹ ፡ የአ
ገሩ ፡ ሰዎች ፡ እስከሚማረኩበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
የዳን ፡ ነገድ ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ። ሚካም ፡ ያደ ፴፩ ፡
ረገውን ፡ የተቀረጸ ፡ ምስል ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ በሴሎ ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ አቆሙ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ፩ ፡
ንጉሥ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ በተራራማው ፡ በኤ
ፍሬም ፡ አገር ፡ ማዶ ፡ የተቀመጠ ፡ ሌዋዊ ፡ ነበረ ፤
ከቤተ ፡ ሌሔምም ፡ ይሁዳ ፡ ቁባት ፡ አገባ ። ፪ ፡
ቁባቱም ፡ አመነዘረችበት ÷ ትታውም ፡ ወደ ፡
አባትዋ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡
ሄደች ፤ በዚያም ፡ አራት ፡ ወር ፡ ተቀመጠች ።
፫ ፡ ባልዋም ፡ ተነሣ ÷ ከእርስዋም ፡ ዕርቅ ፡ ሽቶ ፡
ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሊመልሳት ፡ ፍለጋዋን ፡ ተከትሎ ፡
ሄደ ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ ሁለ
ትም ፡ አህዮች ፡ ነበሩ ። እርስዋም ፡ ወደ ፡ አባ
ትዋ ፡ ቤት ፡ አገባችው ፡ አባትዋም ፡ ባየው ፡
ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተገናኘው ። ፬ ፡ የብላቴናይ
ቱም ፡ አባት ፡ አማቱ ፡ የግድ ፡ አለ ÷ በቤቱም ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ፤ በሉም ÷ ጠጡም ÷
በዚያም ፡ አደሩ ። በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ ማል ፭ ፡
ደው ፡ ተነሡ ÷ እርሱም ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣ ፤
የብላቴናይቱም ፡ አባት ፡ አማቹን ፡ — ሰውነት
ህን ፡ በቀኑሽ ፡ እንጀራ ፡ አበርታ ÷ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ። ተቀመጡም ፡ በአ
ንድ ፡ ላይም ፡ በሉ ፡ ጠጡም ፤ የብላቴናይቱም ፡
አባት ፡ ሰውዮውን ፡ — ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ለማ
ደር ÷ እባክህ ÷ ፍቀድ ÷ ልብህንም ፡ ደስ ፡ ይበ
ለው ፡ አለው ። ሰውዮውም ፡ ሊሄድ ፡ ተነሣ ፡
አማቱ ፡ ግን ፡ የግድ ፡ አለው ÷ ዳግመኛም ፡
በዚያ ፡ አደረ ። ፮ ፡ በአምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ለመ
ሄድ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፤ የብላቴናይቱም ፡ አባት ፡ —
እባክህ ÷ ሰውነትህን ፡ አበርታ ፡ ቀኑም ፡ እስኪ
ዋገድ ፡ ድረስ ፡ ቆይ ፡ አለው ። ሁለቱም ፡ በሉ ። ፯ ፡
ሰውዮውም ፡ ከቁባቱና ፡ ከአሽከሩ ፡ ጋር ፡ ለመ
ሄድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የብላቴናይቱ ፡ አባት ፡
አማቱ ፡ — እነሆ ÷ ቀኑ ፡ ተዋግዶአል ፡ በዚህ ፡
እደሩ ፡ እነሆ ÷ ቀኑ ፡ ለማለፍ ፡ ተዋግዶአል ፡
ልባችሁ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ በዚህ ፡ እደሩ ፡
ነገም ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ እንድትደርሱ ፡ ማል
ዳችሁ ፡ መንገዳችሁን ፡ ትሄዳላችሁ ፡ አለው ።
፰ ፡ ሰውዮው ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ ለማደር ፡
አልፈቀደም ÷ ተነሥቶም ፡ ሄደ ÷ ኢየሩሳሌ
ምም ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ ወደ ፡ ኢያቡስ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ደረሰ ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ የተ
ጫኑ ፡ አህዮች ፡ ነበሩ ÷ ቁባቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
፱ ፡ ነበረች ። ወደ ፡ ኢያቡስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡
መሸባቸው ÷ አሽከሩም ፡ ጌታውን ፡ — ና ÷ ወደ
ዚህ ፡ ወደ ፡ ኢያቡሳውያን ፡ ከተማ ÷ እባክህ ÷
እናቅና ÷ በእርስዋም ፡ እንደር ፡ አለው ። ጌታ
ውም ፡ — ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ወዳልሆነች ፡
ወደ ፡ እንግዳ ፡ ከተማ ፡ አንገባም ፡ እኛ ፡ ወደ ፡
ጊብዓ ፡ እንለፍ ፡ አለው ። አሽከሩንም ፡ — ና ÷
ከእነዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ እንቅረብ ፡
በጊብዓ ፡ ወይም ፡ በራማ ፡ እንደር ፡ አለው ።
መንገዳቸውንም ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ፤ የብንያምም ፡
ነገድ ፡ በምትሆነው ፡ በጊብዓ ፡ አጠገብ ፡ ሳሉ ፡
፲ ፡ ፀሐይ ፡ ገባችባቸው ። በጊብዓም ፡ ገብተው ፡
ያድሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ አቀኑ ። በገባም ፡
ጊዜ ፡ ሊያሳድራቸው ፡ ማንም ፡ በቤቱ ፡ አልተ
ቀበላቸውምና ፡ በከተማው ፡ አደባባይ ፡ ተቀ
መጡ ።
፲፩ ፡ እነሆም ÷ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ከእርሻው ፡ ሥራ ፡
ወደ ፡ ማታ ፡ መጣ ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ ከተራራ
ማው ፡ ከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ነበረ ፤ በጊብዓም ፡
በእንግድነት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ የዚያ ፡ አገር ፡
፲፪ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ብንያማውያን ፡ ነበሩ ። ዓይኑ
ን ፡ አንሥቶ ፡ መንገደኛውን ፡ በከተማው ፡
አደባባይ ፡ አየ ፤ ሽማግሌውም ፡ — ወዴት ፡ ትሄዳ
ለህ ? ከወዴትስ ፡ መጣህ ? አለው ። እርሱም ፡ —
እኛ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ ተራራ
ማው ፡ ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ አገር ፡ ማዶ ፡ እናልፋለን ፤
እኔ ፡ ከዚያ ፡ ነኝ ÷ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ ይሁዳ ፡
ሄጄ ፡ ነበር ÷ አሁንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ እሄዳለሁ ፤ በቤቱም ፡ የሚያሳድረኝ ፡
፲፫ ፡ አጣሁ ፡ ለአህዮቻችን ፡ ገለባና ፡ ገፈራ ፡ አለን ፤
ለእኔና ፡ ለገረድህ ፡ ከባሪያዎችህም ፡ ጋር ፡
ላለው ፡ አሽከር ፡ እንጀራና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡
አለን ፤ አንዳችም ፡ አላጣንም ፡ አለው ። ሽማ
ግሌውም ፡ — ሰላም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፤
የምትሻውንም ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ እሰጥሃለሁ ፤ በአ

ደባባይ ፡ ግን ፡ አትደር ፡ አለው ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ፳ ፡
፲፬ ፡ አስገባው ÷ ለአህዮቹም ፡ ገፈራ ፡ ጣለላቸው ፡
እግራቸውንም ፡ ታጠቡ ÷ በሉም ፡ ጠጡም ።
ሰውነታቸውንም ፡ ደስ ፡ ባሰኙ ፡ ጊዜ ፡ ወስ ፳፪ ፡
ላቶች ፡ የሆኑ ፡ የከተማው ፡ ሰዎች ፡ ቤቱን ፡
ከበቡ ፡ በሩንም ፡ ይደበድቡ ፡ ነበር ፤ ባለቤቱንም ፡
ሽማግሌውን ፡ — ወደ ፡ ቤትህ ፡ የገባውን ፡ ሰው ፡
እንድንደርስበት ፡ አውጣልን ፡ አሉት ። ባለ ፳፫ ፡
ቤቱም ፡ ሽማግሌው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወጥቶ ፡ —
ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ ይህን ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ እባክ
ችሁ ፡ አታድርጉ ÷ ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡
ገብቶአልና ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ እት
ሥሩ ። ድንግል ፡ ልጄና ፡ የእርሱም ፡ ቁባት ፡ ፳፬ ፡
እነሆ ÷ አሉ ÷ አሁንም ፡ አወጣቸዋለሁ ፤ አዋ
ርዳአቸው ፡ እንደ ፡ ወደዳችሁም ፡ አድርጉባ
ቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንደ
ዚህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ አታድርጉ ፡ አላቸው ።
ሰዎቹ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ አልሰሙም ፡ ሰውዮ ፳፭ ፡
ውም ፡ ቁባቱን ፡ ይዞ ፡ አወጣላቸው ፡ ደረሱባ
ትም ÷ ሌሊቱንም ፡ ሁሉ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡
አመነዘሩበት ፤ ነህ ፡ በቀደይም ፡ ጊዜ ፡ ለቀቁ
አት ። ሴቲቱም ፡ ማለዳ ፡ መጣች ÷ ጌታዋም ፡ ፳፮ ፡
ባለበት ፡ በሰውዮው ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ወድቃ ፡ እስ
ኪነጋ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ቀረች ።
ጌታዋም ፡ ማለዳ ፡ ተነሣ ፡ የቤቱንም ፡ ደጅ ፡ ፳፯ ፡
ከፈተ ÷ መንገዱንም ፡ ለመሄድ ፡ ወጣ ፤ እነሆም ፡
ቁባቲቱ ፡ ሴት ፡ በቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ወድቃ ፡ እጅዋም ፡
በመድረክ ፡ ላይ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ — ተነሺ ÷ ፳፰ ፡
እንሂድ ፡ አላት ፤ እርስዋ ፡ ግን ፡ ሞታ ፡ ነበርና ፡
አልመለሰችም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በአህያው ፡ ላይ ፡
ጫናት ÷ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ሄደ ።
ወደ ፡ ቤቱም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ካራ ፡ አነሣ ÷ ቁባ ፳፱ ፡
ቱንም ፡ ይዞ ፡ ከአጥንቶችዋ ፡ መለያያ ፡ ላይ ፡
ለአሥራ ፡ ሁለት ፡ ቈራርጦ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡
አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰደደ ። ያየም ፡ ሁሉ ፡ — የእስራ ፴ ፡
ኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡
አልተደረገም ÷ አልታየምም ፡ አስቡት ÷ በዚ
ህም ፡ ተመካከሩ ÷ ተነጋገሩም ፡ ይባባል ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ወጡ ÷ ማኅ ፩ ፡
በሩም ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ድረስ ÷ ከገለ
ዓድም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ÷ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡
ተሰበሰቡ ። ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ የሆኑ ፡ ፪ ፡
የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አለቆች ፡ ሰይፍ ፡ በሚመዝዙ ፡
በቊጥርም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ እግረኞች ፡
በሆኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ጉባኤ ፡ ቆሙ ። ፫ ፡
የብንያምም ፡ ልጆች ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ወደ ፡ ምጽጳ ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ሰሙ ። የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ — ይህ ፡ ክፋ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡
ምን ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ንገሩን ፡ አሉ ። የተገደ ፪ ፡
ለችውም ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ሌዋዊው ፡ እንዲህ ፡

ብሉ ፡ መለሰላቸው ፡— እኔና ፡ ቁባቴ ፡ በዚያ ፡
ለማደር ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡
ፍ፡ መጣን ። የጊብዓም ፡ ሰዎች ፡ ተነሡብኝ ፡ ቤቱ
ንም ፡ በሌሊት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ከበቡት ፡ ሊገድ
ሉኝም ፡ ወደዱ ፡ በቁባቴም ፡ አጥብቀው ፡ አመ
ፍ፡ ነዘሩባት ፡ እርስዋም ፡ ሞተች ። እኔም ፡ ቁባ
ቴን ፡ ይገር ፡ ቈራረጥኋት ፡ በእስራኤልም ፡
ዘንድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአትና ፡ ስንፍና ፡
ስለ ፡ ተሠራ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ርስት ፡ አገር ፡
ፍ፡ ሁሉ ፡ ሰደዳሁ ። እነሆ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ሆይ ፡ ሁላችሁ ፡ ምክራችሁንና ፡ እዝናታች
ሁን ፡ በዚህ ፡ ስጡ ።
ሕ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነ
ሥተው ፡ አሉ ፡— ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ወደ ፡
ድንኳኑ ፡ አይሄድም ፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አይመለ
ስም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ የምናደር
ገው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በዕጣ ፡ እንወጣባታ
ፍ፡ ለን ። ወደ ፡ ብንያም ፡ ጊብዓ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡
እርስዋ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንዳደረገችው ፡
እንደ ፡ ስንፍናዋ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ለሕዝብ ፡
ስንቅ ፡ የሚይዙ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡
ከመቶው ፡ አሥር ፡ ሰው ፡ ከሺሁም ፡ መቶ ፡
ሰው ፡ ከአሥሩም ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡
ፍ፡ እንወስዳለን ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡ በከተማይቱ ፡
ላይ ፡ ተሰበሰቡ ።
ፍ፡ ፍ፡ የእስራኤልም ፡ ነገዶች ፡— በእናንተ ፡ መካ
ከል ፡ የተደረገ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡
ነው ? አሁንም ፡ እንድንገድላቸው ፡ ከእስራኤ
ልም ፡ ክፋትን ፡ እንድናርቅ ፡ በጊብዓ ፡ ውስጥ ፡
ያሉትን ፡ ምናምንቴዎቹን ፡ ሰዎች ፡ አውጥታ
ችሁ ፡ ስጡን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ነገድ ፡
ሁሉ ፡ ሰዎችን ፡ ላኩ ። የብንያም ፡ ልጆች ፡ ግን ፡
የወንድሞቻቸውን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
ፍ፡ ቃል ፡ ሊሰሙ ፡ አልወደዱም ። የብንያምም ፡
ልጆች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሊዋጉ ፡
ፍ፡ ከየከተማው ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ተሰበሰቡ ። በዚ
ያም ፡ ቀን ፡ ከየከተማው ፡ የመጡ ፡ የብንያም ፡
ልጆች ፡ ተቈጠሩ ፤ ቀኞቻቸውም ፡ ከጊብዓ ፡
ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ሀያ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ ሰይፍ ፡ የሚ
መዝዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ከጊብዓም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡
ፍ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጠሩ ። ከእነዚያም ፡
ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ የተመረጡ ፡ ግራኝ ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ድንጋይ ፡ ይወ
ነጭፉ ፡ ነበር ፤ አንዲት ፡ ጠጕርስ ፡ እንኳ ፡ አይ
ስቱም ።
ፍ፡ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ ሌላ ፡ የእስራኤል ፡
ሰዎች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመ
ዝዙ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጠሩ ፤ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ሰል
ፍ፡ ፈኞች ፡ ነበሩ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተነ
ሥተው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወጡ ፡ እግዚአብሔ
ርንም ፡— የብንያምን ፡ ልጆች ፡ ለመውጋት ፡
እስቀድሞ ፡ ማን ፡ ይውጣልን ? ብለው ፡ ጠየቁት ፡
እግዚአብሔርም ፡— ይሁዳ ፡ ይቅደም ፡ አለ ።

የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በማለዳ ፡ ተነሥተው ፡ ፲፱፡
በጊብዓ ፡ ፊት ፡ ሰፈሩ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ፳፡
ከብንያም ፡ ጋር ፡ ሊዋጉ ፡ ወጡ ፤ የእስራኤልም ፡
ሰዎች ፡ በጊብዓ ፡ አጠገብ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተሰ
ልፈው ፡ ቆሙ ። የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ከጊብዓ ፡ ፳፡፩፡
ወጡ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከእስራኤላውያን ፡ ሀያ ፡
ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ። ሕዝቡም ፡ የእ ፳፡፪፡
ስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ተበራቱ ፡ በፊተኛውም ፡
ቀን ፡ በተሰለፉበት ፡ ስፍራ ፡ ደግመው ፡ ተሰ
ለፉ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወጥተው ፡ በእ ፳፡፫፡
ግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ አለ
ቀሱ ፤ እግዚአብሔርንም ፡— ከወንድሞቻችን ፡
ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ዳግ
መኛ ፡ እንቀርባለን ? ብለው ፡ ጠየቁ ። እግዚአ
ብሔርም ፡— በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፡ አለ ።
ፍ፡ በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፳፡፬፡
ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሊዋጉ ፡ ቀረቡ ።
ፍ፡ በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ ብንያም ፡ ከጊብዓ ፡ በእነ ፳፡፭፡
ርሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
ደግሞ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፤
እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዝዙ ፡ ነበሩ ። ፳፡፮፡
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡
ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጡ ፡ አለቀሱም ፡
በዚያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተቀመጡ ፡
በዚያም ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ጾሙ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሚቃጠል ፡ የደኅን
ነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ ፳፡፯፡፳፡፰፡
የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ታቦት ፡ በዚያ ፡
ነበረና ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአ
ልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ በፊቱ ፡ ይቆም ፡ ነበ
ርና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡—
ከወንድሞቻችን ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡
ለመዋጋት ፡ ዳግመኛ ፡ እንውጣን ፡ ወይስ ፡ እን
ቅር ? ብለው ፡ ጠየቁ ። እግዚአብሔርም ፡— ነገ ፡
በእጃችሁ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁና ፡ ውጡ ፡
አለ ።
እስራኤልም ፡ በጊብዓ ፡ ዙሪያ ፡ የተደበቁ ፡ ፳፡፱፡
ሰዎች ፡ እኛሩበት ። በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የእ ፳፡፡
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ልጆች ፡
ወጡ ፡ በጊብዓም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡
ጊዜ ፡ ተሰለፉ ። የብንያምም ፡ ልጆች ፡ በሕዝቡ ፡ ፳፡፲፡
ላይ ፡ ወጡ ፡ ከከተማይቱም ፡ ተሳቡ ፡ እንደ ፡
ቀድሞውም ፡ ጊዜ ፡ በአውራዎቹ ፡ መንገዶች ፡
አንደኛው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ሁለተኛውም ፡
ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ሜዳ ፡ በሚወስዱት ፡ መንገዶች ፡
ላይ ፡ ሕዝቡን ፡ ይመቱ ፡ ይገድሉም ፡ ጀመር ፤
ከእስራኤልም ፡ ሠላሳ ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎችን ፡
ገደሉ ። የብንያምም ፡ ልጆች ፡— እንደ ፡ ቀድ ፡ ፳፡፳፡፡
ሞው ፡ በፊታችን ፡ ተመቱ ፡ አሉ ። የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡— እንሸሽ ፡ ከከተማም ፡
ወደ ፡ መንገድ ፡ እንሳባቸው ፡ አሉ ። የእስራኤ ፡ ፳፡፲፡፡
ልም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከስፍራቸው ፡ ተነሥተው ፡
በበአልታማር ፡ ተሰለፉ ። ከእስራኤልም ፡ ተደ
ብቀው ፡ የነበሩት ፡ ከስፍራቸው ፡ ከጊብዓ ፡ ሜዳ ፡

ፍ፡ ፍ፡ ወጡ ። ከእስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ የተመረጡ ፡
አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ አንጻር ፡
መጡ ፤ ሰልፍም ፡ በርትቶ ፡ ነበር ፤ መከራም ፡
ፍ፡ ፍ፡ እንዲያገኛቸው ፡ አላወቁም ፡ ነበር ። እግዚአ
ብሔርም ፡ ብንያምን ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ መታ ፤
በዚያም ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከብንያም ፡
ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡
ገደሉ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዝዙ ፡
ነበሩ ።
ፍ፡ ፍ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ተመቱ ፡ አዩ ፤
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ በኖ
ሩት ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ ታምነዋልና ፡ ለብንያም ፡
ፍ፡ ፍ፡ ስፍራ ፡ ሰቀቁላቸው ። ተደብቀውም ፡ የነበሩት ፡
ፈጥነው ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ሮጡ ፤ ተደብቀውም ፡
የነበሩት ፡ መጥተው ፡ ከተማውን ፡ ሁሉ ፡ በሰ
ፍ፡ ፍ፡ ይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ። የተደበቁትም ፡ ሰዎች ፡ ከከ
ተማው ፡ ብዙ ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ እንዲያ
ስነሡ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ በተደበቁት ፡
ሰዎች ፡ መካከል ፡ ምልክት ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።
ፍ፡ ፍ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከሰልፉ ፡ አፈገፈጉ ፤
ብንያማውያንም ፡— እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሰልፍ ፡
በፊታችን ፡ ተመትተዋል ፡ እያሉ ፡ ከእስራኤል ፡
ሰዎች ፡ ሠላሳ ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡ መምታትና ፡
መግደል ፡ ጀመሩ ። ምልክቱ ፡ በጢሱ ፡ ዓምድ ፡
ከከተማው ፡ ሲወጣ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ብንያማ
ውያን ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ተመለከቱ ፡ እነሆም ፡ ፡
የሞላ ፡ ከተማው ፡ ጥፋት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ። ፡
ፍ፡ ፍ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ፡ የብንያምም ፡
ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ አይ ፡
ፍ፡ ፍ፡ ተዋልና ፡ ደነገጡ ። ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡
ፊት ፡ ጀርባቸውን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ መንገድ ፡ ሸሹ ፤ ሰልፉም ፡ ተከታትሎ ፡ ደረ ፡
ሰባቸው ፡ ከየከተማውም ፡ የወጡት ፡ በመካ ፡
ፍ፡ ፍ፡ ከላቸው ፡ ገደሉአቸው ። ብንያማውያንንም ፡
ከበቡ ፡ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ እስካለው ፡
እስከ ፡ ጊብዓ ፡ አንጻር ፡ ድረስ ፡ አሳደዱአቸው ፡
ፍ፡ ፍ፡ በመኑሔም ፡ አጠፋአቸው ። ከብንያምም ፡
አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፤ እነዚህ ፡
ፍ፡ ፍ፡ ሁሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ። ከእነርሱም ፡ የተረፉት ፡
ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ሬሞን ፡
ዓለት ፡ ሸሹ ፡ ከእነርሱም ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡
አምስት ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ለቀሙ ፡ ወደ ፡ ጊድአ
ምም ፡ አሳደዱአቸው ፡ ከእነርሱም ፡ ሁለት ፡
ፍ፡ ፍ፡ ሺህ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ። እንዲሁም ፡ በዚያ ፡
ቀን ፡ ከብንያም ፡ የሞቱት ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡
ሰይፍ ፡ የሚመዝዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡
ፍ፡ ፍ፡ ሁሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ። ስድስቱም ፡ መቶ ፡
ሰዎች ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡
ሬሞን ፡ ዓለት ፡ ሸሹ ፡ በሬሞን ፡ ዓለት ፡ አራት ፡
ፍ፡ ፍ፡ ወር ፡ ተቀመጡ ። የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በብ
ንያም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ዳግመኛ ፡ ተመለሱ ፡ ሞላ
ውን ፡ ከተማ ፡ ከብቱንም ፡ ያገኙትንም ፡ ሁሉ ፡
በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፤ ያገኙትንም ፡ ከተማ ፡
ሁሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡— ከእኛ ፡ ማንም ፡ ፩፡
ሰው ፡ ልጁን ፡ ለብንያም ፡ ልጆች ፡ አያጋባ ፡
ብለው ፡ በምጽጳ ፡ ተማምለው ፡ ነበር ። ሕዝቡም ፡ ፪፡
ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ ፡
ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ጽኑ ፡ ልቅሶ ፡
አለቀሱ ። እንርሱም ፡— አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ ፫፡
አምላክ ፡ ሆይ ፡ ዛሬ ፡ ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡
መታጣቱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይህ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
ሆነ ? አሉ ። በነጋውም ፡ ሕዝቡ ፡ ማልደው ፡ ፬፡
ተነሡ ፡ በዚያም ፡ መሠዊያ ፡ ሠሩ ፡ የሚቃጠ
ልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕትንም ፡ አቀረቡ ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፭፡
ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ስላልወጣ ፡ ማን ፡ ነው ፡
ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ከጉባኤ ፡ ጋር ፡ ያለ ፡
ስለ ፡ ምን ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ መሐላ ፡ ምሎ ፡ ነበ
ርና ፡— ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልወጣ ፡ ማን ፡ ነው ?
አሉ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ወንድሞ ፡ ፮፡
ቻቸው ፡ ስለ ፡ ብንያም ፡ ልጆች ፡ ተጸጽተው ፡—
ዛሬ ፡ ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ጠፍቶአል ።
እኛ ፡ ልጆቻችንን ፡ እንዳንድርላቸው ፡ በእግዚ ፡ ፯፡
አብሔር ፡ ምለናልና ፡ የተረፉት ፡ ሚስቶችን ፡
እንዲያገኙ ፡ ምን ፡ እናድርግ ? አሉ ።
እነርሱም ፡— ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ እግ ፡ ፰፡
ዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ያልወጣ ፡ ማን ፡ ነው ?
አሉ ። እነሆም ፡ ከኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ወደ ፡
ሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ማንም ፡ አልወጣም ፡ ነበር ።
ሕዝቡም ፡ በተቈጠሩ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ በኢያቢስ ፡ ፱፡
ገለዓድ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ። ማኅበ ፡ ፲፡
ሩም ፡ ወደዚያ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ኃያላን ፡
ሰዎች ፡ ሰድደው ፡— ሂዱ ፡ በኢያቢስ ፡ ገለዓ
ድም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ከሴቶችና ፡ ከሕፃናት ፡
ጋር ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ግደሉ ። የምታደርጉ ፡ ፲፡፡
ትም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወንዱን ፡ ሁሉ ፡ ከወንድ ፡
ጋር ፡ የተኛችይቱንም ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማ
ችሁ ፡ አጥፉ ፡ ብለው ፡ አዘዙአቸው ። ወንድ ፡ ፲፡፪፡
ያላወቁ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ቈነጃጅት ፡ ደናግሎች ፡
በኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ በሚኖሩ ፡ መካከል ፡ አገኙ ፤
በከነዓንም ፡ አገር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡
ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ አመጡአቸው ።
ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ በሬሞን ፡ ዓለት ፡ ወዳሉት ፡ ፲፡፫፡
ወደ ፡ ብንያም ፡ ልጆች ፡ መልክተኞችን ፡ ላኩ ፡
በዕርቅ ፡ ቃልም ፡ ተናገሩአቸው ። በዚያም ፡ ፲፡፬፡
ጊዜ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፤ ከኢያ
ቢስ ፡ ገለዓድም ፡ ሴቶች ፡ ያዳኑአቸውን ፡ ሴቶች ፡
አገቡአቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚበቁ ፡ ሴቶች ፡
አላገኙም ። እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ፲፡፭፡
ነገድ ፡ ውስጥ ፡ ስብራት ፡ ስላደረገ ፡ ሕዝቡ ፡
ስለ ፡ ብንያም ፡ ተጸጸቱ ።
የማኅበሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡— ከብንያም ፡ ፲፡፮፡
ሴቶች ፡ ጠፍተዋልና ፡ የቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ሚስት ፡
እንዲያገኙ ፡ ምን ፡ እናደርጋለን ? አሉ ። ደግ ፡ ፲፡፯፡

ሞም ፡— ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይደ
መስስ ፡ ከብንያም ፡ ላመለጡት ፡ ርስት ፡ ይኑር ። ፲፯ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡— ልጁን ፡ ለብንያም ፡
የሚድር ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ምለዋልና ፡
እኛ ፡ ልጆቻችንን ፡ ለእነርሱ ፡ ማጋባት ፡ አይሆ
፲፰ ንልንም ፡ አሉ ። እነርሱም ፡— እነሆ ÷ በቤቴል ፡
በሰሜን ፡ በኩል ÷ ከቤቴልም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡
በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ÷
በለቦና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለችው ፡ በሴሎ ፡
የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ በየዓመቱ ፡ አለ ፡ አሉ ።
፳ የብንያምንም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አዘ
ዙአቸው ፡— ሂዱ ፡ በወይኑም ፡ ስፍራ ፡ ተደ
፳፩ በቁ ፤ ተመልከቱም ÷ እነሆም ÷ የሴሎ ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ አታሞ ፡ ይዘው ፡ ለዘፈን ፡ ሲወጡ ፡
ከወይኑ ፡ ስፍራ ፡ ውጡ ÷ ከሴሎም ፡ ሴቶች ፡
ልጆች ፡ ለየራሳቸሁ ፡ ሚስት ፡ ንጠቁ ÷ ወደ ፡
፳፪ ብንያም ፡ ምድርም ፡ ሂዱ ። አባቶቻቸውና ፡
ወንድሞቻቸውም ፡ ሊጣሉአችሁ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
በመጡ ፡ ጊዜ ፡— ስለ ፡ እኛ ፡ ማሩአቸው ፡ እኛ ፡
ሚስት ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በሰልፍ ፡ አልወሰድ
ንላቸውምና ÷ እናንተም ፡ በደል ፡ ይሆንባችሁ ፡
ስለ ፡ ነበረ ፡ አላጋባችኋቸውምና ÷ እንላቸኋ
ለን ። የብንያምም ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ÷ ፳፫
በቀኖዋቸውም ፡ መጠን ፡ ከተነጠቁት ፡ ዘፋ
ኞች ፡ ሚስት ፡ ወሰዱ ፡ ወደ ፡ ርስታቸውም ፡ ተመ
ልሰው ፡ ሄዱ ÷ ከተሞችንም ፡ ሠርተው ፡ ተቀ
መጡባቸው ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የእስራኤል ፡ ፳፬
ልጆች ፡ ከዚያ ፡ ተነሡ ÷ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡
ነገዱና ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ሄደ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡
ከዚያ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ተመለሰ ።

በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ ፳፭
አልነበረም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ መልካም ፡
መስሎ ፡ የታየውን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ሩት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ መሳፍንት ፡ ይፈርዱ ፡ በነ
በረ ፡ ጊዜ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ሆነ ። አንድ ፡
ሰውም ፡ ከሚስቱና ፡ ከሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ጋር ፡
በሞዓብ ፡ ምድር ፡ ሊቀመጥ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡
፪ ፡ ይሁዳ ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ። የሰውዮውም ፡ ስም ፡
አቢሜሌክ ፤ የሚስቱም ፡ ስም ፡ ኑኃሚን ፤ የሁ
ለቱም ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ መሐሎንና ፡ ኬሌዎን ፡
ነበረ ፡ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳም ፡ የኤፍራታ ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ። ወደ ፡ ሞዓብም ፡ ምድር ፡ መጡ ፡
፫ በዚያም ፡ ተቀመጡ ። የኑኃሚንም ፡ ባል ፡ አቤ
ሜሌክ ፡ ሞተ ፡ እርስዋና ፡ ሁለቱ ፡ ልጆችዋ ፡
፬ ቀሩ ። እነርሱም ፡ ከሞዓባውያን ፡ ሴቶች ፡
ሚስት ፡ አገቡ ፡ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ዖርፋ ፡ የሁ
ለተኛዪቱም ፡ ስም ፡ ሩት ፡ ነበረ ። በዚያም ፡
፭ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተቀመጡ ። መሐሎ
ንና ፡ ኬሌዎንም ፡ ሁለቱ ፡ ሞቱ ፡ ሴቲቱም ፡ ከሁ
ለቱ ፡ ልጆችዋና ፡ ከባልዋ ፡ ተለይታ ፡ ቀረች ።
፮ እርስዋም ፡ በሞዓብ ፡ ምድር ፡ ሳለች ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ እንደ ፡ ጐብኝ ፡ እንጀራም ፡
እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ሰማች ÷ ከሞዓብ ፡
ምድር ፡ ልትመለስ ፡ ከሁለቱ ፡ ምራቶችዋ ፡ ጋር ፡
፯ ፡ ተነሣች ። እርስዋም ፡ ከሁለቱ ፡ ምራቶችዋ ፡
ጋር ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ስፍራ ፡ ወጣች ፡ ወደ ፡
ይሁዳም ፡ ምድር ፡ ሊመለሱ ፡ በመንገድ ፡ ሄዱ ።
፰ ኑኃሚንም ፡ ምራቶችዋን ፡— ሂዱ ÷ ወደ ፡
እናቶቻችሁም ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ፡ በእኔና ፡ በሞ
ቱት ፡ እንዳደረጋችሁ ÷ እግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡
፱ ፡ ያድርግላችሁ ። እግዚአብሔር ፡ በየባላችሁ ፡
ቤት ፡ ዕረፍት ፡ ይስጣችሁ ፡ አለቻቸው ። ሳመ
ቻቸውም ፡ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡
አለቀሱ ። እነርሱም ፡— ከእንቺ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ፲
ሕዝብሽ ፡ እንመለሳለን ፡ አሉአት ። ኑኃሚንም ፡ ፲፩
አለች ፡— ልጆቼ ፡ ሆይ ÷ ተመለሱ ፡ ለምን ፡
ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትሄዳላችሁ ? በሎቻችሁ ፡ የሚ
ሆኑ ፡ ልጆች ፡ በሆይ ፡ አሉኝን ? ልጆቼ ፡ ሆይ ÷ ፲፪
ተመለሱ ፡ ባል ፡ ለማግባት ፡ እርጅቻለሁና ፡ ሂዱ ፡
ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ብል ÷ ዛሬ ፡ ሌሊትስ ፡ እንኳ ፡
ባል ፡ ባገባ ÷ ወንዶች ፡ ልጆችም ፡ ብወልድ ÷
እነርሱ ፡ እስኪያድጉ ፡ ድረስ ፡ ትቆያላችሁን ? ፲፫
ስለ ፡ እነርሱስ ፡ ባል ፡ ማግባት ፡ ትተቀላላችሁን ?
ልጆቼ ፡ ሆይ ÷ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ወጥቶአልና ፡ ከእናንተ ፡
የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ተመርሬአለሁ ። ድምፃቸው ፲፬
ንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አለቀሱ ፡
ያርፋም ፡ አማትዋን ፡ ሳመች ፡ ሩት ፡ ግን ፡ ተጠ
ጋቻት ። ኑኃሚንም ፡— እነሆ ÷ ባልንጀራሽ ፡ ፲፭
ወደ ፡ ሕዝብዋና ፡ ወደ ፡ አማልክትዋ ፡ ተመልሳ
ለች ፡ አንቺም ፡ ደግሞ ፡ ከባልንጀራሽ ፡ ጋር ፡ ተመ
ለሽ ፡ አለቻት ። ሩትም ፡— ወደምትሄጂበት ፡ ፲፮
እሄዳለሁና ÷ በምታድሪበትም ፡ አድራለሁና ፡
አንድተውሽ ፡ ከአንቺም ፡ ዘንድ ፡ አንድመለስ ፡
አታስቸግሪኝ ፡ ሕዝብሽ ፡ ሕዝቤ ÷ አምላክሽም ፡
አምላኬ ፡ ይሆናል ፡ በምትሞችበትም ፡ ስፍራ ፡ ፲፯
አሞታለሁ ÷ በዚያም ፡ እቀበራለሁ ፡ ከሞት ፡
በቀር ፡ አንቺንና ፡ እኔን ፡ አንዳች ፡ ቢለየን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፡ እንዲሁም ፡
ይጨምርብኝ ፡ አለች ። ኑኃሚንም ፡ ከእርስዋ ፡ ፲፰
ጋር ፡ ለመሄድ ፡ እንደ ፡ ቈረጠች ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡
እርስዋን ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ አለች ።

ሁሉቱም ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ድረስ ፡ ፲፱
ሄዱ ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡
የከተማይቱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡—

ይህች ፡ ኑኃሚን ፡ ናትን ? እያሉ ፡ ተንጫጩ ።
፳ እርስዋም ፡— ሁሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ አስ
መርሮኛልና ፡ ማሩ ፡ በሉኝ ፡ እንጂ ፡ ኑኃሚን ፡
፳፩ ፡ አትበሉኝ ። በሙላት ፡ ወጣሁ ÷ እግዚአብሔ
ርም ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ባዶዬን ፡ መለሰኝ ፤ እግዚአ
ብሔር ፡ አዋርዶኛልና ÷ ሁሉንም ፡ የሚችል ፡
አምላክ ፡ አስጨንቆኛልና ፡ ኑኃሚን ፡ ለምን ፡
፳፪ ፡ ትሉኛላችሁ ? አለቻቸው ። ኑኃሚንም ፡ ከእ
ርስዋም ፡ ጋር ፡ ከሞዓብ ፡ ምድር ፡ የተመለሰ
ችው ፡ ሞዓባዊቱ ፡ ምራትዋ ፡ ሩት ፡ ተመለሱ ። ፳፫
የገብስም ፡ መከር ፡ በተጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ ልሔም ፡ መጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ለኑኃሚንም ፡ ባል ፡ የሚዘመደው ፡ ከአቤሜ
ሌክ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ኃያል ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ በዔዝ ፡
፪ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ሞዓባዊቱም ፡ ሩት ፡
ኑኃሚንን ፡— በፊቴ ፡ ሞገስ ፡ የማገኘውን ፡ ተከ
ትዬ ፡ እህል ፡ እንድቃርም ፡ ወደ ፡ እርሻ ፡ ልሂድ ፡
አለቻት ። እርስዋም ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ ሂጂ ፡
፫ ፡ አለቻት ። ሄደችም ÷ ከአጫጆችም ፡ በኋላ ፡
በእርሻ ፡ ውስጥ ፡ ቃረመች ፤ እንደ ፡ አጋጣሚ
ውም ፡ የአቤሜሌክ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡
፬ ፡ ወደ ፡ በዔዝ ፡ እርሻ ፡ ደረሰች ። እነሆም ÷ በዔዝ ፡
ከቤተ ፡ ልሔም ፡ መጣ ÷ አጫጆችንም ፡— እግ
ዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አላቸው ።
፭ እነርሱም ፡— እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ፡ ብለው ፡
መለሱለት ። በዔዝም ፡ በአጫጆች ፡ ላይ ፡
አዛዥ ፡ የነበረውን ፡ ሰውዬውን ፡— ይህች ፡
፮ ፡ ቆንጆ ፡ የማን ፡ ናት ? አለው ። የአጫጆቹም ፡
አዛዥ ፡— ይህችማ ፡ ከሞዓብ ፡ ምድር ፡ ከኑኃ
ሚን ፡ ጋር ፡ የመጣች ፡ ሞዓባዊቱ ፡ ቆንጆ ፡ ናት ፡
፯ ፡ እርስዋም ፡— ከአጫጆቹ ፡ በኋላ ፡ በነጆው ፡
መከከል ፡ እንድቃርምና ፡ እንድለቅም ÷ እባ
ክህ ÷ ፍቀድልኝ ፡ አለች ፤ መጣችም ÷ ከማለ
ዳም ፡ ጀምራ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ቆይታ
ለች ፡ በቤትም ፡ ዋቂት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ አላረፈ
ችም ፡ አለው ።

፰ በዔዝም ፡ ሩትን ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ ትሰሚያለ
ሽን ? ቃርሚያ ፡ ለመቃረም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ እርሻ ፡
አትሂጂ ÷ ከዚህም ፡ አትላወሺ ÷ ነገር ፡ ግን ፡
ገረዶቼን ፡ ተጠጊ ። ወደሚያጭዱበትም ፡
ስፍራ ፡ ተመልከቺ ÷ ተከተያቸውም ፡ እንዳያ
ስቸግሩሽም ፡ ጐበዛዝቱን ፡ አዝዣለሁ ፡ በተ
ጠማሽም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማድጋው ፡ ሄደሽ ፡ ጐበ
፱ ፡ ዛዝቱ ፡ ከቀዱት ፡ ውኃ ፡ ጠጪ ፡ አላት ። በግም
ባርዋም ፡ ተደፍታ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰገደች
ለት ፡— እኔንስ ፡ ለመቀበል ፡ በምን ፡ ነገር ፡ በፊ
ትህ ፡ ሞገስ ፡ አገኘሁ ? እኔ ፡ እንግዳ ፡ አይደለ
ሁምን ? አለችው ። በዔዝም ፡— ባልሽ ፡ ከሞተ ፡
በኋላ ፡ አባትሽንና ፡ እናትሽን ፡ የተወለድሽበ
ትንም ፡ ምድር ፡ ትተሽ ፡ ቀድሞ ፡ ወደማታውቂ
ው ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ መጣሽ ÷ ለአማትሽ ፡ ያደ
ረግሽውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ሰምቻለሁ ። ፲፪
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሥራሽ ፡ ይስጥሽ ፡ ከክ
ንፋም ፡ በታች ፡ መጠጊያ ፡ እንድታገኚ ፡ በመ
ጣሽበት ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ ደመወዝሽ ፡ ፍጹም ፡ ይሁን ፡
አላት ። እርስዋም ፡— ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ ከባሪያዎ ፲፫
ችህ ፡ እንደ ፡ አንዳቱ ፡ ሰልሆን ፡ አጽናንተኸኛ
ልና ÷ የባሪያህንም ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ አሰኝተሃልና ፡
በዓይንህ ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለችው ።

፲፬ በምሳም ፡ ጊዜ ፡ በዔዝ ፡— ወደዚህ ፡ ቅረቢ ፡
ምሳ ፡ ብዪ ÷ እንጀራሽንም ፡ በሆምጣጤው ፡ አጥ
ቅሽ ፡ አላት ። በአጫጆቹም ፡ አጠገብ ፡ ተቀመ
ጠች ፡ የተጠበሰም ፡ እሸት ፡ ሰጣት ÷ በልታም ፡
ጠገበች ÷ አተረፈችም ። ደግሞም ፡ ልትቃ ፲፭
ርም ፡ በተነሣች ፡ ጊዜ ፡ በዔዝ ፡ ጐበዛዝቱን ፡—
በነጆው ፡ መካከል ፡ ትቃርም ÷ እናንተም ፡ አታ
ሳፍሩአት ፤ ደግሞ ፡ ከነጆው ፡ እስቀርታችሁ ፡ ፲፮
ተዉላት ፤ እርስዋም ፡ ትቃርም ÷ አትውቀሱ
አትም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

በእርሻውም ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ፲፯
ቃረመች ፤ የቃረመችውንም ፡ ወቃችው ፤
አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ያህልም ፡ ገብስ ፡
ሆነ ። ተሸከማውም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባች ÷ ፲፰
አማትዋም ፡ የቃረመችውን ፡ አየች ፤ ከጠገበ
ችም ፡ በኋላ ፡ የተረፋትን ፡ አውጥታ ፡ ሰጠቻት ።
አማትዋም ፡— ዛሬ ፡ ወዴት ፡ ቃረምሽ ? ወዴ ፲፱
ትስ ፡ ሠራሽ ? የተቀበለሽ ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፡
አለቻት ። እርስዋም ፡— ዛሬ ፡ የሠራሁበት ፡
ሰው ፡ ስም ፡ በዔዝ ፡ ይባላል ፡ ብላ ፡ በማን ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሠራች ፡ ለአማትዋ ፡ ነገረቻት ።
ኑኃሚንም ፡ ምራትዋን ፡— ቸርነቱን ፡ በሕያዋ ፲፡
ንና ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡ አልተወምና ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፡ አለቻት ። ኑኃሚ
ንም ፡ ደግሞ ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ የቅርብ ፡ ዘመዳ
ችን ፡ ነው ÷ እርሱም ፡ ሊቤዠን ፡ ከሚችሉት ፡
አንዱ ፡ ነው ፡ አለቻት ። ሞዓባዊቱ ፡ ሩትም ፡— ፳፡
ደግሞ ፡— መከሬን ፡ እስከ ፡ ጨርሱ ፡ ድረስ ፡ ጐበ
ዛዝቴን ፡ ተጠጊ ፡ አለኝ ፡ አለቻት ። ኑኃሚንም ፡ ፳፪
ምራትዋን ፡ ሩትን ፡— ልጄ ፡ ሆይ ÷ ከገረዶቹ ፡
ጋር ፡ ብትወጪ ÷ በሌላም ፡ እርሻ ፡ በያገኙሽ ፡
መልካም ፡ ነው ፡ አለቻት ። ሩትም ፡ የገብሱና ፡ ፳፫
የስንዴው ፡ መከር ፡ እስኪ ፡ ጨረስ ፡ ድረስ ፡ ልት
ቃርም ፡ የበዔዝን ፡ ገረዶች ፡ ተጠጋች ፡ በአማ
ትዋም ፡ ዘንድ ፡ ትቀመጥ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ አማትዋም ፡ ኑኃሚን ፡ አለቻት ፡— ልጄ ፡
ሆይ ÷ መልካም ፡ እንዲሆንልሽ ፡ ዕረፍት ፡ አል
ፈልግልሽምን ? አሁንም ፡ ከገረዶቹ ፡ ጋር ፡ የነበ ፲
ርሽበት ፡ በዔዝ ፡ ዘመዳችን ፡ አይደለምን ?
እነሆ ÷ እርሱ ፡ በዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በአውድማው ፡
ላይ ፡ ገብሱን ፡ በመንሽ ፡ ይበትናል ። እንግ ፲፡
ዲህ ፡ ታጠቢ ÷ ተቀቢ ÷ ልብስሽን ፡ ተላበሺ ÷
ወደ ፡ አውድማውም ፡ ውረጂ ፤ ነገር ፡ ግን ፡
መብሉንና ፡ መጠጡን ፡ እስኪ ፡ ጨርስ ፡ ድረስ ፡

፪ ለሰውዮው ፡ አትታዩው ። በተኛም ፡ ጊዜ ፡
የሚተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ተመልከቺ ÷ ገብተ
ሽም ፡ እግሩን ፡ ግለጪ ÷ ተጋደሚም ፡ የምታ
፭ ደርጊውንም ፡ እርሱ ፡ ይነግርሻል ። ሩትም ፡—
የተናገር ሽኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለቻት ።
፮ ወደ ፡ አውድማውም ፡ ወረደች ÷ አማት
፯ ዋም ፡ ያዘዘቻትን ፡ ሁሉ ፡ አደረገች ። በዒዝም ፡
ከበላና ፡ ከጠጣ ፡ ሰውነቱንም ፡ ደስ ፡ ካሰኘ ፡
በኋላ ÷ በአህሉ ፡ ከምር ፡ አጠገብ ፡ ሊተኛ ፡
ሄደ ፡ ሩትም ፡ በቀስታ ፡ መጣች ÷ እግሩንም ፡
ገልጣ ፡ ተኛች ። መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ በሆነ ፡
ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ደነገጠ ÷ ዘወርም ፡ አለ ፤ እነ
ሆም ÷ አንዲት ፡ ሴት ፡ በእግርጌው ፡ ተኝታ ፡
፱ ነበረች ። እርሱም ፡— ማን ፡ ነሽ ? አለ ። እርስ
ዋም ፡— እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ሩት ፡ ነኝ ፡ ዋርሳዩ ፡ ነህና ፡
ልብስህን ፡ በባሪያህ ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ፡ አለችው ።
፱ በዒዝም ፡ አላት ፡— ልጂ ፡ ሆይ ÷ በእግዚአብ
ሔር ፡ የተባረክሽ ፡ ሁኚ ፤ በለጠጋም ፡ ድህም ፡
ብለሽ ፡ ጉበዛዝትን ፡ አልተከተልሽምና ፡ ከፊ
ተኛው ፡ ይልቅ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ቸርነት ፡
፲፩ አድርገሻል ። አሁንም ÷ ልጂ ፡ ሆይ ÷ አትፍሪ ፡
በአገሬ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ምግባረ ፡ መል
ካም ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ሆንሽ ፡ ያውቃሉና ፡ ያልሽ
፲፪ ውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደርግልሻለሁ ። የቅርብ ፡
ዘመድ ፡ መሆኔ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡
፲፫ ከእኔ ፡ የቀረበ ፡ ዘመድ ፡ አለ ። ዛሬ ፡ ሌሊት ፡
እደሪ ፡ ነገም ፡ እርሱ ፡ ዋርሳ ፡ መሆን ፡ ቢወድድ ፡
መልካም ፡ ነው ÷ ዋርሳ ፡ ይሁን ፤ ዋርሳ ፡ ሊሆን ፡
ባይወድድ ፡ ግን ÷ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ! እኔ ፡
ዋርሳ ፡ እሆንሻለሁ ፡ አስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ተኚ ።
፲፬ እስኪነጋም ፡ በእግርጌው ፡ ተኛች ፡ በዒዝም ፡—
ሴት ፡ ወደ ፡ አውድማው ፡ እንደ ፡ መጣች ፡
ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ገና ፡
፲፭ ሰውና ፡ ሰው ፡ ሳይተያይ ፡ ተነሣች ። እር
ሱም ፡— የለበስሽውን ፡ ኩታ ፡ አምጥተሽ ፡
ያዢው ፡ አላት ፤ በያዘችም ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡
መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰፈረላት ፡ አሸከማትም ።
፲፮ እርሱም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ ሄደ ። ወደ ፡ አማ
ትዋም ፡ መጣች ÷ አማትዋም ፡— ልጂ ፡ ሆይ ÷
እንዴት ፡ ነሽ ? አለቻት ፡ እርስዋም ፡ ሰውዮው ፡
፲፯ ያደረገላትን ፡ ሁሉ ፡ ነገረቻት ። ወደ ፡ አማ
ትሽ ፡ ባዶ ፡ እጅሽን ፡ አትሂጂ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡
፲፰ ስድስት ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰጠኝ ፡ አለቻት ። እር
ስዋም ፡— ልጂ ፡ ሆይ ÷ ሰውዮው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡
ዛሬ ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ አያርፍምና ፡ ፍጻ
ሜው ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ በዪ ፡ አለች ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ በዒዝም ፡ ወደ ፡ ከተማይቱ ፡ በር ፡ አደባባይ ፡
ወጥቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ። እነሆም ÷ በዒዝ ፡
ስለ ፡ እርሱ ፡ ይናገር የነበረው ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡
ሲያልፍ ፡ በዒዝ ፡— አንተ ፡ ቀርበህ ፡ በዚህ ፡
ተቀመጥ ፡ አለው ። እርሱም ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ተቀ
፪ መጠ ። በዒዝም ፡ ከከተማይቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡
አሥር ፡ ሰዎች ፡ ጠርቶ ፡— በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡
አላቸው ። እነርሱም ፡ ተቀመጡ ። በዒዝም ፡ ፫
የቅርብ ፡ ዘመዱን ፡— ከሞዓብ ፡ ምድር ፡ የተመ
ለሰችው ፡ ኑኃሚን ፡ የወንድማችንን ፡ የአቤሜ
ሌክን ፡ ጢንጣ ፡ ትሸጣለች ። እኔም ፡ በዚህ ፡ ፬
በተቀመጡት ፡ በሕዝቤ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡
እንድትገዛው ፡ አስታውቅህ ፡ ዘንድ ፡ አሰብሁ ።
መቤዠት ፡ ብትወድድ ፡ ተቤዠው ፡ መቤዠት ፡
በትወድድ ፡ ግን ፡ ከእንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወራሽ ፡
የለምና ÷ እኔም ፡ ከእንተ ፡ በኋላ ፡ ነኝና ፡ እንዳ
ውቀው ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። እርሱም ፡— እቤዠ
ዋለሁ ፡ አለው ። በዒዝም ፡— እርሻውን ፡ ከኑ ፫
ኃሚን ፡ እጅ ፡ በምትገዛበት ፡ ቀን ÷ ለሞተው ፡
በርስቱ ፡ ስሙን ፡ እንድታስነሣለት ፡ ከምዋቹ ፡
ሚስት ፡ ከሞዓባዊቱ ፡ ከሩት ፡ ደግሞ ፡ ትገዛለህ ፡
አለ ። የቅርብ ፡ ዘመዱም ፡— የራሴን ፡ ርስት ፡
እንዳላበላሽ ፡ መቤዠት ፡ አልችልም ፤ እኔ ፡
መቤዠቱን ፡ አልችልምና ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡ መቤ
ዠቱን ፡ ውሰደው ፡ አለ ።
በጥንት ፡ ጊዜም ÷ ማንም ፡ ቢሸጥ ፡ ቢለው ፯
ጥም ÷ ነገሩን ፡ ለማጽናት ፡ ሰው ፡ ጫማውን ፡
እንዲያወልቅ ፡ ለባልንጀራውም ፡ እንዲሰጠው ፡
በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በእ
ስራኤል ፡ ምስክር ፡ ነበረ ። የቅርብ ፡ ዘመዱም ፡
በዒዝን ፡— አንተ ፡ ግዛው ፡ አለው ፤ ጫማው ፡
ንም ፡ አወለቀ ። በዒዝም ፡ ሽማግሌዎችንና ፡ ፱
ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡— ለአቤሜሌክና ፡ ለኬሌዎን ፡
ለመሐሉንም ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ከኑኃሚን ፡
እጅ ፡ እንደ ፡ ገዛሁ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡
ናችሁ ። ደግሞም ፡ የምዋቹ ፡ ስም ፡ ከወንድ ፡ ፲
ሞቹ ፡ መካከል ፡ ከእንሩም ፡ ደጅ ፡ እንዳይጠፋ ÷
የምዋቹን ፡ ስም ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ እንዳስነሣ ፡
የመሐሉንን ፡ ሚስት ፡ ሞዓባዊቱን ፡ ሩትን ፡
ሚስት ፡ ትሆነኝ ፡ ዘንድ ፡ ወሰድሁአት ፤ እና
ንተም ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ፡ አላቸው ።
በከተማይቱ ፡ በር ፡ አደባባይም ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ፲፩
ሁሉ ፡ ሽማግሌዎቹም ፡— እኛ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፡
እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ የምት
ገባውን ፡ ሴት ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡
ሠሩ ፡ እንደ ፡ ሁለቱ ፡ እንደ ፡ ራሔልና ፡ እንደ ፡
ልያ ፡ ያድርጋት ፤ አንተም ፡ በኤፍራታ ፡ ባለ
ጠጋ ፡ ሁን ÷ ስምህም ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ይጠራ ።
ቤትህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚህች ፡ ቈንጆ ፡ ከሚ ፡ ፲፪
ሰጥህ ፡ ዘር ፡ ትዕማር ፡ ለይሁዳ ፡ እንደ ፡ ወለደ
ችው ፡ እንደ ፡ ፋሬስ ፡ ቤት ፡ ይሁን ፡ አሉት ።
በዒዝም ፡ ሩትን ፡ ወሰደ ÷ ሚስትም ፡ ሆነ ፲፫
ችው ፡ ደረሰባትም ÷ እግዚአብሔርም ፡ ፅንስ ፡
ሰጣት ÷ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ። ሴቶችም ፡ ፲፬
ኑኃሚንን ፡— ዛሬ ፡ ዋርሳ ፡ ያላሳጣሽ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይባረክ ፡ ስሙም ፡ በእስራኤል ፡ ይጠራ ።
ከሰባትም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ለአንቺ ፡ ፲፭
ከምትሻል ፡ ከምትወድድሽ ፡ ምራት ፡ ተወል
ዶአልና ፡ ሰውነትሽን ፡ ያሳድሰዋል ÷ በእርጅና
ሽም ፡ ይመግብሻል ፡ አሉአት ። ኑኃሚንም ፡ ፲፮

ሕፃኑን ፡ ወሰደች ፡ አቀፈችውም ÷ ሞግዚትም ፡
ሆነችው ። ሴቶችም ፡ ጎረቤቶችዋ ፡ ለኑኃሚን ፡
ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደላት ፡ እያሉ ፡ ስም ፡ አወ
ጡለት ፡ ስሙንም ፡ ኢዮቤድ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።
እርሱም ፡ የዳዊት ፡ አባት ፡ የእሴይ ፡ አባት ፡ ነው ።
የፋሬስም ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ፋሬስ ፡
ኤስሮምን ፡ ወለደ ÷ ኤስሮምም ፡ አራምን ፡ ፲፱
ወለደ ÷ አራምም ፡ አሚናዳብን ፡ ወለደ ÷ አሚ ፳
ናዳብም ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ÷ ነአሶንም ፡ ሰል
ሞንን ፡ ወለደ ÷ ሰልሞንም ፡ በዒዝን ፡ ወለደ ÷ ፳፩
በዒዝም ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ÷ ኢዮቤድም ፡ ፳፪
እሴይን ፡ ወለደ ÷ እሴይም ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ።

(እርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ።)

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ከአርማ
ቴም ፡ መሴፋ ፡ የሆነ ፡ ስሙ ፡ ሕልቃና ፡ የተባለ ፡
ኤፍሬማዊ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ እርሱም ፡ የኢያሬም ፡
ኤል ፡ ልጅ ፡ የኢሊዮ ፡ ልጅ ፡ የቶሑ ፡ ልጅ ፡
የናሲብ ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ሁለትም ፡ ሚስቶች ፡
ነበሩት ፡ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ሐና ፡ የሁለተኛዪ
ቱም ፡ ስም ፡ ፍናና ፡ ነበረ ፤ ለፍናናም ፡ ልጆች ፡
ነበሩአት ÷ ለሐና ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አልነበራትም ።
፪ ያም ፡ ሰው ፡ በሴሎ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ለሠራ
ዊት ፡ ጌታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡
ከከተማው ፡ በየዓመቱ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። የእግ
ዚአብሔርም ፡ ካህናት ፡ ሁለቱ ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡
አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ። ሕልቃና ፡
የሚሠዋበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜም ፡ ለሚስቱ ፡
ለፍናና ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ ፡
እድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ሰጣቸው ። ሐናንም ፡ ይወ
ድድ ፡ ነበርና ፡ ለሐና ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ እድል ፡
ፈንታ ፡ ሰጣት ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ማኅፀን
ዋን ፡ ዘግቶ ፡ ነበር ። ፮ እግዚአብሔርም ፡ ማኅፀ
ንዋን ፡ ዘግቶ ፡ ነበርና ፡ ጣውንትዋ ፡ ታስቈጣት ፡
ታበሳጫትም ፡ ነበር ። በየዓመቱም ፡ እንዲህ ፡
ሲደረገ ፡ ጊዜ ፡ እርስዋም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
በምትወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ታበሳጫት ፡ ነበር ፤
ሐናም ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ÷ አንዳችም ፡ አትቀም
ስም ፡ ነበር ። ፰ ባልዋም ፡ ሕልቃና ፡— ሐና ፡
ሆይ ÷ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ ? ለምንስ ፡ አትቀም
ሺም ? ለምንስ ፡ ልብሽ ፡ ያዝንብሻል ? እኔስ ፡
ከአሥር ፡ ልጆች ፡ አልሻልልሽምን ? አላት ።
፱ በሴሎ ፡ ከበሉና ፡ ከጠጡ ፡ በኋላም ፡ ሐና ፡
ተነሣች ። ካህኑም ፡ ዔሊ ፡ በእግዚአብሔር ፡
መቅደስ ፡ መቃን ፡ አጠገብ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡
ተቀምጦ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ በልብዋ ፡ ትመ
ረር ፡ ነበር ÷ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ጸለየች ÷
ጽኑ ፡ ልቅሶም ፡ አለቀሰች ። እርስዋም ፡—
አቤቱ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ÷ የባሪያህን ፡
መዋረድ ፡ ተመልከተህ ፡ ብታስበኝ ÷ እኔንም ፡
ባትረሳ ÷ ለባሪያህም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ብትሰጥ ÷
ዕድሜውን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጠዋ
ለሁ ÷ ምላጭም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አይደርስም ፡
ብላ ፡ ስእለት ፡ ተሳለች ።
፲ ጸሎትዋንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባበ ፲፩
ዛች ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ አፍዋን ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።
ሐናም ፡ በልብዋ ፡ ትናገር ፡ ነበር ፤ ድምፅዋም ፡ ፲፪
ሳይሰማ ፡ ከንፈርዋን ፡ ታንቀሳቅስ ፡ ነበር ፤
ዔሊም ፡ እንደ ፡ ሰከረች ፡ ቈጠራት ። ፡ ዔሊም ፡—
ስከርሽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? የወይን ፡ ጠጅ ፡
ሽን ፡ ከእንቺ ፡ አርቂው ፡ አላት ። ፲፫ ሐናም ፡—
ጌታዬ ፡ ሆይ ÷ አይደለም ፡ እኔስ ፡ ልብዋ ፡ ያዘ
ነባት ፡ ሴት ፡ ነኝ ፤ ጠጅና ፡ ሴላ ፡ የሚያሰክር ፡
ነገር ፡ አልጠጣሁም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ነፍሴን ፡ አፈሰስሁ ፤ ኀዘኔና ፡ ጭን ፲፬
ቀቴ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ተናግሬ
አለሁና ፡ ባሪያህን ፡ እንደ ፡ ምናምንቴ ፡ ሴት ፡ አት
ቊጠረኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ። ዔሊም ፡— በደ ፲፭
ኅና ፡ ሂጂ ÷ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የለመን
ሽውን ፡ ልመና ፡ ይስጥሽ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ።
እርስዋም ፡— ባሪያህ ፡ በዓይንህ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ፲፮
ላግኝ ፡ አለች ። ሴቲቱም ፡ መንገድዋን ፡ ሄደች ፡
በላችም ÷ ፊትዋም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አዘ
ንተኛ ፡ መስሎ ፡ አልታየም ።
ማልደው ፡ ተነሥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፲፯
ፊት ፡ ሰገዱ ÷ ተመልሰውም ፡ ወደ ፡ እርማቴም ፡
ወደ ፡ ቤታቸው ፡ መጡ ። ሕልቃናም ፡ ሚስ
ቱን ፡ ሐናን ፡ አወቃት ፤ እግዚአብሔርም ፡
አሰባት ፤ የመፅነስዋም ፡ ወራት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ፳
ሐና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፤ እርስዋም ፡—
ከእግዚአብሔር ፡ ለምንዋለሁ ፡ ስትል ፡ ስሙን ፡
ሳሙኤል ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።
ሰውዮውም ፡ ሕልቃና ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ፳፩
ጋር ፡ የዓመቱን ፡ መሥዋዕትና ፡ ስእለቱን ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ። ሐና ፡ ፳፪
ግን ፡ አልወጣችም ÷ በልዋንም ፡— ሕፃኑ ፡
ጡት ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ እቀመጣለሁ ፡ ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታይ ፡
ዘንድ ÷ በዚያም ፡ ለዘላለም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
አመጣዋለሁ ፡ አለችው ። ፳፫ ሕልቃና ፡— ፡
በዓይንሽ ፡ ደስ ፡ ያሰኘሽን ፡ አድርጊ ÷ ጡትም ፡
እስኪተው ፡ ድረስ ፡ ተቀመጪ ፤ ብቻ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ቃሉን ፡ ያጽና ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡
ልጅዋን ፡ እያጠባች ፡ ጡት ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡
በቤትዋ ፡ ተቀመጠች ። ፳፬ ጡትም ፡ በተው ፡ ጊዜ ፡
ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ እርሱንና ፡ አንድ ፡ የሦስት ፡